ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ሥነ ጽሑፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

# የገፀባህርያት ሰብእና ውቅር በምህረት ደበበ ሌላ ሰው ረጅም ልቦለድ ውስጥ፤ ከፍሮይዳዊ ፍካሬ ልቦና አንፃር

በ

ባምላኩ አስማረ

ነሀሴ 2012 ዓ.ም

ጅማ

# የገፀባህርያት ሰብእና ውቅር በምህረት ደበበ ሌላ ሰው ረጅም ልቦለድ ውስጥ፤ ከፍሮይዳዊ ፍካሬ ልቦና አንፃር

ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት


በ

ባምላኩ አስማረ


አማካሪዎች

ዶክተር ማንያለው አባተ (ዋና)

አቶ ሀብታሙ እንግዳው (ረዳት)


ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ሥነ ጽሑፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር



ነሀሴ 2012 ዓ.ም

ጅማ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ሥነ ጽሑፍ - አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

# የገፀባህርያት ሰብእና ውቅር በምህረት ደበበ ሌላ ሰው ረጅም ልቦለድ ውስጥ፤ ከፍሮይዳዊ ፍካሬ ልቦና አንፃር

ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ

ባምላኩ አስማረ

ነሀሴ 2012 ዓ.ም

የፈተና ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም________________________________ፊርማ_______ቀን__________

የውስጥ ፈታኝ ስም___________________________ፊርማ_______ቀን__________

የውጭ ፈታኝ ስም____________________________ፊርማ_______ቀን__________

# ምስጋና

ይህ ጥናት ይህንን መልክና ቅርጽ ይዞ ይወጣ ዘንድ ገንቢ የሆኑ ሙያዊ አስተያየቶችን በመስጠት የተባበራችሁኝ አማካሪዎቼ ዶክተር ማንያለው አባተና አቶ ሀብታሙ እንግዳው ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

ለዚህ ጥናት ብቻ ሳይሆን ለሕይወት መሠረት የሚሆኑ አባታዊና ወንድማዊ ምክሮችን ለሰጣችሁኝና የፈለኩትን መረጃ በፈለኩት ጊዜ ወስጄ ጥሩ ስራ እንድሰራ ስታበረታቱኝ ለነበራችሁ ውድ አስተማሪዎቼ ተባባሪ ፕሮፌሰር ለማ ንጋቱ (ፒ.ኤች.ዲ.) እና ዶክተር ጌታቸው አንተነህ ያለኝ ምስጋና ከፍ ያለ ነው፡፡

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት ‹‹የገፀባህርያት ሰብእና ውቅር በምህረት ደበበ *ሌላ ሰው* ረጅም ልቦለድ ውስጥ፤ ከፍሮይዳዊ ፍካሬ ልቦና አንፃር›› በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን፣ ዋና ዓላማው የገፀባህርያት ሰብእና በልቦለዱ ታሪክ ውስጥ እንዴት እንደተዋቀረ መመርመር ነው፡፡ ንዑሳን ዓላማዎቹ ደግሞ የገፀባህርያቱን ሰብእና ከፍሮይዳዊ የፍካሬ ልቦና ሒስ አንፃር መፈከር፣ የገፀባህርያቱ ሰብእና የተዋቀረበትን ስልት መተንተን፣ እንዲሁም ይህ የሰብእና አወቃቀር ለልቦለዱ ታሪክ ያበረከተውን ኪናዊ ፋይዳ መለየት ናቸው፡፡ ጥናቱ የሥነ ጽሑፋዊ ጥናት እንደመሆኑ መጠን አይነታዊ የምርምር ዘዴንና ገላጭ የጥናት ንድፍን የተከተለ ሲሆን፣ የፍሮይዳዊ ፍካሬ ልቦና ትወራዊ ማህቀፍን በመጠቀም በተመረጠው ረጅም ልቦለድ ላይ ‹‹ጽሑፋዊ ትንታኔ›› (Textual Analysis) አካሒዷል፡፡ የተተነተኑት መረጃዎችም በ*ሌላ ሰው* ረጅም ልቦለድ ውስጥ ያሉ ገፀባህርያት ሰብእና በውስጣዊ የአእምሮ መዋቅር፣ ውስጣዊ የአእምሮ መዋቅር ከአካባቢ ጋር በሚኖረው መስተጋብር፣ ቤተሰብና ማህበራዊ ጉዳዮች በሚፈጥሩት ቁርኝት፣ በአካባቢና በማህበረሰብ በሚኖር መስተጋብርና በቤተሰብ አያያዝ እንደተዋቀረ ያሳያሉ፡፡ የትንተናው ውጤት አብዛኛዎቹ ገፀባህርያት የሰብእና መዛባት እንዳለባቸው፣ ለዚህ ያበቃቸው ደግሞ የሰብእና ውቅራቸው እንደሆነ፣ እንዲሁም ይህንን የሰብእና መዛባት ለማካካስም የተለያዩ ሥነ ልቦናዊ የጭንቀት መከላከያ ዘዴዎችን እንደሚጠቀሙ ያሳያል፡፡ የገፀባህርያቱ ሰብእና አወቃቀር ለልቦለዱ ጭብጥ ማጉያነት፣ እንዲሁም ለንግርና ምልሰት ማዋቀሪያነት አገልግሏል፡፡ ከእነዚህ ውጤቶች በመነሳትም ተደራስያን ልቦለዱን በሚያነቡበት ወቅት በገፀባህርያት ላይ የሚስተዋለው የሰብእና መዛባት ከሰብእና አወቃቀራቸው ጋር የሚያያዝ እንደሆነና የሰብእና መዛባቱ የሚፈጥርባቸውን ውጥረት ለመቀነስም ሥነ ልቦናዊ የጭንቀት መከላከያ ዘዴዎችን ተግባራዊ እንደሚያደርጉ ይህንን ሲያደርጉም ለልቦለዱ ቴክኒክ ማዋቀሪያነት ተገዥ ሆነው እንደቀረቡ ከግምት ውስጥ ቢያስገቡ የሚለው አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

## ማውጫ

ርዕስ ገጽ


ምስጋና ........................................ I

አጠቃሎ ........................................ II

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ ........................................ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ........................................ 2
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........................................ 5
1.3. የምርምር ጥያቄዎች ........................................ 6
1.4. የጥናቱ ዓላማዎች ........................................ 6
1.4.1. የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ ........................................ 6
1.4.2. የጥናቱ ንዑሳን ዓላማዎች ........................................ 6
1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ........................................ 7
1.6. የጥናቱ ወሰን ........................................ 7

ክለሳ ድርሳናት

ክለሳ ድርሳናት ........................................ 8

2.1. የንድፈ ሀሳባዊ ጽሑፍ ክለሳ ........................................ 8
2.1.1. የሰብእና ምንነት ........................................ 8
2.1.2. የሰብእና መዋቅር (Personality Structure) ........................................ 10
2.1.2.1. ኑባሬያዊ የልቦና ሞዴል (Topographic Model of the Psyche) ........................................ 10
2.1.2.2. መዋቅራዊ የልቦና ሞዴል (Structural Model of the Psyche) ........................................ 12
2.1.3. የሰብእና መዛባት (Personality Disorder) ........................................ 15
2.1.3.1. ምድብ ‹‹ሀ›› የሰብእና መዛባት (Cluster ‹‹A›› Personality Disorder) ...... 16
2.1.3.2. ምድብ ‹‹ለ›› የሰብእና መዛባት (Cluster ‹‹B›› Personality Disorder) ...... 18
2.1.3.3. ምድብ ‹‹ሐ›› የሰብእና መዛባት (Cluster C Personality Disorder) .......... 19
2.1.4. ሥነ ልቦናዊ የጭንቀት መከላከያ ስልቶች (Defense Mechanisms) ................. 20

2.1.5. ሥነ ጽሑፍና ፍካሬ ልቦና (Literature and Psychoanalysis) ........................ 23
2.2. ትወራዊ ማህቀፍ ........................................................................................ 25
2.3. የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ............................................................................ 27

ምዕራፍ ሦስት

የጥናቱ ሥነ ዘዴና ንድፍ ................................................................................... 32

3.1. የጥናቱ ዘዴ ............................................................................................ 32
3.2. የመረጃ ምንጭና አመራረጥ ......................................................................... 32
3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ........................................................................... 33
3.4. የመረጃ አደረጃጀትና መተንተኛ ስልት ............................................................ 33
3.4.1. የመረጃ አደረጃጀት ................................................................................ 33
3.4.2. የመረጃ መተንተኛ ስልት ........................................................................... 34

ምዕራፍ አራት

የገፀባህርያት ሰብእና ውቅር ትንተና በሌላ ሰው ረጅም ልቦለድ ውስጥ ................................. 35

4.1. የሌላ ሰው ረጅም ልቦለድ ጭምቅ ታሪክ ........................................................... 35
4.2. የገፀባህርያት ሰብእና አቀራረጽ ስልት በሌላ ሰው ረጅም ልቦለድ ውስጥ ........................ 37
4.2.1. ውስጣዊ የአእምሮ መዋቅር ከአካባቢ ጋር በሚኖረው መስተጋር ሰብእናቸው የተቀረጸ ገፀባህርያት ........................................................................................ 37
4.2.2. በቤተሰብና በማህበራዊ መስተጋብር ሰብእናቸው የተዋቀረ ገፀባህርያት ................. 44
4.2.3. ከቤተሰብ ተጽእኖ ጋር ተያይዞ ሰብእናቸው የተዋቀረ ገፀባህርያት ........................ 51
4.2.4. ከአካባቢና ከማህበረሰብ ጋር በሚኖር መስተጋብር ሰብእናቸው የተዋቀረ ገፀባህርያት ........................................................................................ 59
4.2.5. ውስጣዊ የአእምሮ መዋቅርን መሠረት በማድረግ ሰብእናቸው የተቀረጸ ገፀባህርያት ........................................................................................ 65
4.3. የገፀባህርያት ሰብእና ውቅር ኪናዊ ፋይዳ በሌላ ሰው ረጅም ልቦለድ ............................ 68

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያና አስተያየት ..................................................................................... 77

5.1. ማጠቃለያ ............ 77
5.2. አስተያየት ............ 78
ዋቢ ጽሑፎች ............ 79

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

ሥነ ጽሑፍ አሁን ከደረሰበት ደረጃ ላይ ለመድረስ የተለያዩ ሒደቶችን አልፏል፡፡ የሥነ ጽሑፍን ያህል ዕድሜ እንዳስቆጠረ የሚታመነው የሥነ ጽሑፍ ጥናትም ከክርስቶስ ልደት በፊት በነበሩት የአውሮፓ ፈላስፋዎች አማካኝነት የተጀመረ ሲሆን አድማሱን እያሰፋ፣ እየጠለቀና እየረቀቀ መጥቶ በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ደግሞ ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ መቅረብ ጀመረ፡፡ ቀስ በቀስም ወርዱን እያሰፋና ቁመቱን እያረዘመ ከሌሎች የሙያ መስኮች ጋር መጎራበት፣ መቀራረብ ብሎም መዛመድ ጀመረ፡፡ በመሆኑም ለሥነ ጽሑፍ ጥናት የሚያገለግሉ ትወራዎችንና ንድፈ ሃሳቦችን እየተዋሰና ለራሱ እንዲገዙ እያደረገ መጠቀም ሲጀምር በሒደት በይነ ዲሲፐሊናዊ (Interdisciplinary) ሆነ (ቴዎድሮስ፣ 2001፣ Xi) ፡፡ ከፍልስፍና፣ ከታሪክ፣ ከባህል ከስነ ልቦናና ከመሳሰሉት የእውቀት መስኮች ጋር በመተባበርም እየተጠና ይገኛል፡፡

ይህ ጥናትም ምህረት ደበበ *ሌላ ሰው* (2007) በሚል ርዕስ ለንባብ ባበቁት ረጅም ልቦለድ ላይ የሰብእናን ውቅር ከስነ ልቦናዊ ንድፈ ሀሳቦች አንፃር ተንትኗል፡፡ በመሆኑም በተመረጠው ረጅም ልቦለድ ውስጥ ያሉት ገፀባህርያት ሰብእና እንዴት እንደተዋቀረ፣ ሰብእናን ለመገንባት ጥቅም ላይ የዋሉ ዘዴዎች ምን ምን እንደሆኑ፣ በልቦለዱ ውስጥ የሚታዩ የሰብእና መዛባቶች ምንምን እንደሆኑ፣ ለሰብእና መዛባት የሚዳርጉ ሁኔታዎች እንዴት እንደቀረቡና በስነ ጽሑፍ ስራው ውስጥ እንዴት ተገዥ ሆነው እንደቀረቡ ተንትኗል፡፡ ለልቦለዱ ያበረከቱትን ኪናዊ ፋይዳም መርምሯል፡፡

ጥናቱ በአምስት ምዕራፎች ተደራጅቶ የቀረበ ሲሆን በመጀመሪያው ምዕራፍ ውስጥ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ዓላማዎች፣ የጥናቱ ጠቀሜታዎችና የጥናቱ ወሰን ቀርቧል፡፡ በሁለተኛው ምዕራፍ ላይ ከጥናቱ ጋር ተያያዥነትና ተዛማጅነት ያላቸው ጽንሰ ሀሳቦች፣ መረጃዎችን ለመተንተንና ለማብራራት የሚያስችለው ትወራዊ ማህቀፍ እና ከዚህ በፊት የተሰሩ ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው ተመሳስሎና ልዩነት ተፈትሾበታል፡፡ ምዕራፍ ሶስት የጥናቱ ስነ ዘዴና ንድፍ የቀረበበት ሲሆን በስሩም የጥናቱ ዘዴ፣ የመረጃ ምንጭና አመራረጥ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ፣ የመረጃ አደረጃጀትና የመተንተኛ ስልት በዝርዝር ተገልጸዋል፡፡ ምዕራፍ አራት መረጃው የተተነተነበትና የተብራራበት ክፍል ነው፡፡ ምዕራፍ አምስት ውስጥ ደግሞ ማጠቃለያና አስተያየት ቀርቧል፡፡

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

የሰብእና ጥናት ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረ ሲሆን የጥናቱ ጀማሪዎችም የአውሮፓ ፈላስፋዎችና ጸሐፊዎች ናቸው፡፡ ዛሬ ላይ የሚታየውና ዘመናዊው የሰብእና ጥናትም የእነዚህን ባለሙያዎች ፈለግ በማስተጋባት የተፈጠረ ነው፡፡ በስራቸው ውስጥ ሰብእናን ካስተዋወቁና ካጠኑ ቀደምት ምሁራንና ፈላስፋዎች መካከልም Plato (427-347)፣ Aristotle (384-322)፣ Rene Descartes (1596-1650) እና Niccolo Machiavelli (1469-1527)ን በዋናነት መጥቀስ እንደሚቻል Ellis፣ Abram እና Abrams (2009፣ 3-4) ያስረዳሉ፡፡ Plato ነፍስ (Soul) የሰው ልጅ የሰብእና ማደሪያ እንደሆነችና ባሕርይን ለመቅረጽ የሚያስችል ስሜት (Emotion)፣ ፍላጎት (Appetite) እና ምክንያት (Reason) የሚሉ ሶስት መሠረታዊ ኃይላትን በውስጧ እንደምታካትት በጥናታቸው (በተለይ The Republic በሚለው ታዋቂ መጽሐፋቸው ውስጥ) የገለጹ ሲሆን Aristotle ደግሞ ልቦና (Psyche) የሰው ልጆች የሰብእና ማደሪያ እንደሆነ በጥናታቸው አሳይተዋል፡፡ Descartes ሰብእና የመለኮታዊና መሠረታዊ ኃይል ድምር ውጤት እንደሆነ ሲገልጹ Machiavelli ደግሞ ሰብእና የማህበራዊ አውድ (Social context) ውጤት እንደሆነ አመላክተዋል (Ellis et al፣ 2009፣ 3-4)፡፡

ዘመናዊ የሰብእና ጥናት በስነ ልቦና ባለሙያዎች መጠናት የጀመረው ከ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመጀመሪያዎቹ አስርት ዓመታት ጀምሮ እንደሆነና መሠረቱ የተጣለው በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በምሁራን ዘንድ ይቀነቀኑ በነበሩት ግለኝነት (Individualism)፣ ኢምክንያታዊነት (Irrationality) እና ኢንቁ (Unconscious) በሚሉት ሶስት ጭብጦች እንደሆነ Winter እና Barenbaum (1999፣ 4) ይገልጻሉ፡፡ ሰብእና (Personality) የሚለው ቃልም እስከ 1920ዎቹ ድረስ የተቃወሰ ወይም ያልተለመደ (Abnormal) የሚለውን ሀሳብ ለመግለጽ በአእምሮ ህክምና ባለሙያዎች ዘንድ ይታወቅ እንደነበር ያስረዳሉ፡፡

ሰብእናን የሚመለከቱ የተለያዩ ስራዎችና ጽሑፎች ከ1908 እስከ 1928 ባሉት 20 ዓመታት ውስጥ ብቅ ብቅ ማለት ቢጀምሩም ሰብእና በምርምር ጥናት ላይ በህትመት መልኩ ለመጀመሪያ ጊዜ ብቅ ያለው በMcDougall (1932) እንደሆነ McAdams (1997፣ 4) ይገልጻሉ፡፡ *Characters and Personality* የሚል ርዕስ ይዞ ብቅ ያለው የMcDougall ጥናት የጀርመናውያንን፣ የእንግሊዛውያንንና የአሜሪካውያንን ግላዊ ሰብእና በማጥናት ላይ ያተኮረ

እንደነበረም ያስረዳሉ። በተጨማሪም Lewin (1935)፣ Allport (1937) እንዲሁም Murray (1938) በሰብእና ላይ የተለያዩ ጥናቶችን እንዳካሔዱ ያብራራሉ።

Susan (2009፣ 3) እንደሚገልጹት ሰብእና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ መጠናት የጀመረው Gordon Allport (1937) *Personality: A Psychological Interpretation* በሚል ርዕስ በሰብእና ላይ የሚያተኩር መጽሐፍ ለንባብ ካበቁ በኋላ ነው። ጥናቱ በሰብእና ጥናት ፊር ቀዳጅና ለአሁኑ የሰብእና ጥናትም መነሻ ሆኗል። ምንም እንኳ በሰብእና ጥናት ታሪክ ላይ ተጽዕኖ መፍጠር ባይችልም በዚሁ ዓመት Ross Stagner (1937) *Psychology of Personality* በሚል ርዕስ የጻፉትን መጽሐፍ ለንባብ እንዳበቁና Henry Murray (1938) ደግሞ *Explorations in personality* በሚል ርዕስ የተዘጋጀ መጽሐፍ እንዳቀረቡ ያስረዳሉ። እነዚህ በሰብእና ዙሪያ የሚያጠነጥኑ መጻሕፍት ለዘመናዊው የሰብእና ጥናት በር ከፋች ናቸው።

የሰብእና ጥናት መጀመሪያ አካባቢ ነሲባዊነት ወይም ወላዊነት (Holistic) የሚታይበት አካሔድ የሚከተል ነበር። ሁሉንም ሰዎች የጥናት ተሳታፊ በማድረግ የግለሰብን ሰብእና ለመመርመር ጥረት ያደርግ እንደነበር የሚገልጹት McAdam (1997፣4) በኋላ ላይ የሰብእና ስነ ልቦና ባለሙያዎች (Personality Psychologist) ሰብእናን ሙከራዊ (Expermental) በሆነ መንገድ ማጥናት ሲጀምሩና ሰብእና ከውጫዊ ቀስቃሾች (External Stimuli) ጋር ዝምድና እንዳለው ሲያረጋግጡ ሀሳባቸውን እንደቀየሩ ይገልጻሉ። በመሆኑም ለሁሉም ግለሰብ ዓለም አቀፋዊ በሆነ መንገድ ሊሰራ የሚችል የሰብእና ጥናት ህግን ለማስተዋወቅ እንደቻሉ ያስረዳሉ። ይኸውም ሰብእና ሰዎች በምን በምን ሁኔታዎች ይመሳሰላሉ? በምንስ ይለያያሉ? የሚሉትን ጥያቄዎች በመመለስ ላይ ማተኮር አለበት የሚል ነው። ባህላዊ የሰብእና ተመራማሪዎች[1] አብዛኛውን ጊዜ ለጤናማ ወይም መደበኛ ሰብእና ትኩረት ሲሰጡ በጣም በጥቂቱ ደግሞ ለሰብእና መዛባት ትኩረት ይሰጡ እንደነበር Lenzenweger እና Clarkin (2005፣ 5) ይገልጻሉ። የሰብእና ጥናት በአሁኑ ወቅት በተለያዩ የእውቀት ዘርፎች ቅንጅት ዘመናዊና ሳይንሳዊ አካሔድን ተከትሎ በመከናወን ላይ ይገኛል። ቀደም ሲል እንደሚስተዋሉት የሰብእና ጥናቶች አንድ ጽንፍ ብቻ ይዞ የሚጓዝ ሳይሆን ጤናማ ወይም መደበኛ እና የሰብእና መዛባት በሚሉ ሁለት ምድቦች ተከፍሎ ይጠናል። ለሰብእና ጥናት የሚያገለግሉ ሞዴሎችና ትወራዎችም እየተቀመሩ በስራ ላይ

---

[1] ባህላዊ የሰብእና ተመራማሪዎች በሚል የተገለጹት፣ ዘመናዊው የሰብእና ጥናት መካሔድ ከመጀመሩ በፊት ስለ ሰብእና ያጠኑ የነበሩት አካላት ናቸው። በመሆኑም ከ1937 በፊት በሰብእና ላይ ጥናት ያደርጉ የነበሩትን ምሁራን የሚገልጽ ነው። Plato፣ Aristotle፣ Descartes፣ Machiavelli፣ McDougall እና Lewin በባህላዊ የሰብእና ተመራማሪነት ለአብነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው።

ውለዋል። በዚህም ለሰብእና መቃወስ የሚዳርጉ ሁኔታዎችንና መፍትሔዎችን ለመጠቆም ጥረት እየተደረገ ይገኛል። ትወራዎቹም የተለያዩ የእውቀት ዘርፎችን በማስተሳሰርና በማገናኘት እንደ ድልድይ ሊያገለግሉ ችለዋል። ድንበር ተሻግረው ዝምድናንና ጉርብትናን በመፍጠር ከሚታወቁት የሰብእና ትወራዎች መካከል ፍካሬ ልቦናዊ ትወራ አንዱ ነው። ይህ ትወራ ትኩረቱን ካሳረፈባቸው የእውቀት መስኮች መካከል አንዱ ሥነ ጽሑፍ ነው። ፍካሬ ልቦና ገና ከጅምሩ ሥነ ጽሑፋዊ ስራዎችን ለራሱ እንዲመቹ በማድረግ እያለመደ ሲጠቀምባቸው ጉዳዩ ማህበረሰብ አቀፍ የሆነው ሥነ ጽሑፍም የፍካሬ ልቦናን መርሆች እና ንድፈ ሀሳቦች ለራሱ እንዲገዙ እያደረገ ለማጥኛነትና ለመተንተኛነት ሊጠቀምባቸው ችሏል።

የሰብእና ጥናት ከላይ በተገለጸው መልኩ ተጀምሮ አሁን ካለበት ደረጃ ላይ ለመድረስ የተለያዩ ሒደቶችን አልፏል። በሒደቱም የተለያዩ አከራካሪ ጉዳዮች በምርምር ታግዘው እየቀረቡ የእውቀት መስኩን ለማዳበር ተችሏል። በተለይ ደግሞ ከሥነ ጽሑፋዊ ስራዎች ጋር አስተሳስሮ ለማጥናት ችግሮች ነበሩ። ለዚህም በምክንያትነት ከሚጠቀሱት ጉዳዮች መካከል አንዱ በሥነ ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙትን የገሀዱ ዓለም ሰዎች ወኪሎች (ገፀባህርያት) ሰው አይደሉም (ልቦና የላቸውም)፤ ሰው ካልሆኑ ደግሞ ሰብእናቸው ሊጠና አይገባም የሚለው እሳቤ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ Tyson (2006፣35) አንዳንድ ሀያስያን ፍካሬ ልቦናን (Psychoanalysis)ን በመጠቀም የገፀባህርያት ባሕርይ መረዳትንም ሆነ ማጥናትን እንደሚቃወሙ ይገልጻሉ። እነዚህ ሀያስያን እንደ ምክንያት የሚያቀርቡትም በሥነ ጽሁፍ ስራዎች ውስጥ የሚገኙ ገፀባህርያት ተጨባጭ አይደሉም (ምናባዊ ናቸው)፤ ተጨባጭ ካልሆኑ ልቦና (Psyche) የላቸውም፤ ይህ ካልሆነ ደግሞ በፍካሬ ልቦና መርሆች ሊተነተኑ አይገባም የሚለው እንደሆነ ያስረዳሉ። ይሁን እንጂ ፍካሬ ልቦናን ገፀባህርያትን ለመተንተንም ይሁን ባሕርያቸውን ለማሳየት መጠቀም እንደሚቻል ይመክራሉ። ገፀባህርያትን በፍካሬ ልቦና ማጥናት ተጨባጭ ሰው ናቸው ማለት ሳይሆን የገሀዱ አለም ወኪል የሆኑት ገፀባህርያት የገሀዱ ዓለም ነፀብራቅ በሆነው የሥነ ጽሑፍ ስራ የሰውን ልጅ ስነ ልቦናዊ ልምድና ሁኔታ እንዴት ይዘው ተወክለዋል የሚለውን ለመመርመር እንደሚያስችል ያስገነዝባሉ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ገፀባህርያት የገሀዱ ዓለም ሰዎች ወኪሎች እንደመሆናቸው መጠን ሰብእናቸው በምን መልኩ ቀርቧል? የሚለውን መመርመርና መፈተሽ ተገቢ መሆኑ ታመነ። የተለያዩ የጥናት ስራዎችም ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ። በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች የሚገኙ የሥነ ጽሑፍ ምሁራንና ሀያስያንም ሰብእናን ከሥነ ልቦናዊ ትንተና ጋር በማዛመድ የሥነ

ጽሑፍ ስራዎችን በመመርመር ላይ ይገኛሉ፡፡ Robinson (1985)፣ Gill (1986)፣ Montes እና Alvarez (2004)፣ Johnson፣ Carroll፣ Gottschall እና Kruger (2010)፣ Kusumawati (2013)፣ Aras (2015)፣ Flekova እና Gurevych (2015) ሰብእናን ከሥነ ጽሑፍ ጋር በማዛመድ ጥናታቸውን አካሒደዋል፡፡ አብዛኛዎቹ የዋና ገፀባህርይውን ሰብእና በመመርመር ላይ ያተኮሩ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ የሥነ ጽሑፍ ስራውን ከደራሲው ጋር በማያያዝ የደራሲውን ሰብእና ለማጥናት የሚሞክሩ ናቸው፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ሥነ ጽሑፉ የበቀለበት ማህበረሰብ ሰብእና በሥነ ጽሑፍ ስራዎች ውስጥ እንዴት እንደተንጸባረቀ የሚፈትሹ ናቸው፡፡ የእነዚህ ተመራማሪዎች ጥናቶች ሰብእናን ከደራሲው በመነጠል በሥነ ጽሁፍ ስራዎች ውስጥ እንዴት እንደተዋቀረ፣ ከዋና ገፀባህርይው ውጭ ያሉት ገፀባህርያት ሰብእና ምን እንደሚመስልና ገፀባህርያት ይዘውት ለቀረቡት ሰብእና ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮች ምን ምን እንደሆኑ አልተመለከቱም፡፡ ይህ ጥናትም እነዚህን ክፍተቶች በመሙላት አስተዋጽኦ ያበረክታል ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለዚህም ሰብእና በሌላ ሰው ረጅም ልቦለድ ውስጥ እንዴት እንደተዋቀረ፣ በልቦለዱ ውስጥ ያሉ ገፀባህርያትን ሰብእና ለመቅረጽ ጥቅም ላይ የዋሉት ስልቶች ምን ምን እንደሆኑና እነዚህ ስልቶች ለልቦለዱ ያበረከቱትን ኪናዊ ፋይዳ መርምሯል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በጥናቱ ዳራ ላይ የቀረቡትን መረጃዎች ዋቢ በማድረግ በሰብእና ላይ የተካሔዱ ጥናቶችን ስንመለከት አብዛኛዎቹ ትኩረታቸው በሥነ ጽሑፍ ስራዎች ውስጥ በተለይ የዋና ገፀባህርያትን ሰብእና በማጥናት ላይ ብቻ የሚያተኩሩ በሚመስል ሁኔታ የሚገኙ ናቸው፡፡ ሌሎች ገፀባህርያትን ጨምሮ ሰብእና ላይ ትኩረት በማድረግ ለሥነ ጽሑፉ ያበረከቱትን ኪናዊ ፋይዳ፣ ገፀባህርያቱ ለሚያሳዩት የባሕርይ ምስቅልቅልነትም ይሁን የሰብእና መዛባት ወይም መቃወስ እንዲሁም መልካም ሰብእና መላበስ ምክንያት የሚሆኑ ውስጣዊም ይሁኑ ውጫዊ ምክንያቶችን ከስነ ጽሑፍ ስራዎች ውስጥ እየነቀሱ በማውጣት እና በመተርጎም ትንታኔ ሲሰጥባቸው አይስተዋልም፡፡

በአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ጥናት ታሪክ ላይ ምርምር ያደረጉት Taye እና Shiferaw (2000፣ 27) የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ጥናት ከሥነ ጽሑፍ አጀማመር ጋር ተመሳሳይነት እንዳለው ገልጸው አብዛኛዎቹ ጥናቶች ቅርጽን፣ ይዘትን፣ የአተራረክ ዘዴንና የመሳሰሉትን በመግለጽ ላይ የሚያተኩሩ እንደሆኑ ያስረዳሉ፡፡ ምንም እንኳ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከተለያዩ የእውቀት መስኮች ጋር በማዛመድና ትወራዎችን በማላመድ ትንታኔ ለመስጠት ሙከራዎች ቢኖሩም አጥጋቢ

ሊባል በሚችል ደረጃ ተሰርተዋል ብሎ በእርግጠኝነት ለመናገር ግን አያስደፍርም። ለምሳሌ ሥነ ልቦናን ከሥነ ጽሑፍ ጋር በማስተሳሰር ጥናት ሲደረግ ብዙም አይስተዋልም። በተለይ በአማርኛ ቋንቋ በሚሰሩ ጥናቶች ሥነ ልቦናዊ መርሆችን መገልገል ብዙም አልተለመደም።

የፍካሬ ልቦናን ንድፈ ሀሳብ ከሥነ ጽሑፍ ጋር በማስተሳሰር ሰብእናን እንደ ማደሪያና ማዕከላዊ ሀሳብ ማጠንጠኛ በማድረግ የተጠና የምርምር ስራ ለማግኘትም አዳጋች ነው። ይህ ጥናት እንዲካሔድ ምክንያት የሆነውም ይህ በመስኩ ላይ የሚስተዋለው ክፍተት ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚመነጨው ሌላው ምክንያት ደግሞ ሥነ ልቦናዊ ጉዳዮችን ከሥነ ጽሑፍ ጋር እንዴት ማቅረብ ይቻላል? በዘመኑ የሚታዩት ሥነ ልቦናዊ ጉዳዮች በምን መልኩ ቀርበዋል? የሚሉትን ጉዳዮች እና በምን አይነት ዘዴ ለሥነ ጽሑፍ ኪናዊ ፋይዳ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ? የሚለውን ለመመርመር ካለ ፍላጎት የተነሳ ነው። በመሆኑም በሀገራችን የሥነ ጽሁፍ ጥናት ላይ የሚስተዋለውን ክፍተት በመሙላት በኩል የበኩሉን አስተዋጽኦ ያበረክት ዘንድ የራሱን መሰረታዊ የምርምር ጥያቄዎች መሪ በማድረግ ተካሒዷል።

## 1.3. የምርምር ጥያቄዎች

ጥናቱ የሚከተሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎች መልሷል።

- *ሌላ ሰው* (2007) በተሰኘው የምህረት ደበበ ረጅም ልቦለድ ውስጥ ያሉ ገፀባህርያት ሰብእና እንዴት ቀርቧል?
- በ*ሌላ ሰው* ረጅም ልቦለድ ውስጥ የገፀባህርያት ሰብእና የተዋቀረበት ስልት ምንድን ነው?
- በ*ሌላ ሰው* ረጅም ልቦለድ ውስጥ ሰብእና የተዋቀረበት ስልት ለልቦለዱ ምን ኪናዊ ፋይዳ አበርክቷል?

## 1.4. የጥናቱ ዓላማዎች

ጥናቱ የሚከተሉትን ዐቢይና ንዑሳን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ተከናውኗል።

### 1.4.1. የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የገፀባህርያት ሰብእና በ*ሌላ ሰው* ረጅም ልቦለድ ውስጥ እንዴት እንደተዋቀረ መመርመር ነው።

### 1.4.2. የጥናቱ ንዑሳን ዓላማዎች

ጥናቱ የሚከተሉትን ንዑሳን ዓላማዎች መነሻ በማድረግ ተካሒዷል።

- *ሌላ ሰው* (2007) በተሰኘው የምህረት ደበበ ረጅም ልቦለድ ውስጥ ያሉ ገፀባህርያትን ሰብእና መፈከር፤
- በ*ሌላ ሰው* ረጅም ልቦለድ ውስጥ የገፀባህርያት ሰብእና የተዋቀረበትን ስልት መመርመር፤
- በ*ሌላ ሰው* ረጅም ልቦለድ ውስጥ ሰብእና የተዋቀረበት ስልት ለልቦለዱ ያበረከተውን ኪናዊ ፋይዳ መለየት፤ የሚሉት የዚህ ጥናት ንዑሳን ዓላማዎች ናቸው፡፡

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ ሰብእና በሌላ ሰው ረጅም ልቦለድ ውስጥ በምን መልኩ እንደተቀረጸና እንዴት ሊተረጎም እንደሚችል ለተደራስያን ፍንጭ ይሰጣል፤ ደራስያን ሰብእናንም ይሁን ሌሎች የሥነ ልቦና መሰረተ ሀሳቦችን የሀሳባቸው ማደሪያ በማድረግ በስራዎቻቸው ውስጥ እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ አቅጣጫ ሊጠቁም ይችላል፤ በመስኩ ላይ የሚታየውን ክፍተት በመሙላት የበኩሉን አስተዋጽኦ ሊያበረክት ይችላል፤ የደራሲውን ሰብእና ከስራው ጋር በማዛመድ እንዲሁም የሥነ ጽሑፍ ስራው በተደራስያን ላይ ሊፈጥር የሚችለውን የሰብእና ውቅር ማጥናት ለሚፈልግ ተመራማሪ እንደመነሻ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በተለያዩ ጊዜያት ከታተሙ የአማርኛ ረጅም ልቦለዶች መካከል ምህረት ደበበ በ2007 ዓ.ም *ሌላ ሰው* በሚል ርዕስ ባሳተሙት ረጅም ልቦለድ ላይ የተወሰነ ነው፡፡ ይህም የሆነው ሰፊ ርዕሰ ጉዳይን ይዞ ከዚህም ከዚያም ቁንጽል መረጃዎችን እየመዘዙ መቋረጫ የሌለው ሀሳብ ከማንሳት ይልቅ በአንድ የሥነ ጽሁፍ ስራ ላይ ተወስኖ ጥልቅ የሆነ ምርምር ማካሔድ የተሻለ ነው ተብሎ ስለታመነ ነው፡፡

ከርዕሰ ጉዳይ አንፃር የፍካሬ ልቦና ሒስ ከሚያተኩርባቸው መሠረታዊ ጉዳዮች (የደራሲው ሥነ ልቦናና የፈጠራ ሒደት፣ የገፀባህርያት ሥነ ልቦና እና የተደራስያን ሥነ ልቦና) መካከል በገፀባህርያት ሥነ ልቦና ላይ ብቻ ያተኮረ ነው፡፡ በዋናነትም ሰብእና በሚለው የሥነ ልቦና መሠረታዊ ሀሳብ ዙሪያ ያተኩራል፡፡ በመሆኑም ንቁ፣ ከፊል ንቁና ኢንቁ እንዲሁም ኢድ፣ ኢጎና ሱፐር ኢጎ የልቦና ሞዴሎች የጥናቱ ማጠንጠኛ ሆነዋል፡፡ የደራሰውን ሰብእና ከሥነ ጽሑፉ ጋር በማያያዝ ማጥናት እንዲሁም የሥነ ጽሑፍ ስራው በተደራስያን ላይ ሊፈጥር የሚችለውን የሰብእና ሁኔታ መመርመር የዚህ ጥናት የትኩረት አቅጣጫዎች አይደሉም፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምዕራፍ ስር ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውና መረጃዎችን ለመተንተን የሚያስችሉ ንድፈ ሀሳቦች፣ መረጃዎችን ለመቀንበብ የሚያስችለው ትወራዊ ማህቀፍ እና ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ቀደምት ጥናቶች ቀርበዋል፡፡

## 2.1. የንድፈ ሀሳባዊ ጽሑፍ ክለሳ

በዚህ ርዕስ ስር ከሰብእና ጋር የተያያዙና ለጥናቱ ንድፈ ሀሳባዊ ማህቀፍም ይሁን ትንተና ያግዛሉ ተብለው የታመነባቸው የተለያዩ ጽንሰ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

### 2.1.1. የሰብእና[2] ምንነት

ኪዳነወልድ (1948፣ 843) የሰብእናን ምንነት ሲገልጹ ‹‹ሰውነት፤ ሰው፡መኾን፤ የሰው፡ባሕርይ፤ አካሉ፡ ገላው፤ ኹለንተናው፤ ኹለመናው፡፡›› ይሉታል፡፡ በመሆኑም ሰብእና አንድ ግለሰብ ከሌላ ግለሰብ ተለይቶ የሚታወቅበት ባሕርይ፣ ፀባይ፣ ድርጊት ወይም እንቅስቃሴ ሆኖ በተለያዩ ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎች በጊዜ ሒደት በሕይወት ዘመን ሊገነባ የሚችልና በተለያዩ ሁኔታዎች ሊንጸፀባረቅ የሚችል የሰው ልጅ መለያ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ሰብእና በሀይማኖት ጠበብት፣ በፈላስፋዎች፣ በማበረሰብ አጥኚዎችና በስነ ልቦና ባለሙያዎች የተለያየ ብያኔ እንደሚሰጠው የሚገልጹት Hampson (1988፣1) በአብዛኛው በሥነ ልቦና ምሁራን ዘንድ ተቀባይነትን ያገኘው ብያኔ ሰብእና በአንጻራዊነት ቋሚ የሆነ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ የማይለዋወጥ፣ ቀጣይነት ያለው የአንድ ሰው ውስጣዊና ግላዊ ባሕርይ ሆኖ ከሌሎች ሰዎች ባሕርይ ጋር ሲነጻፀር ልዩነት የሚታይበት ነው የሚለው እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ በዚህ ብያኔ ውስጥ ቋሚነት፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ የማይለዋወጥ፣ ውስጣዊ እና ግላዊ ልዩነት የሚሉት ጽንሰ ሀሳቦች በተለያዩ መስኮች በተለያዩ ጊዜያት ለሚሰጡ የሰብእና ብያኔዎች የጋራ ማጠንጠኛ በመሆን እንደሚያገለግሉም ያስረዳሉ፡፡ ቋሚና ቀጣይነት ያለው የሚሉት ጽንሰ ሀሳቦችም የግድ መሆን አለባቸው ወደሚል ማጠቃለያ የሚያደርሱ ሳይሆኑ በአንፃራዊነት በሚቻልበት አጋጣሚ ሊገኙ ይችላሉ የሚል አቋማቸውን ያንፀባርቃሉ፡፡ ውስጣዊ እና ግላዊነት የሚሉት መሠረተ

[2] ሰብእና (Personality) ፐርሶና (Persona) ከሚለው የላቲን ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም ጭንብል (Mask) ማለት ነው፡፡ ይኸውም ቀደም ሲል የግሪክ ተዋንያን ድራማ በሚሰሩበት ወቅት ራሳቸውን በተለያዩ ነገሮች ሸፍነው በመቅረብ የተለያየ መልክ ለመጎናጸፍ ይጠቀሙበት ነበር፡፡ ሰብእና ድብቅና በቀላሉ ሊታወቅ የማይችል መሆኑ ከጭንብል ጋር ስለሚያመሳስለው ‹‹Personality›› የሚለውን መጠሪያ ሊያገኝ ችሏል፡፡

ሀሳቦችም ቢሆኑ የሚቻልበት አጋጣሚ እንዳለ ይጠቁሙ እንደሁ እንጂ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ የሚገለጹ አይደሉም። ምክንያቱም ሰብእና የተፈጥሯዊ ወይም ውስጣዊ ጣጣ ብቻ ሳይሆን የአካባቢያዊ እና/ወይም ባህላዊ ጉዳዮችም ድምር ውጤት ነው።

በተመሳሳይ መልኩ McAdams (2007፣ 4) በሰብእና ጥናት በጉልህ የሚታወቁትን Allport (1937)ን በመጥቀስ ሰብእና ከ49 በላይ ብያኔዎች በየጊዜው እንደተሰጡት ያስረዳሉ። በMcAdams (1997፣ 4) እንደተገለጸው የሰብእና ጥናትን ከሰብአዊነት ሥነ ልቦና አንፃር ፈር እንዳስያዘና ተጽእኖውን እንዳሳረፈ የሚታወቀው Allport ሰብእና በእያንዳንዱ ግለሰብ ውስጥ ያለ የልቦናዊና አካላዊ ስርዓት ተለዋዋጭ ቅንጅት ሆኖ ግለሰቡ ከአካባቢው ጋር የሚኖረውን መስተጋብር ልዩ በሆነ መንገድ ለማስተካከልና ለማወቅ የሚያስችል ነው ብለው ያብራራሉ። ይኸው ብያኔ በ1961 ላይ የተወሰነ የቃላት ማሻሻያ በራሱ በጸሐፊው ከተደረገበት በኋላ እስካሁን ድረስ በማገልገል ላይ እንደሚገኝም ያስገነዝባሉ። በመሆኑም ሰብእና የሞራል፣ የሥነ ልቦናና የሥነ ምግባር ጣጣ ያለበት የአንድ ግለሰብ ባሕርይ ወይም ጸባይ ሆኖ በቤተሰብ (በቤተሰብ ሲባል በዘር ሀረግ የሚተላለፍ የሚለውንም ያመለክታል።) በጎረቤት በአካባቢ ብሎም በሀገር ደረጃ ባሉና በአምስቱ የስሜት ህዋሳት ሊቀሰሙ በሚችሉ ሁኔታዎች ሊቀረጽና ሊገነባ የሚችል ነው ማለት ይቻላል። Bienvenu (2011፣ 234) እንደሚገልጹት ደግሞ ሰብእና አንድ ሰው በህይወት ዘመኑ በሚቆይበት አውድ ውስጥ የሚገኝ  የስሜት፣ የአስተሳሰብና የባሕርይ ድምር ውጤት ነው። በመሆኑም የሰው ልጅ ሰው ካልሆኑ ፍጥረታት ሁሉ የሚለይበት አንዱ ጉዳይ ነው ማለት ይቻላል። Lawrie (1974፣ 307) ሰብእና ከእንስሳነት፣ ከቁሳቁስነት ወይም ከግዑዝነት የመለየት ሁኔታ ነው፤ በመሆኑም ሁሉም ሰው የራሱ ሰብእና አለው በማለት ይገልጻሉ። ይኸውም የሰው ልጅ ሰው ለመባል ሰብእና ሊኖረው እንደሚገባና ሰብእናው ግን በተለያዩ ሁኔታዎች ምክንያት ተዛንቆ ሊንፀባረቅ እንደሚችል የሚያመለክት ሀሳብ ነው።

ሰብእና በውስጣዊም ሆነ ውጫዊ ምክንያቶች እንዴት ሊዋቀር እንደሚችል ሳይንሳዊ ጥናቶች ሲደረጉ ይስተዋላሉ። በዚህም በፈር ቀዳጅነት የሚታወቀው Sigmund Freud (1856-1939) ሲሆን ሰብእና የንቁ፣ ከፊል ንቁና ኢንቁ በኋላ ላይ ደግሞ የኢድ፣ ኢጎ እና ሱፐር ኢጎ ቅንጅት ወይም ድምር ውጤት እንደሆነ ያስረዳሉ። ለዚህ ጥናትም በንድፈ ሀሳባዊ ማጠንጠኛነት ጥቅም ላይ የሚውሉ በመሆናቸው እያንዳንዳቸው በሚቀጥለው ርዕስ ስር ተብራርተው ቀርበዋል።

### 2.1.2. የሰብእና መዋቅር (Personality Structure)

የሰብእና መዋቅር አንድ ግለሰብ የሚያሳየው ባሕርይ ወይም ጠባይ ሊዳብርና ሊበለጽግ የቻለበት ሒደት ነው። ሰዎች ለያዙት ሰብእና መሠረት ሊሆኑ የሚችሉ ውስጣዊም ሆኑ ውጫዊ ጉዳዮችን የሚመለከት ጽንሰ ሐሳብም ነው። ይህን በሚመለከት Freud (1856-1939) ሶስት የሰብእና መዋቅሮችን በተለያዩ ጊዜያት ያስተዋወቁ ሲሆን በመጀመሪያ ያስተዋወቋቸውን ኑባሬያዊ[3] ሞዴል (Topographic Model) በማለት ሲጠሯቸው በኋላ ደግሞ ተያያዥነት ያላቸውና ለእነዚህ አጋዥ የሆኑትን የሰብእና ክፍሎች መዋቅራዊ ሞዴል (Structural Model) በሚል አስተዋውቀዋል (Jess እና Gregory፣ 2005፣ 27)። ቀጥሎ የቀረቡት ርዕሶችም እነዚህን ሁለት ሞዴሎች በሰፊው የሚያብራሩ ናቸው።

#### 2.1.2.1. ኑባሬያዊ የልቦና ሞዴል (Topographic Model of the Psyche)

#### ሀ. ኢንቁ (Unconscious)

ኢንቁ ማስታወስ የማንፈልጋቸው የህይወት ጠባሳዎች ታጭቀው ወይም ታግተው የሚኖሩበት የአእምሮ ክፍል ነው። ኢንቁ ከእውቅናችን ውጭ የሆኑ፣ የሚያነሳሱና አንድን ድርጊት እንድንፈጽም የሚገፋፉንን ደመነፍሳዊ ኃይሎች የሚመለከት ነው (Jess እና Gregory፣ 2005፣ 24)። ለምንናገራቸው ቃላት፣ ለምናፈልቃቸው ሀሳቦችና ለምናከናውናቸው ተግባራት እንደ ቀስቃሽ ወይም አነሳሽ በመሆን ሊያገለግል እንደሚችልም ያስረዳሉ። ኢንቁ የሚገለጠው በህልም፣ በምላስ አድጥ/ወለምታና ረስተን ወይም ሆን ብለኝ በአእምሯችን ውስጥ አምቀን ከያዝናቸው ስሜቶች ጀርባ ፍች ወይም ትርጓሜ ስንፈልግ እንደሆነ ያስገነዝቡናል። ኢንቁ በሒደት፣ በድብቅና በመዛባት ከፍተኛ የሆነ የሳንሱር ስራ ተደርጎበት ወደ ንቁ ሊያልፍ ይችላል። ወደ ንቁ ከደረሰ በኋላ በድብቅ ይቆይና በተለያዩ ምክንያቶች ለመውጣት መንገድ ይፈልጋል። ይህ ዑደትም ቅድመ ንቁ ወይመ ከፊል ንቁ ተብሎ ይጠራል።

ኢንቁ የአእምሮ ክፍል ፍካሬ ልቦና በስፋት የሚጠቀምበትና በትኩረት የሚመለከተው የአእምሮ ክፍል እንደሆነ የሚገልጹት Burger (2010፣ 43) በአእምሯችን ወዲያውኑ የማንጠቀምባቸው ነገር ግን በአንዳንድ ጫፍ የወጡ አሳሳቢ ምክንያቶች ወደ ንቁው የአእምሮ ክፍል እንዲመጡ በማድረግ የምንጠቀምባቸው መረጃዎች የሚቀመጡበት ክፍል እንደሆነ ያስረዳሉ። ሆኖም

---

[3] ኑባሬ የሚለው ቃል ‹‹ነበረ›› ተቀመጠ ከሚለው የግዕዝ ቃል በጽሑፉ ውስጥ የገባበትን አውዳዊ ፍች እንዲይዝና ‹‹Topography›› የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል በአቻነት እንዲተካ ጥቅም ላይ የዋለ ነው። ለያዘው አውዳዊ ፍች ምቹ እንዲሆንም ‹‹-ኣዊ›› የሚል ቅጥያ ተጨምሮበት የወገን አመልካች ቅጽልነት ሚና እንዲኖረው ተደርጓል።

በየቀኑ ለምናሳያቸው ባሕርያት ተገዥ እንደሆኑ ያስገነዝባሉ፡፡ ኢንቁው የአእምሮ ክፍል የሚያሳድረው ተጽእኖም የባሕርይ መዛባት በሰዎች ላይ እንዲከሰት ያደርጋል የሚለው ጽንሰ ሀሳብ የፍካሬ ልቦና አንዓር ማጠንጠኛ እንደሆነ ያብራራሉ፡፡ ኢንቁ ሁልጊዜም ንቁ መሆን አይፈልግም ማለት አይደለም፡፡ ኢንቁ የሆኑ ቀስቃሽ ኃይሎች ምንጊዜም ቢሆን ንቁ ለመሆን በቋሚነት ጥረት ያደርጋሉ፡፡ አንዳንዶችም ይሳካላቸውና ንቁ ሆነው ይገለጻሉ፡፡

### ለ. ቅድመ ወይም ከፊል ንቁ (Preconscious)

ቅድመ ንቁ የምንለው የአእምሮ ደረጃ በኢንቁና በንቁ መካከል ያለ ሲሆን ኢንቁ ስሜቶች ንቁ ለመሆን ተዘጋጅተው የሚጠብቁበት ደረጃ ነው፡፡ በንቁና ኢንቁ መካከል ስለሚገኝ ከፊል ንቁ ተብሎም ይጠራል፡፡ Jess እና Gregory (2005፣ 25) እንደሚገልጹት ቅድመ ንቁ የአእምሮ ደረጃ ሁሉንም ንቁ ያልሆኑትን ግን ንቁ ለመሆን የሚችሉትንና በዝግጅት ላይ ወይም በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ያሉ ስሜቶችን የሚመለከት ነው፡፡ እነዚህ ስሜቶች ጊዜ ጠብቀው በተለያዩ ዘዴዎች አማካኝነት ወደ ንቁነት ደረጃ ይሸጋገራሉ፡፡ በአንደኛው የማለዘቢያ ዘዴ ሲደናቀፉ ሌሎችን እያማተሩ ይጠብቁና ድንገት ይከሰታሉ፡፡ ቅድመ ንቁ የአእምሮ ክፍል በአእምሯችን ውስጥ ተደራጅተው የተቀመጡና ማስታወስ ስንፈልግ ወደ ንቁው የአእምሮ ክፍል የሚሸጋገሩ መረጃዎችን የሚይዝ ነው (Burger፣ 2010፣ 43)፡፡

የቅድመ ንቁ ይዘት ንቁና ኢንቁ ከሚሉት ከሁለት ምንጮች የሚፈልቅ ነው፡፡ ንቁ ከሆነው የሚፈልቀው በህይወት ዑደት ውስጥ በምናደርገው የትኩረትና የመቀበል ወይም የመረዳት መለዋወጥ አማካኝነት የሚከሰት ነው፡፡ ኢንቁ ከሆነው የሚመነጨው ደግሞ ታፍነው፣ ተጨቁነውና ታምቀው የኖሩት ስሜቶች መውጫ ቀዳዳ እየፈለጉ ለመውጣት በሚያደርጉት ትግል ነው፡፡ በመሆኑም በህልም፣ በምላስ አድጥ/ወለምታ፣ በቀልድ እና በተለያዩ ሥነ ልቦናዊ የጭንቀት መከላከያ ዘዴዎች አማካኝነት ይወጣሉ (Jess እና Gregory፣ 2005፣ 25)፡፡

### ሐ. ንቁ (conscious)

ንቁ የምንለው የአእምሮ ክፍል ወይም ደረጃ ዘወትራዊና የተለመደ ነው፡፡ በአእምሯችን የምናውቀውና የተለመደ ሲሆን በፍካሬ ልቦና ትወራ ብዙም ሚና የለውም (Jess እና Gregory፣ 2005፣ 25-26)፡፡ አእምሯችን በቀጥታ የሚጠቀምበት ወይም በስራ ላይ የሚያውለው ደረጃ እንደሆነም ያስረዳሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ Burger (2010፣ 43) ንቁው የአእምሯችን ክፍል ወዲያውኑ በስራ ላይ የምናውላቸውንና የምንጠቀምባቸውን ሀሳቦች እንደሚያካትት ይገልጻሉ፡፡ በንቁው የአእምሮ ክፍል የሚገኘው ሀሳብም ሌላ አዲስ ሀሳብ

በሚመጣበት ጊዜ ቦታውን ይለቅና ከእውቅና ውጭ እንደሚሆን ያስረዳሉ፡፡ በንቁው የአእምሮ ክፍል የሚገኘው መረጃ በአጠቃላይ በአእምሯችን ከሚገኘው መረጃ በጣም ጥቂት ፐርሰንት የሚሸፍን እንደሆነ ያስገነዝባሉ፡፡ ሀሳብ በሁለት ሒደቶች ወደ ንቁ አእምሮ ክፍል ከሁለት አቅጣጫዎች የሚመጣ ሲሆን አንደኛው ባለን የመረዳትና የመገንዘብ ችሎታ የሚከሰት የንቁነት ስልት ነው፡፡ ይህም በስሜት ህዋሳታችን ውጫዊ ንቁነት ወይም ቀስቃሽነት የሚፈጠር ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ከአእምሯችን ውስጣዊ አወቃቀር የሚመነጭ ነው፡፡ ይኸውም በቅድመ ንቁ ክፍል መፍትሔ ያላገኙ ጉዳዮች እና በኢንቁው በአግባቡ ያልተደበቁት ጉዳዮች የሚገለጹበት ነው፡፡

Freud በኑባሬያዊ (Topographic Model) ሲጠቀም ከቆየ በኋላ በ1920 ላይ መዋቅራዊ ሞዴልን (Structural Model) እንዳስተዋወቀ Jess እና Gregory (2005፣ 27) ይገልጻሉ፡፡ መዋቅራዊ ሞዴልም በኑባሬያዊ ሞዴል የተተካ ሳይሆን እንደአጋዥ እንዲያገለግል ታስቦ እንደተቀመረ ያስረዳሉ፡፡ በመሆኑም ኢድ ሙሉ በሙሉ ኢንቁ ሲሆን ኢጎ ደግሞ ኢንቁና ቅድመንቁ እንደሆነ ያስገነዝባሉ፡፡

### 2.1.2.2. መዋቅራዊ የልቦና ሞዴል (Structural Model of the Psyche)

Freud ከኑባሬያዊ ሞዴል በኋላ ያስተዋወቀው መዋቅራዊ ሞዴል ኢድ፣ ኢጎ እና ሱፐር ኢጎን በውስጡ የሚይዝ ነው፡፡ እነዚህ የሰብእና መዋቅሮች እርስበርሳቸው በእጅጉ የተቆራኙ ስርዓት ሆነው ሰብእናን ለመገንባት ወይም ለማዋቀር የሚያገለግሉ ጡቦች እንደሆኑ Hampson (1988፣ 6) ይገልጻሉ፡፡ እነዚህ መዋቅራዊ ንድፎች ልቡናዊ ኃይልን (Psyche Power) ለመቆጣጠር እርስ በእርሳቸው ፉክክር ውስጥ የሚገቡ እንደሆኑም ያስረዳሉ፡፡ በዚህ ፉክክርም ሰብእና ይገነባል፡፡

#### ሀ. ኢድ (Id)

ኢድ ደመነፍሳዊ፣ ኢሥነ ምግባራዊ፣ ኢሞራላዊና ኢምክንያታዊ የሆኑ ተግባራትን ለማከናወን የሚገፋፋ ግብታዊ የሆነ የሰብእና ውቅር ነው፡፡ ኢድ በማህበራዊ ስምምነት ወይም ልምድ የተጠሉና የተወገዙ ፍላጎቶችንና ምኞቶችን የሚይዝ እንደሆነ Tyson (2006፣25) ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም በአእምሮ ውስጥ ብልጭ የሚልን ማንኛውም ሀሳብ እንደወረደ ከመተግበር አይመለስም፡፡ ለማህበራዊ ስሪትና ለባህላዊ እሴቶች አይጨነቅም፡፡ ውስጣዊ ስሜት ያዘዘውን መፈጸምና ፍላጎትን ማርካት መገለጫዎቹ ናቸው፡፡ ለውጫዊ ተጽእኖ ደንታ የለውም፤ ውስጥን

በማዳመጥ ፍላጎትን ለማሳካት ጥረት ማድረግም መለያው ነው (Jess እና Gregory፣ 2005፣ 25)።

ኢድ በጣም ራስ ወዳድነት የሚታይበት፣ ግላዊ ፍላጎትን ለማሟላት ብቻ ጥረት የሚያደርግ፣ ያለምንም አካላዊና ባህላዊ ውስንነት ጊዜያዊ ደስታን ለመፍጠር የሚተጋ የሰብእና ውቅር ነው (Burger 2010፣ 43-44)። ህጻናት ወዲያውኑ እንደተወለዱ የሚኖራቸው የሰብእና ውቅር እንደሆነ የሚያስረዱት Burger ለምሳሌ ህፃናት የሆነ ነገር ሲያዩ ምንም እንኳ ለማግኘት አዳጋች እንዲሁም አደገኛ ቢሆን ለማግኘት ጥረት ከማድረግ እንደማይመለሱ ያስገነዝባሉ። ይህ ቅጽበታዊ ድርጊት በጉልምስና ጊዜም እንደማይጠፋ ያብራራሉ። ኢድ በባህል ተጽእኖ ምክንያት ኢንቁ በሆነው የአእምሮ ክፍል ታግተውና ተጨቁነው የሚገኙ ፍላጎቶችና ምኞቶች መተንፈሻ ነው። ተፈጥሯዊ የሆኑ ፍላጎቶች በእጅጉ የሚተገበሩበትና ምላሽ የሚያገኙበትም ነው።

ኢድ የሰብእና መሠረታዊ ጉዳይ፣ ሙሉ በሙሉ ኢንቁ፣ ከነባራዊው እውነታ ጋር ግንኙነት የሌለው ሆኖም መሠረታዊ ፍላጎትን በግብታዊነት በማሟላት ጭንቀትን ለመቀነስ የሚያገለግል መዋቅር እንደሆነ Jess እና Gregory (2005፣ 27) ያስረዳሉ። ለዚህም ምክንያቱ ዋናውና ብቸኛው ተግባሩ ደስታን መፈለግ ወይም መፍጠር መሆኑ ነው። አዲስ የተወለዱ ህፃናት የሚያዳብሩት ወይም የሚኖራቸው የሰብእና መዋቅር በኢጎና በሱፐር ኢጎ ማዕቀብ ያልተጣለበት ኢድ እንደሆነ ያስገነዝባሉ። ህፃናት ይቻላል አይቻልም፣ የተፈቀደ ነው የተከለከለ፣ ጥሩ ነው መጥፎ የሚባል ነገር ስለማያስጨንቃቸው ምኞታቸውና ፍላጎታቸው ሁሉ እንዲሳካላቸው ይፈልጋሉ።

ኢድ ኢምክንያታዊና ኢሞራላዊ ብሎም ከሥነ ምግባራዊው እውነታ ወጣ ያሉ የሰብእና ጣጣዎችን ስለሚያስተናግድ ፍላጎትን ወይም ምኞትን እስካረኩ እና ደስታን እስከፈጠሩ ድረስ አእምሮ በተለያዩ የሚጣረሱና እርስ በርስ በሚቃረኑ ሀሳቦች ሊታጨቅ ይችላል Jess እና Gregory (2005፣ 28)። ለምሳሌ አንዲት ሴት ንቁ በሆነ መንገድ እናቷን አጥብቃ ልትወድ ትችላለች፤ ሆኖም ኢንቁ በሆነ መንገድ ደግሞ እናቷን የማጥፋት ፍላጎት ሊኖራት ይችላል። ይህ እርስ በእርስ የሚጣረስ ሀሳብ በኢድ ሰብእና የተለመደ ነው። ምክንያቱም ኢድ ከሞራል፣ ከባህላዊ እሴት ወይም መጥፎና ጥሩ ከሚባሉ መመዘኛዎች ነጻ ነውና። በጥቅሉ ኢድ ከመጀመሪያዎቹ የልጅነት እድሜ የሚጀምር፣ ምስቅልቅል፣ ለንቁው የማይገዛ፣ ኢሞራላዊ፣ ኢምክንያታዊ፣ ያልተደራጀ በመሠረታዊ ፍላጎት የሚገፋ ወይም የሚመራና ደስተኛነትን ለመፍጠር ብቻ የሚያገለግል ነው።

### ለ. ኢጎ (Ego)

ኢጎ ሚዛናዊ የሆነ፣ በምክንያታዊነት የሚያምን፣ ከውስጣዊ ጉዳዮች ይልቅ ለውጫዊ ጉዳዮች የሚጨነቅ ነው። የኢድን ጽንፍ የረገጠ ግብታዊነት እና የሱፐር ኢጎን ጫፍ የወጣ ሞራላዊነት (የባህታዊነት ባሕርይ) ለማመጣጠን በዳኝነት እንደሚያገለግል Tyson (2006፣25) ይገልጻሉ። ስለሆነም ማህበረሰቡ የሚመራበትን ባህላዊ እሴት ለማክበርና ማህበራዊ ስሪቱ በሚሔድበት መንገድ ለመጓዝ ጥረት ያደርጋል። ለሚፈጸሙ ነገሮች ሁሉ ምክንያት መፈለግ መለያ ባህርይው ነው። የኢድን ፍላጎት ለማሟላት ከማህበራዊ ስሪቱና ባህላዊ አውዱ የሚያመልጥበትን ስልት ወይም የመከላከያ ዘዴ (Defense Mechanism) በማመቻቸት ፍላጎቱ እንዲሟላ መንገድ ይከፍታል። ምክንያት በመደርደር የሱፐር ኢጎንና የኢድን ፍላጎት ለማሟላት ጥረት ያደርጋል።

ህፃናት ከአካባቢያቸው ጋር መስተጋብር ሲጀምሩ በሁለተኛው ዓመት መጀመሪያ ላይ ሁለተኛውን የሰብእና መዋቅር ወይም ኢጎን በሒደት ይገነባሉ (Burger፣ 2010፣ 44)። ኢጎ በነባራዊውና በእውነታው ዓለም መመሪያ የሚመራ እንደሆነና የእውነታውን ዓለም ከግምት ውስጥ በማስገባት የኢድን ፍላጎት ማሟላት ተቀዳሚ ተግባሩ እንደሆነም ያስረዳሉ። አብዛኛው የኢድ ፍላጎት ማህበራዊ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑም ኢጎ ኢንቂ ወደሆነው የአእምሮ መዋቅር በመላክና የተለያዩ ስነ ልቦናዊ የጭንቀት መከላከያ ስልቶችን በመጠቀም የኢድን ፍላጎት እንደሚያሟላ ያስገነዝባሉ።

ኢጎ ብቸኛውና ከነባራዊው ዓለም ጋር ግንኙነት ያለው የሰብእና መዋቅር ነው (Jess እና Gregory፣ 2005፣ 29)። በእውነታው ዓለም መመሪያዎች የሚመራና ከውጨኛው ዓለም ጋር ተግባቦትን ለመፍጠር ጥረት የሚያደርግ የሰብእና መዋቅር እንደሆነም ያስረዳሉ። ኢጎ ውሳኔ የሚያስተላልፍ የሰብእና ክፍል ነው። ምክንያቱም በከፊል ንቁ፣ በከፊል ቅድመ ንቁና በከፊል ኢንቁ ስለሆነ ነው።

### ሐ. ሱፐር ኢጎ (Super Ego)

ሱፐር ኢጎ ሲበዛ ሞራላዊና ሥነ ምግባራዊ ከመሆኑ የተነሳ የባህታዊነት ባሕርይ እንዲከሰት የሚያደርግ ነው። Tyson (2006፣25) ሱፐር ኢጎ የኢድ ተቃራኒ እንደሆነ ይገልጻሉ። ለዚህም ምክንያቱ ሱፐር ኢጎ ለማህበራዊ ስሪትና ባህላዊ እሴቶች አጥብቆ የሚጨነቅ፣ ከራስ ይልቅ ለሌሎች መኖርን የሚደግፍ፣ በስሜት ሳይሆን በሞራል ልዕልና የሚመራ መሆኑ ነው።

በአንጻሩ ኢድ ውስጣዊ የግል ፍላጎትን ለማሟላትና ስሜትን ለማርካት ጥረት የሚያደርግና ግለኝነት የሚያይልበት ነው፡፡

ህፃናት በተወለዱ በአምስተኛው ዓመታቸው ሱፐር ኢጎ ተብሎ የሚታወቀውን ሶስተኛውን የሰብእና መዋቅር የሚያዳብሩ ሲሆን በሰፊው የማህበረሰቡንና በጠባቡ ደግሞ የቤተሰባቸውን እሴቶችና መመሪያዎች ለመወከል ጥረት ያደርጋሉ (Burger፣ 2010፣ 44)፡፡ ሱፐር ኢጎ መደረግ ያለበትንና የሌለበትን ከማህበራዊ እሴት አንጻር እየገመገመ ገደብ የሚያስቀምጥ የሰብእና መዋቅር እንደሆነም ያስረዳሉ፡፡

ሱፐር ኢጎ ሞራላዊ እና ህሊናዊ የሆኑ የሰብእና ጉዳዮችን የሚመለከት ሆኖ በሞራላዊና ህሊናዊ መርሆች የተገነባ ነው፡፡ ከእውነታው የሚያፈነግጡ ሁኔታዎችን ለማስተካከል ጥረት ያደርጋል፡፡ በአግባቡ የዳበረ ሱፐር ኢጎ ወሲባዊና ጭካኔ የተሞላባቸውን ድርጊቶች ለመፈጸም የሚያነሳሱ ስሜቶችን በመጨቆን ለመቆጣጠር ጥረት ያደርጋል (Jess እና Gregory፣ 2005፣ 30)፡፡ የመጨቆን ስራው የሚከናወነው በራሱ ሳይሆን ኢጎን እንዲፈጽመው በማስገደድ ነው፡፡ ኢጎ የሱፐር ኢጎን ሞራላዊ መርህ ካልጠበቀና ጥፋት ከተፈጸመ የጥፋተኝነት ስሜት ይዳብራል፡፡ ኢጎ የሱፐር ኢጎን ማስተካከያ ካልተቀበለና ካላስተካከለ የበታችነት ስሜት ይፈጥራል፡፡

እስካሁን የቀረቡት የሰብእና መዋቅሮች አለመመጣጠን ወይም በቅንጅት አለመስራት፣ እንዲሁም የተለያዩ ውጫዊና ውስጣዊ ሁኔታዎች በሰብእና ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራሉ፡፡ ይህም የሰብእና መዛባትን ያስከትላል፡፡

### 2.1.3. የሰብእና መዛባት (Personality Disorder)

የሰብእና መዛባት ከሰው ልጅ የተለመደና ዘወትራዊ ባሕርይ የተለየ ባሕርይ ማሳየትን የሚመለከት ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የሰው ልጅ በተለያዩ ውስጣዊም ሆኑ ውጫዊ ምክንያቶች ችግር ሲያጋጥመው ከመደበኛ ሰብእናው የሚያፈነግጥበትን ሒደት የሚመለከት ነው፡፡ የሰብእና መዛባት ጽኑ የሆነ፣ ቋሚነት ያለው፣ ያልተለመደ፣ አሉታዊ ወይም ጤናማ ያልሆነ ማህበራዊ ግንኙነትን የሚመለከት እንደሆነ Gask፣ Evans  እና Kessler (2013፣ 28) ይገልጻሉ፡፡ የሰብእና መዛባት ከአእምሮ ህመም እንደሚለይም ያስረዳሉ፡፡ ምክንያቱም የሰብእና መዛባት በሰው ልጅ የዕድገት ደረጃዎች ከአካባቢው በሚገጥመው ተጋልጦ በየጊዜው እየዳበረ የሚሔድና ቋሚነት የሚታይበት ሲሆን የአእምሮ ህመም ግን በህይወት ዑደት ውስጥ

በአንድ አጋጣሚ ሊፈጠር የሚችል ነው፡፡ የሰብእና መዛባት ያለባቸው ሰዎች አብዝተው ይጨነቃሉ፤ ይሰቃያሉ፤ ይገለላሉ፤ በአካባቢያቸው ላይም ጭንቀትን ይፈጥራሉ፡፡ ጭንቀትና ድባቴ ሲበዛም ራስን የማጥፋት ሀሳብ እንዲፀነስ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ በተግባር የሚፈጸምበት ጊዜም ይኖራል፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ ከተቀመጡት ባህላዊ እሴቶች ጋር የመጋጨትን ሁኔታም ይከሰታል፡፡ ለሰብእና መዛባት ችግር ተጋላጭ የሆኑ አካላት ሁልጊዜ በጭንቀትና በድባቴ የማሳለፍና የመኖር አጋጣሚያቸው ሰፊ ነው፡፡

የሰብእና መዛባት ከዝርያ ጋር እና ከአካባቢያዊ ሁኔታዎች ጋር በሚያያዙ የተለያዩ ምክንያቶች ይከሰታል (Gask et al. 2013፣ 29)፡፡ የልጅነት ጊዜ ልምድና ቤተሰብ በሰብእና መዛባት ላይ ከፍተኛ የሆነ ተጽእኖ እንደሚያሳድሩም ያስረዳሉ፡፡ የሰብእና መዛባት በተለያዩ ሥነ ሕይወታዊ ወይም አካላዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮች ይፈጠራል፡፡ ሥነ ህይወታዊው በዘር ከቤተሰብ ሊወረስ ሲችል ማህበራዊው ደግሞ ከአካባቢና ከቤተሰብ ጋር በሚኖር ግንኙነት መልካም ካልሆኑ ምልከታዎችና ድርጊቶች ይከሰታል፡፡

የሰብእና መዛባት የተለያየ አይነት እንዳለው የሚገልጹት Parnas፣ Licht እና Bovet (2005፣ 1) ዋናዋናዎቹና በአብዛኛው የዓለም ክፍል በሰዎች ላይ ሲደርሱ የሚታዩትን ምድብ ‹‹ሀ›› (Cluster ‹‹A››)፣ ምድብ ‹‹ለ›› (Cluster ‹‹B››) እና ምድብ ‹‹ሐ›› (Cluster ‹‹C››) በሚል ከፋፍሎ መመልከት እንደሚቻል ያስረዳሉ፡፡

### 2.1.3.1. ምድብ ‹‹ሀ›› የሰብእና መዛባት (Cluster ‹‹A›› Personality Disorder)

ይህን የሰብእና መዛባት ምድብ የሚፈጥሩት ከውጭው ዓለም ሸሽተው በራሳቸው ዓለም የሚኖሩ (Schizoid Personality Disorder)፣ ከመጠን ያለፈ ሰዎችን ያለማመን ችግር ያለባቸው (Paranoid Personality Disorder) እና በአነጋገራቸው፣ በባሕርያቸው በአስተሳሰባቸው ላይ መዛባት ያለባቸው (Schizotypal Personality Disorder) በጋራ በመዋቀር ነው፡፡

#### ፩. ከውጭው ዓለም ሸሽተው በራሳቸው ዓለም የሚኖሩ (Schizoid Personality Disorder)

የዚህ ዓይነት የሰብእና መዛባት ያለባቸው ሰዎች በራሳቸው ዓለም አብዝተው የሚመሰጡ፣ ተጨባጭ ያልሆኑና በእውኑ ዓለም ሊደረስባቸው የማይችሉ ሀሳቦችን የሚያልሙ፣ ለማህበራዊ ህጎችና ደንቦች የማይጨነቁ እና ከሰዎች ጋር ስሜታዊ ትስስር ለመፍጠር የማይፈልጉ ናቸው፡፡ ከማህበራዊ ግንኙነት ተነጥለው መኖር ያዘወትራሉ (Barlow እና Durand፣2015፣ 448-49)፡፡

ለቤተሰብ አባል እንኳ ቢሆን ደስታቸውንም ይሁን ፍላጎታቸውን መግለጽ አይፈልጉም፤ ለውጭው አካል ሁሉ ዝግ ናቸው፡፡ ሁልጊዜም ሊባል በሚችል ደረጃ ብቸኝነትን ይመርጣሉ፡፡ ብዙ ተግባራትን አከናውነው ጥቂት ደስታን ያገኛሉ፡፡ የመጀመሪያ ከሚሏቸው የቅርብ ዘመዶቻቸው ውጭ የቅርብ ጓደኛ ወይም የምስጢር ተካፋይ የላቸውም፡፡ በሌሎች ሰዎች ላይ ለሚሰጥ ምስጋናም ይሁን ትችት ወይም ነቀፋ ብቅ የሚሉት በግዴለሽነት ነው፡፡ ስሜተ ቀዝቃዛ ናቸው፤ (ስሜታዊነት አይታይባቸውም) (Parnas et al.፣ 2005፣ 1፣ 55 እና 56)፡፡

## ፪. ከመጠን ያለፈ ሰዎችን ያለማመን ችግር (Paranoid Personality Disorder)

ይህ የሰብእና መዛባት የሚፈጠረው አካባቢን በሙሉ በጥርጣሬ ከመመልከትና ሰውን ሁሉ አደገኛ አድርጎ ከማሰብ የተነሳ ነው፡፡ የዚህ አይነት የሰብእና መዛባት ያለባቸው ሰዎች ያለምንም ተጨባጭ ማስረጃ አንድን ድርጊት ተፈጸመ ብለው ሊያስቡ ይችላሉ (Barlow እና Durand፣2015፣ 448)፡፡ ለምሳሌ የትዳር ጓደኛን ከሌላ ሰው ጋር ግንኙነት መስርቷል/መስርታለች በሚል መጠርጠር እንዲሁም በተለይ ወንዶች ከዓመታት በፊት ወልደው ያሳደጉትን ልጅ የእኔ አይደለም የሚል ጥርጣሬ ሊያድርባቸው ይችላል፡፡ በቅንነት የሚሰነዘረውን ሀሳብ ሁሉ ለጥቃት ተብሎ የተፈጠረባቸው ይመስላቸዋል፡፡ በጣም ተጠራጣሪ ስለሆኑና በሰው ላይ እምነት መጣል ስለሚሳናቸው ሁልጊዜም በጥንቃቄ ውስጥ ናቸው፡፡ በጣም ተከራካሪ፣ ሞጋች እና በጥያቄ የተሞሉም ናቸው (Parnas et al.፣ 2005፣ 1፣ 55 እና 56)፡፡ ማረጋገጫ በሌለው ሀሳብ ውስጥ መዋኘት ልምዳቸው ነው፡፡ ምስጢር ማካፈል አይፈልጉም፡፡ ምክንያቱም ሰዎችን የማያምኑ በመሆናቸውና መልሰው በተናገርነው ምስጢር አደጋ ሊያደርሱብን ይችላሉ በሚል ጥርጣሬ ሁሉን ነገር አምቀው ይይዛሉ፡፡ ቀላል ለሆኑት ጉዳዮች ሁሉ የሚያዋርድና ጥሩ ያልሆነ ትርጓሜ ይሰጣሉ፡፡ ለትንሽ ጥፋትም ቢሆን ይቅርታ ማድረግ አይፈልጉም፡፡ መልሶ ለማጥቃት ቅርብ ናቸው (Barlow እና Durand፣2015፣ 448)፡፡

## ፫. በአነጋገራቸው፣ በባሕርያቸው በአስተሳሰባቸው ላይ መዛባት ያለባቸው (Schizotypal Personality Disorder)

የዚህ አይነት የሰብእና መዛባት ችግር ያለባቸው አካላት ከሌሎች የሰብእና መዛባት ችግር ያለባቸው አካላት በተለየ መልኩ ችግር ውስጥ እንደሆኑ በቀላሉ መለየት ይችላሉ፡፡ ምክንያቱም ከተለመደው ወጣ ያለው አነጋገራቸውና የሚያሳዩት ባሕርይ የዚህ ችግር አመላካች ይሆንባቸዋል፡፡ ራሳቸውን ከማህበራዊነት ያገላሉ፤ ከሰው መቀላቀል አይፈልጉም፤ ኃላፊ የሆኑ የአእምሯዊ መዛባት ምልክቶችን ያሳያሉ፤ ከምንም አይነት ማህበራዊ ግንኙነትም ሆነ ዝምድና

የሚያሳዩት የደስታ ስሜት የለም (Parnas et al.፣ 2005፣ 1)። ምናልባት በእኛ ሀገር ‹‹እብድ›› ወይም የአእምሮ በሽተኛ ብለን የምንጠራቸውን ሰዎች የሚወክሉ ሊሆኑ ይችላል።

**2.1.3.2. ምድብ ‹‹ለ›› የሰብእና መዛባት (Cluster ‹‹B›› Personality Disorder)**

**፩. ለማህበረሰብ ህግና ደንቦች ግድ የሌላቸው (Antisocial Personality Disorder)**

የዚህ አይነት የሰብእና መዛባት ያለባቸው አካላት በሌሎች ሰዎች ላይ ሆን ብለው አካላዊና ሥነ ልቦናዊ ጥቃት የሚያደርሱ፣ ርሕራሔ የሌላቸውና የሰዎችን ስሜት የማይረዱ፣ ባጠፉት ጥፋት ጸጸት የማይሰማቸው፣ ከህይወት ተሞክሮ ትምህርት ወስደው ራሳቸውን ለማሻሻል የማይሞክሩ፣ በረቀቀ መንገድ ወንጀል ፈጽመው በቀላሉ ከህግ የሚያመልጡ ናቸው። Cloninger (2005፣ 125) የዚህ አይነት ሰብእና መቃወስ ያለባቸው አካላት በየእለት ኑሯችን ደጋግመን የምናገኛቸው፣ ለማህበራዊ ህጎች የማይገዙና የወንጀለኛነት ልምድን ያዳበሩ፣ በማንኛውም የእድሜ ክልል ልናገኛቸው የምንችል እንደሆኑ ያስረዳሉ።

**፪. ስለ ራሳቸው ማንነት ማወቅ የተቸገሩ (Borderline Personality Disorder)**

ይህ የሰብእና መዛባት የሚታይባቸው ሰዎች ባዶነት፣ ፍርሀትና የስሜት አለመረጋጋት የሚሰማቸው ሲሆኑ በዚህም ምክንያት ቁጡ፣ ራሳቸውን ለመጉዳትና ለማጥፋት የሚሞክሩ ናቸው (Stone፣ 2005፣ 202፣ 204 እና 205)። በስሜት የሚገፋፉ፣ ችኩል፣ በቀላሉ የሚናደዱና የሚበሳጩ ናቸው። ገለልተኛ፣ ተጠራጣሪ፣ አታላይ፣ ጥራዝ ነጠቅም ናቸው። ይህ የሰብእና መዛባት አብዛኛውን ጊዜ የሚከሰተው በሴቶች ላይ ነው። በተለይ በልጅነታቸው ፆታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ለዚህ ሰብእና መዛባት ችግር ተጋላጭ ናቸው። በመሆኑም የዚህ ሰብእና መዛባት ያለባቸው ሴቶች የኃይለኛነትና የቁጡነት ባሕርይ ላያሳዩ ይችላሉ። ኃይለኛነትና ገደብ የለሽ ቁጡነት ጎልቶ የሚታየው በወንዶች ላይ ነው (Barlow እና Durand፣ 2015፣ 466)።

**፫. በሰውነታቸው ያላቸውን መልካም ዋጋ የማይረዱ (Histrionic Personality Disorder)**

የዚህ ሰብእና መዛባት ሰለባ የሆኑ ሰዎች ስሜታቸውን በተጋነነ መልኩ ማንጸባረቅ የሚፈልጉ፣ የሌሎችን ትኩረት አብዝተው የሚሹና በእቅዳቸው ሁሉ የሌሎችን አበረታችነት የሚጠብቁ ናቸው። ሌላ ሰው ጣልቃ ሳያስገቡ ውሳኔ ለመወሰን ይቸገራሉ። ለፆታዊ ጉዳይ ያላቸው አመለካከትም አሉታዊ ነው። ከመጠን በላይ ለአለባበሳቸውና ለውበታቸው ይጨነቃሉ (Stone፣ 2005፣ 222)።

**፬. ራስወዳድነት የሚታይባቸው (Narcissistic Personality Disorder)**

የዚህ አይነት ሰብእና መዛባት ያለባቸው ሰዎች ሲበዛ ራስ ወዳድ፣ በነገሮች ሁሉ የራሳቸውን ጥቅም ብቻ የሚያሳድዱ፣ ቁጥጥርን የሚያዘወትሩ፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር ሲቀራረቡም ጥቅማቸውን የሚያሰላስሉ፣ እነሱ የፈለጉት ነገር ካልሆነ ለበቀል የሚጋበዙ እና ዓለም በእነሱ ዛቢያ ላይ ብቻ የምትሽከረከር የሚመስላቸው ናቸው (Ronningstam፣ 2005፣ 278፣ 279፣ 280፣ 295)፡፡ የዚህ ሰብእና መዛባት ያለባቸው አንዳንድ ሰዎች ትዕቢተኛ፣ ጉረኛ፣ ትኩረት የሚፈልጉ፣ ሁሉ በእጃቸው የሚመስላቸው ናቸው፡፡ ይህን ባሕርያቸውንም በግልጽና በኩራት ለማረጋገጥ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ሆን ብለውና አስበውበት ለመደበቅ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ የዚህ አይነት ባሕርይ የሚያሳዩ ሰዎችም ብልጥ፣ ቀናተኛ፣ አናዳጅ፣ በቀለኛ፣ ሌሎችን የሚንቁ ናቸው፡፡ በመሆኑም ከሌሎች ጋር የጋራ የሆነ ዝምድናና ግንኙነት መፍጠር አይችሉም፡፡ ለሁሉም ነገር ዋና ወይም ዐቢይ፣ ከሁሉም የበላይና የተለዩ፣ ምርጥ፣ ኃይለኛ፣ ሳቢና ማራኪ፣ የተደነቁ የሚመስላቸው፣ ትችት ነቀፋና ሽንፈት የማይዋጥላቸው ናቸው፡፡

### 2.1.3.3. ምድብ ‹‹ሐ›› የሰብእና መዛባት (Cluster C Personality Disorder)

#### ፩. ከማህበራዊ ሕይወት ራሳቸውን የሚያገሉ (Avoidant Personality Disorder)

በዚህ የሰብእና መዛባት የተጠቁ ሰዎች ሲበዛ የበታችነት ስሜት የሚሰማቸው፣ ሰዎች ሁሉ ስለ እነሱ ብቻ የሚያወሩ የሚመስላቸው፣ ሰዎች የሚወቅሷቸውና የሚያገሏቸው የሚመስላቸው፣ በሀዘንም ይሁን በደስታ ጊዜ በማህበራዊነት ላይ መሳተፍ የማይፈልጉ፣ ከጓደኛ ጋር መዝናናት እንኳ የሚያስጨንቃቸው ናቸው፡፡ በእነዚህም ምክንያቶች ራሳቸውን ከማህበራዊነት ያገላሉ፡፡ በጣም ጠቃሚ በሆነ ማህበራዊ ጉዳይ ላይም ቢሆን ለመገኘት የሚቸገሩ ናቸው፡፡ (Tyrer፣ 2005፣ 353)

#### ፪. በሌሎች ላይ ጥገኛ የሆኑ (Dependent Personality Disorder)

ይህ የሰብእና መዛባት የሚታይባቸው ሰዎች በራስ መተማመን የሌላቸው፣ ሲበዛ ሽቁጥቁጥና ለሰው አጎብዳጅ፣ በዕለት ከዕለት ኑሯቸው የሌሎችን ውሳኔ የሚጠብቁ ናቸው፡፡ ኃላፊነት ለመረከብ ብቁ ያልሆኑ፣ ሲበዛ ጥገኛ፣ ሁልጊዜም የሌሎችን እርዳታ የሚፈልጉ፣ ከሚፈጠር ቅርርብና ግንኙነት ሁሉ እርዳታ የሚጠብቁ፣ እርዳታ ላለማጣት ሲሉ በሁሉም ነገር የሚስማሙ በተቃራኒው አለመስማማትን የሚፈሩ፣ በራስ የመተማመን ብቃት የሌላቸው በዚህም ስራዎችን ኃላፊነት ወስደው ለማከናወን የሚቸገሩ፣ ለውድድር ራሳቸውን የማይጋብዙ፣ ከሰዎች ጋር የነበራቸው ግንኙነት ወይም ወዳጅነት ድንገት ቢቋረጥ በአስቸኳይ አዲስ ግንኙነትን የሚመሰርቱና ብቻቸውን መኖር የሚፈሩ ናቸው (Tyrer፣ 2005፣ 353)፡፡

**፫. ስለአንድ ነገር አጥብቀው የሚያሰላስሉ** (Obsessive Compulsive Personality Disorder)

የዚህ ሰብእና መዛባት ያለባቸው ሰዎች ለህግ፣ ለስርዓትና ለዕቅድ አብዝተው የሚጨነቁ፣ ያቀዱት ጉዳይ ካልተፈጸመ ረፍት የሚነሳቸው፣ የሚለብሱት ልብስ መዛነፍ ሳይቀር የሚረብሻቸው ናቸው። ቋሚ የሆነ እርግጠኝነት የማይታያቸው፣ ዝምድናንና ግንኙነትን የሚፈሩ ናቸው። ሲበዛ ንቁ፣ አንድን ነገር ለማስወገድ በጣም የሚጠነቀቁ፣ የተገደበ የህይወት መርህ የሚከተሉ ግንኙነት ወይም ቅርርቦሽ ለመፍጠር ፈቃደኛ የማይሆኑ ናቸው (Tyrer፣ 2005፣ 353)።

የተለያየ የሰብእና መዛባት ያለባቸው ግለሰቦች አንዳንድ ጊዜ ጭንቀታቸው ከመጠን በላይ ሲሆንባቸው ራሳቸውን ነጻ ለማድረግ ይገደዳሉ። በመሆኑም የተለያዩ ሥነ ልቦናዊ የመከላከያ ስልቶችን መጠቀሚያ በማድረግ ከጭንቀታቸው ያመልጣሉ።

### 2.1.4. ሥነ ልቦናዊ የጭንቀት መከላከያ ስልቶች (Defense Mechanisms)

የመከላከያ ስልቶች ሰዎች አንድን ድርጊት ለመፈጸም ሲነሱ አስቀድመው ከተጠያቂነት ነጻ ለመውጣት የሚነድፏቸው ዘዴዎች ናቸው። አብዛኛውን ጊዜ የኢድ ፍላጎት ሲያይል እና ተፈጻሚነት ሲያገኝ ኢጎ ራሱን ከጭንቀት ለማውጣት የተለያዩ የመከላከያ ስልቶችን ለመቀመር ይገደዳል። በተለያዩ አጋጣሚዎች ለሚገጥሙን አስቸጋሪ ሁኔታዎች ለምሳሌ ህመም፣ ጥሩ ያልሆነ ስሜት ጭንቀትና የመሳሰሉት ከሚፈጥሩብን ስሜት ፋታ ለማግኘት ሲባል እነዚህ ስልቶች አገልግሎት ላይ ይውላሉ። ስልቶቹ ከተፈጠረው ጊዜያዊ ውጥረት እንድንወጣና ከያዘን ህመምም እንድናገግም ይረዱናል። Jess እና Gregory (2005፣ 34-35) የመከላከያ ስልቶች በ1926 በFreud እንደተዋወቁና በኋላ ላይ የFreud ሴት ልጅ Anna Freud ጽንሰ ሀሳቡን እንዳሻሻሏቸውና እንዳደራጇቸው ይገልጻሉ። እነዚህ የመከላከያ ስልቶችም መደበኛና በዓለም አቀፍ ደረጃ እንደሚያገለግሉ ያስረዳሉ። በFreud የተቀመሩት የመከላከያ ስልቶችም ማመቅ ወይም መግታት (Repression)፣ በተቃራኒው ማሰብ (Reaction formation)፣ ስሜትን ለሌላ አካል ማስተላለፍ (Displacement)፣ ወደ መጀመሪያው መመለስ (Regression)፣ ማላከክ (Projection)፣ የሌሎችን ሀሳብ መቀበል (Introjection)፣ ማህበራዊ ተቀባይነት ባለው ተግባር መተካት (Sublimation) እንደሆኑ ይዘረዝራሉ።

**፩. ማመቅ ወይም መግታት** (Repression)

ማመቅ ወይም መግታት መሠረታዊ የሆነ የመከላከያ ስልት ነው። ምክንያቱም በሌሎች ውስጥ ተካቶ የሚገኝ ነው። ማስታወስ የማንፈልጋቸውና በንቁው የአእምሮ ክፍል እንዲቀመጡ

የማንፈቅድላቸው ሁኔታወችን በኢንቁ የአእምሮ ክፍል ውስጥ የማስቀመጥ ሒደትም ነው፡፡ ምንም እንኳ ኢጎ በኢድ ገደብ የለሽ ስሜቶች ተጽእኖ ቢደርስበትም እነዚህን ስሜቶች በማመቅ ራሱን ይጠብቃል፡፡ በአብዛኞቹ ጉዳዮች ማመቅ እስከ ህይወት ፍጻሜ አብሮ ይቆያል (Jess እና Gregory 2005፣ 35)፡፡ ማመቅ ወይም መግታት የመጀመሪያው ሥነ ልቦናዊ የመከላከያ ስልት ሲሆን ሌሎቹ የመከላከያ ስልቶች ተከትለው የሚመጡ ናቸው፡፡ ይህም የሚሆነው ታምቀው የነበሩ ምኞቶችና ስሜቶች ተመልሰው ሲመጡና ንቁ ሆነን ስናስባቸው ወደ ሌሎች ዘዴዎች ስለምናመራ ነው፡፡

ማመቅ በአእምሮ ውስጥ የሚያስጨንቅንና የሚያሳሳብን ስሜት ወደ ኢንቁው የአእምሮ ክፍል አርቆ የማስቀመጥ ሒደት እንደሆነ Paulhus፣ Fridhandler እና Hayes (1997፣ 545) ያስረዳሉ፡፡

**፪. በተቃራኒው ማሰብ (Reaction Formation)**

በሕይወት ዘመን በሚደረግ ትግል የሚያጋጥሙ የተለያዩ ጉዳዮች በስነ ልቦናችን ላይ ከሚያሳድሩት ጫና ራሳችንን ለማላቀቅ በተቃራኒው ማሰብን የሚመለከት ነው፡፡ ፍቅርን በጥላቻ ጥላቻን በፍቅር፣ ጥሩን በመጥፎ መጥፎን በጥሩ ነገር በመተካት ካጋጠመን ችግር ልናገግም የምንችልበትን ሁኔታ መፍጠር ይቻላል (Paulhus et al. 1997፣ 36)፡፡ ለምሳሌ አንድን ነገር እንደምንጠላው ውስጣችን ቢያውቅም እንደምንወደው በማድረግ መቅረብን የሚመለከት ነው፡፡

**፫. ስሜትን ለሌላ አካል ማስተላለፍ (Displacement)**

አንድ ችግር ከማንጋፋው አካል በሚያጋጥምበት ወቅት ከኛ በታች ባሉና አቅም በሌላቸው አካላት ላይ ቁጣን በመግለጽ ራሳችንን ከቀደመው ችግር ነጻ ለማውጣት የሚደረግ ስልት ነው (Jess እና Gregory 2005፣ 36)፡፡ ለምሳሌ አንዳንድ ሰዎች ቤታቸው ውስጥ በተፈጠረ ችግር ስራ ቦታ ላይ ያልተገባ ጸባይ ሊያሳዩ ይችላሉ፡፡ ከቤተሰብ ጋር ለተፈጠረ አለመግባባት የስራ ባልደረባን ውሀ ቀጠነ ፀጉር ይሰንጠቅ እየተባለ በሰበብ አስባቡ የስሜት መተንፈስ ሊኖር ይችላል፡፡ በአንፃሩ ከስራ ኃላፊ ወይም ከባልደረባ ጋር በተፈጠረ አለመግባባት የትዳር አጋርን ወይም የቤተሰብ አባላትን ተገቢ ያልሆነ ንግግር መናገር ሊሆን ይችላል፡፡ በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ሰዎች በአንድ ተግባር አለመሳካት ብስጭት ወይም ንዴት ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ የተለያዩ ቁሳቁሶችንም ይሁን በአካባቢ የሚገኙ እንስሳትን ያለ ጥፋታቸው መቅጣት የተለመደ ተግባር ነው፡፡ በዚህም ብስጭቴ ይቀልልኛል የሚሉ ብዙዎች ናቸው፡፡

### ፬. ወደ መጀመሪያው መመለስ (Regression)

ወደኋላ በመመለስና ባሳለፍነው ዘመናችን የሰራናቸውን መልካም ተግባራትና ጥሩ ስሜት ይሰጡን የነበሩ ሁኔታዎችን በማስታወስ ጥፋተኝነትን ለመርሳት የሚደረግ ስልት ነው (Jess እና Gregory 2005፣ 36)። የሰው ልጆች ቀድሞ ከሚያደርጉት ነገር በተለያዩ ሁኔታዎች ሲነጠሉ የመጨነቅና የመረበሽ አይነት ስሜት በውስጣቸው ሊፈጠር ይችላል። በዚህም ጊዜ ራስን ከጭንቀት ለማውጣት ወደ ቀድሞው የምንመለስበትን ዘዴ በማመቻቸት ጭንቀትን መቀነስ ይቻላል። ሆኖም ሙሉ በሙሉ ወደ ነበርንበት ለመመለስ አዳጋች ስለሚሆን ምልሰቱ በመተካካት የሚከናወን ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ አንድ ህፃን በሁለት ወይም በሦስት ዓመቱ ተከታይ ይወለድበትና ጡት ከመጥባት እንዲታቀብ ይደረጋል። ጡት ከመጥባት ውጭ ዓለም የሌለ የሚመስለውና ሕይወት የምትቀጥለው በመጥባት ብቻ ነው የሚል ስሜትን ያዳበረው ይህ ህፃን ድንገት እንክብካቤው ሲቀነስበትና የግሉ ወደሚመስለው ጡት እንዳይቀርብ ማዕቀብ ሲጣልበት በውስጡ የመገለል ስሜት ይሰማዋል። አዲስ ለተወለደው ህጻን የሚሰጠው እንክብካቤም ያስቀናዋል። በመሆኑም ለከፋ ጭንቀት ይጋለጣል። ከዚህ ጭንቀቱ ለመውጣትም ቀድሞ ያደርግ እንደነበረው የእናቱን ጡት ባያገኝም ከራሱ ጣት ጀምሮ ሊጠባ የሚችልን ነገር ሁሉ እየጠባ ቀድሞ ያገኘው የነበረውን ደስታ ለመቋደስ ጥረት ያደርጋል። በዚህም ቀስ በቀስ ከጭንቀቱ መገላገል ይጀምራል።

### ፭. ማላከክ (Projection)

የችግሩ ምንጭ ራሳችን ሆነን እያለ ሌላ የችግር ምንጭ በመፈለግ ስሜትን ለመግለጽ የሚደረግ ስልት ነው (Jess እና Gregory 2005፣ 37)። የማይፈለግን ውስጥን ሰላም የሚያሳጣን ስሜት ለሌላ አካል የማስተላለፍ ዘዴ ነው። ሌላውን አካል እንደ ችግር ምንጭ በማየት ችግሩን በዚያ አካል ላይ ለመጣል የሚደረግ ሙከራ ነው። ለምሳሌ አንድን ሰው የምንጠላው ቢሆን እሱ ስለማይወደኝ ነው የጠላሁት ወደሚል ማጠቃለያ መድረስን የሚመለከት ነው።

### ፮. የሌሎችን ሀሳብ መቀበል (Introjection)

ኢንቁ በሆነ መንገድ የሌሎችን ሀሳብ ወይም አመለካከት የመቀበልን ሒደት የሚመለከት ነው (Jess እና Gregory 2005፣ 37)። ይኸውም ጥሩ የሚባሉ ማህበራዊ ቅቡልነት ያላቸውንና ተጽእኖ ፈጣሪ የሆኑትን አካላት በማየትና በመስማት ሀሳባቸውንና አመለካከታቸውን የመጋራት ሁኔታ ነው። በተለይ የበታችነት ስሜት የሚሰማቸው አካላት እና በዚህ ሁኔታ ለሚሰቃዩ እንደ መፍትሔ ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

፮.ማህበራዊ ተቀባይነት ባለው ተግባር መተካት (Sublimation)

ይህ ስልት አንድ አስቸጋሪ ሁኔታ ሲያጋጥመን ችግሩን ለመወጣት የምንወስደውን መፍትሔ መልካም እንደሆነ የማሰብ ሒደትን የሚከተል ነው (Jess እና Gregory 2005፣ 38)፡፡ የችግሩን መጥፎ ጎን በመተው ጥሩ ጎኖችን ብቻ በማሰላሰል የሚፈጠር ነው፡፡ ማህበራዊ ተቀባይነት የሌላቸው ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ማህበራዊ ተቀባይነት የሚያገኙበትን መንገድ የመፍጠር ሒደትም ነው፡፡

## 2.1.5. ሥነ ጽሑፍና ፍካሬ ልቦና (Literature and Psychoanalysis)

ሥነ ጽሑፍና ፍካሬ ልቦና ከግሪክ ፈላስፋዎች (ከእነ አርስቶትል) ጀምሮ አንዱ በአንዱ ላይ አሻራውን እያሳረፈ ከዚህ ደርሰዋል፡፡ የሥነ ልቦና ጽንሰ ሀሳቦችን በሥነ ጽሑፋዊ ስራዎች ውስጥ መጠቀምና የኢንቂ ልቦና አሰራርን ለማሳየት መሞከር ዐቢይ ጉዳይ ነው (Abrams 1999)፡፡ ፍካሬ ልቦና በግልጽ በሚታዩ ሰብዓዊ ስሜቶች፣ ሀሳቦችና ባሕርያት ላይ ብቻ የተገደበ ሳይሆን ኢንቂ በሆኑት ስሜትና ባሕርይ ላይ የሚያሳድሩትን ተጽዕኖም ይመለከታል፡፡ በመሆኑም ፍካሬ ልቦና ለሥነ ጽሑፋዊ ሒስ መሠረታዊ የሆነ ጉዳይ ነው፡፡

ቀደም ባሉት ጊዜያት ፍካሬ ልቦና ድርሰትን የደራሲው የኢንቂ ልቦና ምኞት፣ የተፈጥሯዊ ፍላጎቶች እና የልቦና መቃወስ ማካካሻ አድርጎ ይመለከት ነበር፡፡ የFreud ፍካሬ ልቦናዊ ሒስም ይህን የሚያቀነቅን ነበር፡፡ በዋናነት ፍካሬ ልቦና የሚለው ቃልም ያገለግል የነበረው አእምሯቸው የታወከ በሽተኞችን ለማከም ነበር፡፡ ይኸውም በሽታን ለመለየት ከፍተኛ አገልግሎት ይሰጥ ነበር፡፡ በሽተኛው የሚናገራቸውን ነገሮች፣ የሚያከናውናቸውን ተግባራትና ውስጣዊ ፍላጎቱን የመመርመር ዘዴን ይጠቀማል (Gbenoba እና Okoroegbe፣ 2014፣ 250)፡፡ ይህም ሥነ ጽሑፍን የሚጎዳ እንደነበርና  ቀስ በቀስ ይህ አይነቱ ግንዛቤ እየተለወጠ ሊመጣ እንደቻለ ያስረዳሉ፡፡ Lacan የሥነ ጽሑፍን መዋቅር መነሻ በማድረግ በጽሑፉ (Text) የተገለጸውን ሥነ ልቦናዊ ብልሀት እና የገፀባህርያትን አእምሯዊ አሰራር መፈተሽ እንደሚቻል እንዳሳዩም ያስገነዝባሉ፡፡

ሥነ ጽሑፍና ሥነ ልቦና ትስስራቸው ከልቦና ነቅተው በአእምሮ የሚመነጩ ስለሆኑ ብቻ ሳይሆን የኢንቂ ልቦና ትዕምርቶች፣ ፍላጎቶችና ምኞቶች የሚንፀባረቁባቸው ጭምር ስለሆኑ ነው፡፡ ሁለቱም የእውቀት መስኮች በሰው ልጆች ማንነትን በማንፀባረቅና በትዕምርት አፈጣጠር ብቃታቸው አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ዘርፎች ናቸው፡፡ ሁለቱም ዘርፎች የግለሰብ ጉዳዮችን በትዕምርትነት በመውሰድ ለመመርመር የሚሞክሩ ናቸው፡፡ ሥነ ጽሑፍ ትርጉምንና

ኪናዊነትን፣ ሥነ ልቦና ደግሞ የአእምሯዊና ሥነ ልቦናዊ ጉዳዮችን ምንጭ ለመፈለግ የሚጥሩ በመሆናቸው ዝምድናቸው ከፍ ያለ ነው (Habib፣ 2005፣ 571)፡፡

Abrams (1999፣ 248) እንደሚሉት የተከለከሉና አይነኬ ተብለው የተቀመጡት በተለይ ከግብረ ስጋ ግንኙነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ከሰርካዊው የሰው ልጅ አኗኗር ጋር ስለማይስማሙና ስለሚጨቆኑ በኢንቁ ልቦና ውስጥ ተከልለው ይኖራሉ፤ ንቁ ልቡናም እነዚህን ከዘወትራዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ጋር የሚፃረሩ ስለሆኑ በኢጎ አማካኝነት ከዘወትራዊው ህይወት እንዲገለሉ ያደርጋል፡፡ በመሆኑም የኪነ ጥበብ ስራዎች እነዚህን በባህሉ ምክንያት የተከለከሉ ጉዳዮችና ጨቋኝ ሰብእና የማጣጣም እና የማስታረቅ ስልት አላቸው፡፡ አንድን ድርሰት ከሥነ ልቦና አንፃር ለመተንተንም ከሰርካዊ ጉዳዮች ጀርባ መቃኘት ተገቢ ነው፡፡

የፍካሬ ልቦና ሀያሲዎች የሰው ልጅ አእምሯዊ ብቃት በምን መንገድ በሥነ ጽሑፍ ውስጥ እንደተገለፀ ተንትነው ያሳያሉ፡፡ ይህንን የሚያደርጉትም በFreud ስራ ላይ ተመስርተው ነው፡፡ እንደ ሥነ ልቦናውያን እምነት ደግሞ ሁሉም የሰው ልጅ ድርጊትና እንቅስቃሴ የኢንቁው የአእምሮ ክፍል ተጽዕኖ አለበት፡፡ በዚህም የገፀባህርያትን ድርጊትና መነሳሳት ይተነትናል (Gbenoba እና Okoroegbe፣ 2014፣ 250)፡፡ የሰው ልጆች ከሌሎች ሰዎች ጋር በሰላም መኖር ይቻላቸው ዘንድ በርካታ ፍላጎታቸውን እና ምኞታቸውን ይጨቁናሉ፤ ይገታሉ፡፡ እነዚህ ጭቁን ሀሳቦችና ፍላጎቶችም ኢንቁ በሆነው የአዕምሮ ክፍል ይከማቻሉ፤ ይጠራቀማሉ፡፡

የፍካሬ ልቦና ጠበብት የተለያዩ የኪነጥበብ ስራዎችን በመተንተን የከያኒያንን ሥነ ልቦናዊ አወቃቀር ያጠናሉ፡፡ ምክንያቱም የኪነ ጥበብ ስራዎች ስለከያኒው የሚያሳዩት ሥነ ልቦናዊ ጉዳይ ስላለ ነው፡፡ ቀደም ባሉት ጊዜያት የነበሩት ሀያሲዎች የሚያተኩሩት በደራሲያንና ገፀባህርያት ላይ ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት ያሉት ዘመናዊ ሀያሲያን ደግሞ ከደራሲውና ከገፀባህርያት በተጨማሪ ጽሑፉ (Text) እና ተደራስያን ቀልባቸውን የሳቧቸው ጉዳዮች ሆነዋል፡፡ ለምሳሌ ሀያሲ Norman Holland እንደሚሉት አንባቢዎች አንድን የሥነ ጽሑፍ ስራ አንብበው የሚሰጡት የተወሰነ ምላሽ ከኢንቁው የአእምሯቸው ክፍል የመነጨ ነው፡፡ በመሆኑም አንድን ጽሑፍ በሚመለከት የሚሰጠው ምላሽ ከአንባቢ አንባቢ ይለያያል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ፈረንሳያዊው የሥነ ልቦና ሊቅና ሀያሲ Jacques Lacan አንድን የሥነ ጽሑፍ ስራ ያነበቡ አንባቢዎች በተለያየ መንገድ ትንታኔ ሊሰጡ እንደሚችሉ ያስረዳሉ (Gbenoba እና Okoroegbe፣ 2014፣ 251)፡፡

ፍካሬ ልቦና ሥነ ጽሑፍ የደራሲው ኢንቁ ወይም ድብቅ የሆነው አእምሯዊ እውቀት ማንፀባረቂያ ወይም ማሳያ እንደሆነ ያምናል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ በሥነ ጽሑፍ ውስጥ ኢንቁ የሆነው የደራሲው እሳቤ በህልም ወይም በገፀባህርያት አማካኝነት ሲገለፅ ይስተዋላል፡፡ በአንባቢውና በጽሑፉ መካከል ያለውን ዝምድና በመተንተንና በመተርጎም በኩልም ፍካሬ ልቦና አገልግሎት ላይ ይውላል (Gbenoba እና Okoroegbe፣ 2014፣ 253)፡፡ አንድ አጥኝም በአንድ ሥነ ጽሑፋዊ ስራ ላይ በፍካሬ ልቦና ትንታኔ መስጠት ከፈለገ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ እያስገባ ንባቡን ማካሔድ እንደሚችል ይገልጻሉ፡፡

- ሥነ ጽሑፋዊ ስራው ከህልም ጋር ተመሳስሎ የቀረበባቸው መንገዶች ምን ምን ናቸው?
- ኢንቁ የሆኑ ፍላጎቶች፣ ፍርሀቶችና የማይረግቡ ግጭቶች በገፀባህርያት፣ በመቼት ወይም በቀረበው ክስተት በተራኪው አማካኝነት ምን ያህል ከህልም ጋር ተመሳስለው ቀርበዋል?
- የሥነ ጽሑፍ ስራው ስለ ደራሲው ስነ ልቦናዊ ሁኔታ ምን ይገልፃል?
- በአንባቢያን ላይ ሥነ ልቦናዊ መነቃቃት የመፍጠር ሒደቱ ምን ይመስላል? የሚሉትንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ማንሳትና ተገቢ መልስ ለመስጠት በሚያስችል መልኩ ንባብን ማከናወን ተገቢ ነው፡፡

## 2.2. ትወራዊ ማህቀፍ

ለዚህ ጥናት መተንተኛነት ጥቅም ላይ የዋለው ትወራዊ ማህቀፍ ፍካሬ ልቦናዊ ትወራ (Psychoanalytic Theory) ሲሆን ትወራው የተመረጠበት ምክንያትም የሰብእና ጉዳይ ሥነ ልቦናዊ ጣጣ ስላለውና በግልጽ የማይታየውን የሰው ልጅ ድብቅ ሰብእና በFreud የሰብእና ፍካሬ ልቦናዊ መርሆች ለመተንተን አመች ነው ተብሎ ስለታመነ ነው፡፡ በተለይም ኑባሬያዊና መዋቅራዊ የሰብእና አወቃቀር ሞዴሎች ሰብእናን ለማጥናትም ሆነ ለመተንተን አስፈላጊ ሆነው ስለተገኙ ነው፡፡ እንዲሁም ለተለያዩ የሰብእና መዛባቶች ማስታገሻነት ጥቅም ላይ የሚውሉ ሥነ ልቦናዊ የጭንቀት መከላከያ ስልቶች የፍካሬ ልቦና ማጠንጠኛዎች ስለሆኑ ሊመረጥ ችሏል፡፡ እነዚህን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ በማስገባትም ፍካሬ ልቦናዊ ትወራ ለጥናቱ መቀንበቢያነትና መተንተኛነት ሊመረጥ ችሏል፡፡ የትወራውን ምንነት፣ አነሳስና እድገት በሚመለከትም በሚከተለው መልኩ መመልከት ይቻላል፡፡

የስነ ልቦና መርሆችን ለሥነ ጽሑፍ ሳይንሳዊ ጥናት በተግባር ላይ ማዋል የቅርብ ጊዜ ክስተት ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተዋወቀውም Sigmund Freud ሲሆን Alfred Adler፣ Carl Jung እና Jacques Lacan እያሻሻሉና እያስፋፉ ለማሔሻነት ተጠቅመውበታል (Habib፣ 2005፣ 571)። Freudም በየጊዜው ማሻሻያ እያደረገ ለተለያዩ መስኮች ማጥኛነት ምቹ እንዲሆን አድርጎታል።

Cuddon (1998፣ 332-334) ፍካሬ ልቦና ቀደም ባሉት ጊዜያት በከያኒውና በኪነ ጥበብ ስራው መካከል ያለውን ዝምድና በመመርመር ላይ ያተኮረ እንደነበረ ገልጸው አጠቃላይ አጀማመርና እድገቱን በሚመለከት በሚከተለው መልኩ አቅርበውታል።

ፍካሬ ልቦና (Psychoanalysis) የሚለውን ቃል ያስተዋወቀው Sigmund Freud በ1896 ሲሆን *The Interpretation of Dreams* በሚለው ስራው በ1900 የተለያዩ የሥነ ልቦና መርሆችን በመጠቀም በOedipus እና Hamlet ላይ ትንተናውን አካሒዷል። በ1913 *The Theme of The Three Caskets* በሚል ርዕስ ባቀረበው ጽሑፍ *The Merchant of Venice* እና ስለ ንጉሱ Lear በተለይ ደግሞ ከCordelia ጋር እንደገና ስለመሰረተው ጓደኝነት፣ በ1915 *Some Character-Types Met With in Psychoanalytic Work* በሚለው ስራው በLady Macbeth፣ Rechard III እና በIbsen Rebecca ላይ ሰፊ ትንታኔ ሰጥቷል። በ1917 ላይ ደግሞ *Delusion and Dream* በሚለው ስራው የDostoievskiን *The Brothers Karamazov* እና የWilhelm Jensenን *Gradiva* በጥልቀት መርምሯል።

በ1949 የFreud ተከታይ የነበረው Ernest Jones *Hamlet* እና *Oedipus* በሚል የFreudን ሀሳብ በመከተል ጥናቱን አካሒዶ የኤዲፐሳዊ ቅዠትን (Oedipus Complex) ጭብጥ አሳይቷል። Lionel Trilling እና Edmund Wilson የFreudን ሥነ ልቦናዊ መርሆች መሠረት በማድረግ ጥናታቸውን ያካሔዱ ምሁራን ናቸው። የልጅነት ጊዜ ልምድንና የፈጠራ ስራን ግንኙነት ባጠኑበት ስራቸውም ደራሲውን ለመፃፍ ያነሳሳውን ነገር ለመፈተሽና ለመመርመር የደራሲውን የህይወት ታሪክ ማወቅ አስፈላጊ እንደሆነ ጠቁመዋል።

በSigmund Freud እና Erik Erikson የሥነ ልቦና መርሆች ተጽዕኖ ስር የነበሩ ሀያሲዎች በከያኒውና በኪነ ጥበብ ስራው መካከል ጥብቅ የሆነ ግንኙነት እንዳለ በመግለጽ የኪነ ጥበብ ስራዎችም የከያኒው የጭንቀት መተንፈሻዎች እንደሆኑ ያስረዳሉ። Harold Bloom (1973)

*The Anxiety Influence* በሚለው ስራቸው ላይ በተለይ ገጣሚያን በጭንቀትና ስሜት የተጨቆኑ እንደሆኑና ግጥሞቻቸውም የጭቆናቸው መተንፈሻ እንደሆኑ አሳይተዋል፡፡

ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለው ቀደም ባሉት ጊዜያት ፍካሬ ልቦና አብዛኛውን ጊዜ ያተኩር የነበረው በከያኒያንና በኪነጥበብ ስራዎቻቸው መካከል ያለውን ዝምድና በመፈተሽ ላይ ነው፡፡ አጥኝዎችም ይህንን ለመመርመር የደራሲውን የህይወት ታሪክ ማጥናትና በኪነ ጥበብ ስራው ውስጥ የተሳሉ ገፀባህርያትን እንደ ደራሲው የማየት እንዲሁም ከያኒው ጤና የጎደለው ሰው ነው፤ ስራውም የቀውሱ ማካካሻ የሚል አዝማሚያ የሚስተዋልበት ነበር፡፡ በሒደት ግን ይህ ሀሳብ እየተቀየረ ሌሎች የሥነ ልቦና መርሆች መካተት ጀምረዋል፡፡ ከደራሲው ወደ አንባቢው በመሸጋገርም የሚጠናበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ አንድ የሥነ ጽሑፍ ስራ በአንባቢው ላይ ያሳደረው ሥነ ልቦናዊ ሁኔታ ምን ይመስላል የሚለውን መመርመርም የፍካሬ ልቦና ትኩረት እየሆነ መጥቷል፡፡ Cuddon (1998፣ 334) Holland (1975)ን በመጥቀስ እንደሚገልጹት አንባቢ የተለያዩ የሥነ ጽሑፍ ስራዎችን የሚጠቀመው ኢንቁ የሆነውን አእምሯዊ ፍላጎት ለማርካት ነው፡፡ በመሆኑም አንድን የሥነ ጽሑፍ ስራ በሥነ ልቦናዊ መርሆች ለመመርመር ሲታሰብ በደራሲው፣ በፈጠራ ሒደቱ፣ በቀረቡት ሥነ ልቦናዊ ሀሳቦችና በአንባቢው ላይ ሊያሳድር በሚችለው ሥነ ልቦናዊ ተጽዕኖ ላይ ማተኮር እንደሚገባ Wellek እና Warren (1949፣ 75) ይመክራሉ፡፡ ይህ ጥናትም የተተነተነው ከላይ ለማብራራት በተሞከረው ፍካሬ ልቦናዊ ንድፈ ሀሳብ መሠረት ነው፡፡ በመሆኑም የFreudን የሰብእና መዋቅራዊ ሞዴሎችና ሥነ ልቦናዊ የጭንቀት መከላከያ ስልቶች በመከተል ትንተናው ተካሒዷል፡፡

## 2.3. የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

ይህ ክፍል በርእሰ ጉዳይና በመጽሐፍ ወይም በቴክስት ምርጫ ከዚህ ጥናት ጋር ዝምድና ያላቸው ጥናቶች አንድነትና ልዩነት እንዲሁም የትኩረት አቅጣጫ በዝርዝር የሚቀርብበት ነው፡፡ ሆኖም አጥኝው እስካሁን ባደረገው ዳሰሳ በሌላ ሰው ረጅም ልቦለድ ላይ የተጠና የምርምር ስራ አላጋጠመውም፡፡ ከርዕሰ ጉዳይ አንጻር ግን በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች የተካሔዱ ጥናቶችን በበይነ መረብ ባደረገው ዳሰሳ ሊመለከት ችሏል፡፡ ከነዚህም መካከል አንዳንዶቹ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረቡ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ በተለያዩ የጥናትና ምርምር ተቋማት የምርምር መጽሔቶች ላይ ለህትመት የበቁ መጣጥፎች ናቸው፡፡ ከእነዚህ የመመረቂያ ጽሑፎችና መጣጥፎች መካከል ይበልጥ ከጥናቱ ጋር የሚቀራረቡትን

በመለየት ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡ እያንዳንዳቸው ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰሉበትና የሚለያዩበት ጉዳይም በሚከተለው መልኩ በዝርዝር ቀርቧል፡፡

በመጀመሪያ ላይ ለሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረቡት የምርምር ስራዎች ይቃኛሉ፡፡ ከእነዚህም ስራዎች መካከል ከሀገር ውጭ የቀረቡት በቅድሚያ ከተዳሰሱ በኋላ አንድ በሀገር ውስጥ የተሰራ በአንጻራዊነት ከዚህ ጥናት ጋር ግንኙት አለው ተብሎ የታሰበ የምርምር ስራ ተዳሷል፡፡ በመቀጠልም በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ የምርምር መጽሔቶች ላይ የቀረቡ መጣጥፎች ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው ተመሳስሎና ልዩነት በዝርዝር ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

Fauziyah (2008) ‹‹Psychological Analysis of the main character's personality in Go Ask Alice›› በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ጥናት ያደረጉ ሲሆኑ ዋና ዓላማቸውም በልቦለዱ ውስጥ ሰብእና እንዴት እንደተገለጸ መመርመር ነው፡፡ ለዚህም የAbrham Maslowን ቀስቃሽ ትወራ (Motivation Theory) ተገልግለዋል፡፡ ጥናቱ ከፍካሬ ልቦና መሠረታዊ ሀሳቦች አንፃር ሰብእናን ማደሪያ በማድረግ የተካሔደ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ሲመሳሰል ትኩረቱን በዋና ገፀባህርይ ላይ ብቻ ማድረጉና የAbrham Maslowን ቀስቃሽ ትወራ መጠቀሙ ከዚህ ጥናት እንዲለይ ያደርገዋል፡፡ ምክንያቱም ይህ ጥናት የSigmund Freudን ፍካሬ ልቦናዊ ትወራ (በተለይ ከሰብእና ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የሰብእና አወቃቀር ሞዴሎችና ሥነ ልቦናዊ የጭንቀት መከላከያ ስልቶች) መሠረት በማድረግ የተመረጡ ገፀባህርያትን ሰብእና መመርመርን ዋና ዓላማው አድርጎ የተካሔደ ነው፡፡ በተጨማሪም የFauziyah ጥናት የዋና ገፀባህርይዋን ሰብእና መፈተሽ እንጂ ሰብእና የተዋቀረበትን ስልትና ለሥነ ጽሑፉ ሊያበረክት የሚችለውን ኪናዊ ፋይዳ አልተመለከተም፡፡ ይህ ጥናት ግን የገፀባህርያትን ሰብእና ለማዋቀር ጥቅም ላይ የዋለውን ስልትና ለምን ኪናዊ ፋይዳ ጥቅም ላይ እንደዋለ የመረመረ በመሆኑ ከFauziyah ጥናት ይለያል፡፡

Faisal (2011) ‹‹Analysis of Main Character on Bruce Almighty Movie Viewed from Personality Traits Theory by Costa and McCrae›› በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ጥናት አድርገዋል፡፡ ጥናቱ ሰብእናን በሚመለከት የተደረገ መሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ጉዳይ ነው፡፡ ሆኖም ልዩነቶች ይስተዋላሉ፡፡ የFaisal ጥናት ከኪነ ጥበብ ዘውጎች መካከል በፊልም ላይ ሲያተኩር ይህ ጥናት ግን በልቦለድ ላይ ማተኮሩ፣ የFaisal ጥናት በዋና ገፀባህርይው ላይ ማተኮሩ ይህ ጥናት ደግሞ በተመረጡ ገፀባህርያት ላይ የተከናወነ መሆኑ እና የFaisal ጥናት በCosta እና McCrae የሰብእና ትወራ መርሆች የተቃኘ

ሲሆን ይህ ጥናት ግን የፍካሬ ልቦናን ንድፈ ሀሳባዊ መርሆች መሠረት በማድረግ የተካሔደ መሆኑ ጥናቶች እንዲለያዩ የሚያደርጓቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡

ወደ ሀገር ውስጥ ተመልሰን በአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ላይ የተደረጉትን ጥናቶች ስንቃኝ የተወሰኑት ፍካሬ ልቦናዊ ትወራን መሠረት በማድረግ የተከናወኑ አንዳንዶች ደግሞ ፍካሬ ልቦናን በአጋዥነት የተገለገሉ እንደሆኑ ለመቃኘት ተችሏል፡፡ ሆኖም በትወራ አጠቃቀም ከዚህ ጥናት ጋር ቅርበት ሊኖራቸው ይችላሉ ተብለው ቢታሰቡም፣ በቀጥታ ስለማይዛመዱ ለቅኝታዊ ትንታኔ አስፈላጊ መስለው አልታዩም፡፡ በመሆኑም በቀጥታ ሰብእናን ጉዳያቸው አድርገው የተከናወኑ የጥናት ስራዎች ባይገኙም ከሌሎች ጉዳዮች ጋር አዛንቀው የተገለገሉ ጥናቶችን ለመፈተሽ በተደረገው ሙከራ ቴዎድሮስ (2006) ‹‹‹ልጅነት›› በማህሴትና አለንጋና ምስር፤ ሥነ ልቦናዊ ትንተና›› በሚል ርእስ ያካሔዱት የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ሊገኝ ችሏል፡፡ ቴዎድሮስ በዋናነት ይዘውት የተነሱት ዓላማ ልጅነት በተመረጡት የአዳም ስራዎች ውስጥ በምን መልኩ እንደተቀረጸ መፈተሽ ቢሆንም ከዚሁ ጋር አያይዘው ሰብእናን በጥቂቱም ቢሆን የዳሰሱበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡

የቴዎድሮስ ጥናትና ይህ ጥናት ሥነ ልቦናዊ ጉዳዮችን ማንሳታቸውና የFreudን ፍካሬ ልቦናዊ ትወራን በጋራ መገልገላቸው የሚያዛምዳቸው ሲሆን ልዩነቶችም ይስተዋሉባቸዋል፡፡ የቴዎድሮስ ጥናት ፍካሬ ልቦናን መሠረት በማድረግና የFreudን ‹‹ሳይኮሴክሽዋል›› የእድገት ደረጃ (Psychosexual Development) መመሪያ በማድረግ ልጅነትን የመረመረ ሲሆን ይህ ጥናት ግን የFreudን የሰብእና መዋቅር እንዲሁም ፍካሬ ልቦና ወደ ሥነ ጽሑፍ ቤት ሲገባ ይዟቸው የሚገባውን ጓዝ መሠረት በማድረግ ሰብእናን መርምሯል፡፡ በዚህም ልዩነታቸው ይጎላል፡፡ በተጨማሪም የቴዎድሮስ ጥናት የEriksonን ትወራ የተጠቀመ ሲሆን ይህ ጥናት ግን አልተገለገለበትም፡፡

Robinson (1985) ‹‹Style and Personality in the Literary Work›› በሚል ርዕስ ባቀረቡት መጣጥፍ የአጻጻፍ ስልትና ሰብእና በሥነ ጽሑፋዊ ስራዎች ውስጥ ያላቸውን ዝምድና የቃኙ ሲሆን በጥናታቸውም የገፀባህርያት አሳሳልም ሆነ የትልም አወቃቀር የደራሲው የሰብእና ውጤት ወይም ማሳያ ነው ወደሚል ድምዳሜ ለመድረስ ችለዋል፡፡ ጥናቱ ሰብእናን እንደ አንድ ርዕሰ ጉዳይ ይዞ ለመመርመር መነሳቱና የትኩረት አቅጣጫውን በሥነ ጽሑፍ ስራዎች ላይ ማድረጉ ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ ስልትና ሰብእናን በማጣመር የደራሲውን ሰብእና ለመለየት ጥረት የሚያደርግ መሆኑ፣ የሥነ ጽሑፍ ስራውን ከደራሲው

አቅጣጫ ብቻ የመመልከት አዝማሚያ የሚያሳይ መሆኑና ጥቅም ላይ የዋሉት ዘዴዎች በግልጽ ተለይተው አለመታየታቸው ደግሞ ከዚህ ጥናት እንዲለይ ያደርጉታል፡፡ በተጨማሪም በርዕሰ ጉዳይ ምርጫ ሰፊ መሆኑና በአንዱ የሥነ ጽሑፍ ዘውግ ብሎም በአንድ ስራ (Text) ላይ ያልተወሰነ መሆኑ ከዚህ ጥናት ይለየዋል፡፡

Flekova እና Gurevych (2015) ‹‹Personality Profiling of Fictional Characters using Sense-Level Links between Lexical Resources›› በሚል ርዕስ ባቀረቡት ጥናት በልቦለድ ገፀባህርያት በተለይ በዋና ገፀባህርያት ላይ በማተኮር ሰብእና በቃላት አማካኝነት እንዴት ሊገለጽ እንደሚችል ለማሳየት ችለዋል፡፡ የእነ Flekova ጥናት ያተኮረው የዋና ገፀባህርያት ሰብእና በንግግር ወቅት በቃላት ብሎም ግሶችን በሚናገሩበት ጊዜ እንዴት ሊንጸባረቅ እንደቻለ በመፈተሽ ላይ ሲሆን፣ ለሰብእና መዋዠቅ ሰበብ የሚሆኑ ጉዳዮችን ለይቶ በማመልከት በኩል ትኩረት የሰጠ አይመስልም፡፡ ጥናቱ በገፀባህርያት ሰብእና ላይ መመስረቱ ከዚህ ጥናት ጋር ሲያመሳስለው፣ ዋና ትኩረቱን ቃላት ላይ በማድረግ ሰብእናን ለማጥናት መሞከሩ፣ ሰብእናን ለመቅረጽ የሚያስችሉ ጉዳዮችን አለማመላከቱ፣ የገጸ ባሕርያቱ ሰብእና አቀራረብ ለፈጠራ ስራዎች ሊኖረው የሚችለውን ኪናዊ ፋይዳ አለማሳየቱና ለሰብእና መዛባት ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮችን በዝርዝር ለይቶ ማመልከት አለመቻሉ ከዚህ ጥናት ይለየዋል፡፡

በKusumawati (2013) ‹‹The Personality of the Main Character as Reflected in Paulo Coelho's The Devil and Miss Prym: A Psychological Study›› በሚል ርዕስ በተደረገ ጥናት የዋና ገፀባህርይውን ሰብእና እና በገፀባህርይው ሰብእና ላይ ተጽእኖ ያሳደሩ ነገሮች እንዲሁም ሰብእና በልቦለዱ ውስጥ በምን መልኩ ሊገለጽ እንደቻለ በዝርዝር ቀርቧል፡፡ ጥናቱ ሰብእናን በጥናት ርዕስነት ይዞ መቅረቡና ሰብእና እንዴት ሊንጸባረቅ እንደቻለ መመርመሩ ከዚህ ጥናት ጋር ሲያመሳስለው ከዋና ገፀባህርይው ውጭ ያሉትን ገፀባህርያት ሰብእና በምን መልኩ እንደቀረበና ለስራው ያበረከተው አስተዋጽኦ ምን እንደሆነ ለይቶ ባለማመለክቱ ከዚህ ጥናት ይለያል፡፡

Johnson et al. (2010) ‹‹Portrayal of personality in Victorian novels reflects modern research findings but amplifies the significance of agreeableness›› በሚል ርዕስ በቪክተሪያውያን ልቦለዶች ላይ ባካሔዱት ጥናት የገፀባህርያትን ሰብእና በመመርመር ደራስያን በስራዎቻቸው ውስጥ ሰብእናን በብዛት እንደሚሰብኩና እንደሚያትቱ አረጋግጠዋል፡፡ በተለይ ከዘመናዊው የሰብእና ሥነ ልቦና (Modern Personality Psychology) ጋር የሚያያዙ

መሠረታዊ ሀሳቦች እንደተንጸባረቁም ለመፈተሽ ችለዋል፡፡ የእነ Johnson ጥናት በሰብእና ማጠንጠኛነት በልቦለድ ላይ የተካሔደ መሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያዛምደው ሲሆን ጽንሰ ሀሳቡ ጥቅም ላይ ከሚውልበትና ከጽሑፍ (Text) ምርጫ አንጻር ግን ልዩነት ይስተዋላል፡፡ ይኸውም የእነ Johnson ጥናት ሰብእና በልቦለዶች ውስጥ ምን ያህል እንደተንጸባረቀ የሚመረምር ሲሆን ይህ ጥናት ግን የሰብእናን በልቦለዱ ውስጥ መታየት ማረጋገጥ ሳይሆን ሰብእናዊ ጉዳዮች በገፀባህርያት ላይ እንዴት እንደቀረቡና ለምን ኪናዊ ፋይዳ ጥቅም ላይ እንደዋሉ መመርመር ነው፡፡ በቴክስት ምርጫም ቢሆን ጥናታቸው ያተኮረው በቪክቶሪያውያን ልቦለዶች ላይ በሙሉ ሲሆን ይህ ጥናት ግን ከኢትዮጵያ ልቦለዶች መካከል በአንዱ ላይ የተወሰነ ነው፡፡ ይህም ጥናቶቹ ለሚከተሉት የአጠናን ዘዴና ስልት መለያየት ምክንያት ሊሆን ችሏል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የጥናቱ ሥነ ዘዴና ንድፍ

## 3.1. የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት አይነታዊ የምርምር ሥነ ዘዴንና ገላጭ የምርምር ንድፍን ተከትሎ የተካሔደ ሲሆን ጽሑፋዊ ትንታኔ (Text Analysis) ደግሞ በፍካሬ ልቦና መሠረተ ሀሳቦች በመታገዝ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለመተንተን ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ምክንያቱም ለትንታኔ የተመረጡት መረጃዎች በቁጥር የቀረቡ ሳይሆኑ በገለፃ እና በትረካ ስልት በጽሑፍ የቀረቡ በመሆናቸው ነው፡፡ በመሆኑም እንደዚህ አይነት ባሕርይ ያላቸውን የምርምር ስራዎች ለማከናወን ተገቢ ነው ተብሎ ስለታመነ ነው፡፡ እንዲሁም ማን፣ ምን፣ እንዴት የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ስለሚያስችልና ሰብእና በሌላ ሰው ረጅም ልቦለድ ገፀባህርያት ውስጥ እንዴት እንደተዋቀረ ለመመርመር ስለሚያስችል ነው፡፡ ጽሑፎችን ለመተንተን ፍካሬ ልቦናዊ ትወራ (Psychoanalytic Theory) ጥቅም ላይ የዋለውም ከሰብእና ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በልቦለዱ ውስጥ ያላቸውን ኪናዊ ፋይዳ ከፍካሬ ልቦና መርሆች አንፃር ለመተንተን ያስችላል ተብሎ ስለታሰበ ነው፡፡

## 3.2. የመረጃ ምንጭና አመራረጥ

ለዚህ ጥናት በመረጃ ምጭነት ያገለገለው፣ በምህረት ደበበ በ2007 ዓ.ም ሌላ ሰው በሚል ርዕስ ለህትመት የበቃው ረጅም ልቦለድ መጽሐፍ ሲሆን መጽሐፉ የተመረጠውም በዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ስልት (Purposive Sampling Technique) ነው፡፡ ይህ የናሙና ዓመራረጥ ስልት ጥቅም ላይ የዋለው ጥናቱ ይዞት የተነሳውን ዓላማ ከግብ ያደርስ ዘንድ ተፈላጊ የሆነውን የሥነ ጽሑፍ ስራ ለመምረጥ ስለሚያስችል ነው፡፡ ከሌሎች የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ስራዎች ሌላ ሰው ረጅም ልቦለድ የተመረጠበት ምክንያት አንድም ልቦለዱ በቅርብ ለንባብ የበቃ መሆኑ ወቅታዊነትን ጠብቆ ይገኛል ተብሎ መታመኑ ነው፡፡ ሁለትም የልቦለዱ ደራሲ የሥነ ልቦና ባለሙያ እንደመሆኑ መጠን ሥነ ልቦናዊ ጽንሰ ሀሳቦች ወይም ጉዳዮች ተካተው ሊሆን ይችላል ከሚል ግምት በመነሳት በቅድመ ምርምር ዳሰሳ ወቅት ይህን ማረጋገጥ ስለተቻለ ነው፡፡ በመሆኑም ከሌሎች የሥነ ጽሑፍ ስራዎች ይልቅ በዚህ ላይ ጥናቱ ቢካሔድ የተሻለ ግብ መቺ ይሆናል ተብሎ ስለታመነ ነው፡፡ ደራሲው ካሉት ሁለት ልቦለዶች መካከል (*የተቆለፈበት ቁልፍ* እና *ሌላ ሰው*) ሁለተኛው እንዲመረጥ ያስቻለው ከየተቆለፈበት

ቁልፍ ጋር ሲነፃፀር የቅርብ ጊዜ የህትመት ውጤት መሆኑና በቅድመ ምርምር ወቅት በተደረገ ንባባዊ ዳሰሳ ብዙ ከሰብእና ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን አካቶ በመገኘቱ ጥናቱ ይዟቸው ለተነሳቸው ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥና ለዓላማዎች መሳካት ግብ የሚመታ ነው ተብሎ ስለታመነ ነው፡፡

በመጽሐፉ ውስጥ ከቀረቡት ገፀባህርያትና ይዘቶች መካከል ለዚህ ጥናት ዓላማ መሳካት አስፈላጊ ናቸው ተብለው የሚታሰቡት መረጃዎችም በዓላማ ተኮር የናሙና ዓመራረጥ ስልት ተመርጠዋል፡፡ ይህም የሆነው ሁሉንም የጽሑፉን አካል እንዳለ በትንታኔ ውስጥ ከማቅረብ ይልቅ ይበልጥ የምርምሩን ዓላማ የሚያሳኩትንና መሠረታዊ ጥያቄዎችን የሚመልሱትን መምረጡ ተገቢ ስለሚሆን ነው፡፡ ይህን ለማድረግም ዓላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ስልት ከሌሎች ይልቅ የተሻለ ስለሆነ ነው፡፡ በመሆኑም በይዘት ደረጃ ፍሮይዳዊ የፍካሬ ልቦና ጽንሰ ሀሳብ ጎልቶ የሚታይባቸው የልቦለዱ የትረካ ክፍሎች እየተመረጡ በመረጃ ምንጭነት አገልግለዋል፡፡ በልቦለዱ ካሉት ገፀባህርያት መካከልም ይበልጥ ለልቦለዱ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱና የሰብእና ጉዳይ ጎልቶ የሚታይባቸው እንዲሁም ታሪኩ የሚያቀነቅንላቸው እነሱም ለታሪኩ ሒደት ጉልህ ድርሻ የሚያበረክቱት ተመርጠዋል፡፡

### 3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

በዚህ ጥናት ለትንተና የተመረጡት መረጃዎች የተሰበሰቡት ለጥናት በተመረጠው ረጅም ልቦለድ ላይ ጥልቅ ንባብ (A Close Reading of the Selected Novel) በማካሔድ ነው፡፡ ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የተመረጠውም በመረጃ ምንጭነት የሚያገለግለው መጽሐፍ በመሆኑና መረጃዎችም ከመጽሐፉ እየተመዘዙ የሚቀርቡ በመሆናቸው ነው፡፡

## 3.4. የመረጃ አደረጃጀትና መተንተኛ ስልት

### 3.4.1. የመረጃ አደረጃጀት

የተሰበሰበው መረጃ ለትንታኔ ያመች ዘንድ የገፀባህርያት ሰብእና አቀራረጽ ስልት በሌላ ሰው ረጅም ልቦለድ ውስጥ የሚል ዐቢይ ርእስ ከተሰጠው በኋላ የገፀባህርያት ሰብእና የተቀረጸበትን ስልት መነሻ በማድረግ በአምስት ንዑሳን ርዕሶች እንዲደራጅ ተደርጓል፡፡ ንዑሳን ርዕሶችም ውስጣዊ የአእምሮ መዋቅር ከአካባቢ ጋር በሚኖረው መስተጋብር ሰብእናቸው የተቀረጸ ገፀባህርያት፣ በቤተሰብና በማህበራዊ መስተጋብር ሰብእናቸው የተዋቀረ ገፀባህርያት፣ ከቤተሰብ ተጽእኖ ጋር ተያይዞ ሰብእናቸው የተዋቀረ ገፀባህርያት፣ ከአካባቢና ከማህበረሰብ ጋር በሚኖር

መስተጋብር ሰብእናቸው የተዋቀረ ገፀባህርያትና ውስጣዊ የአእምሮ መዋቅርን መሠረት በማድረግ ሰብእናቸው የተቀረጸ ገፀባህርያት የሚሉ ናቸው፡፡

### 3.4.2. የመረጃ መተንተኛ ስልት

ለዚህ ጥናት በመረጃ መተንተኛነት ጥቅም ላይ የዋለው ጽሑፋዊ ትንታኔ (Text Analysis) ሲሆን ይህም በፍካሬ ልቡናዊ ትወራ መነሻነት ተካሒዷል፡፡ ይህም የተመረጠበት ምክንያት መረጃው አይነታዊ በመሆኑና የመረጃው ባህርይ ብሎም የጥናቱ ዓላማ ከዚህ ስልት ጋር የሰመረ ግንኙነት እንዳለው ስለታመነ ነው፡፡ በመሆኑም በልቦለዱ ውስጥ የቀረቡት ከሰብእና ጋር የተያያዙ ሥነ ልቦናዊ ጉዳዮች ተተንትነዋል፤ ተፈክረዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የገፀባህርያት ሰብእና ውቅር ትንተና በሌላ ሰው ረጅም ልቦለድ ውስጥ

በዚህ ምዕራፍ ስር የልቦለዱ ጭምቀ ታሪክ ከቀረበ በኋላ የተሰበሰበው መረጃ በምዕራፍ ሁለት ላይ በቀረቡት ንድፈ ሀሳባዊና ትወራዊ ማህቀፎች አጋዥነት እየተብራራና እየተተረጎመ ተተንትኗል፡፡

### 4.1. የሌላ ሰው ረጅም ልቦለድ ጭምቀ ታሪክ

*ሌላሠው ከአባቱ ከኮሎኔል ዲንሳና ከእናቱ ከወይዘሮ እታለም በአዲስ አበባ ከተማ ይወለዳል፡፡ ዕድሜው ለትምህርት ሲደርስም በአቅራቢያው ከሚገኝ ትምህርት ቤት ትምህርቱን ይከታተላል፡፡ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቆይታው ሰባተኛ ክፍል ሲደርስ ቤተሰቦቿ የስጋ ደዌ በሽተኛ ከሆኑ ገነት ከምትባል ልጅ ጋር ይተዋወቃል፡፡ ጓደኝነታቸውንም አጠናክረው በሁለቱም ቤተሰቦች ዘንድ እንደ ቤተሰብ አባልነት መታየትና አንድ ላይ ማጥናት ይጀምራሉ፡፡ በተለይ ኮሎኔል ዲንሳ ለገነትና ለእናቷ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡ የገነት እናትም ሌላሠውን እንደልጃቸው ማየት ይጀምራሉ፡፡*

*ገነትና ሌላሠው በትምህርታቸው ጎበዝ ተማሪዎች ሲሆኑ ከክፍልም አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ እየያዙ ተከታትለው ይወጣሉ፡፡ የገነት በትምህርቷ ጎበዝ መሆን ይበልጥ በኮሎኔል ዲንሳ ዘንድ ተወዳጅ እንድትሆን ያደርጋታል፡፡ እነሌላሠው አስረኛ ክፍል ሲደርሱ ኮሎኔል ዲንሳ በስራ ምክንያት ተዛውሮ ወደ አስመራ ይሔዳል፡፡ የሌላሠውና የገነት ቅርርብም ከጓደኝነት ያለፈ እየሆነ ይመጣል፡፡ ይህን የተመለከቱት ገነትን ቀድሞም የማይወዷት የሌላሠው እናት ወይዘሮ እታለም በገነት ላይ ይነሱባታል፡፡ ሁለቱን ለማራራቅ አሜሪካ ከምትኖረው ልጃቸው ጋር በመመካከር ሌላሠው ወደ አሜሪካ መሔድ እንዳለበት ይወስናሉ፡፡ ሌላሠው አስረኛ ክፍልን አጠናቆ ክረምት ላይ የአስራ አንደኛ ክፍል ትምህርቱን ከታላቅ እህቱ ጋር ሆኖ አሜሪካ መቀጠል እንዳለበት ይነገረዋል፡፡ በሀሳቡ ባይስማም አማራጭ ስላልነበረው ወደ አሜሪካ በመሔድ ትምህርቱን ይከታተላል፡፡ በኋላም ዩኒቨርስቲ ገብቶ የአእምሮ ህክምናን በማጥናት ላይ እያለ ከንዋይ ጋር ይተዋወቃል፡፡ ንዋይ የልብ ህክምና ሲያጠና ሌላሠው ደግሞ ሳይካትሪስት ይሆናል፡፡*

*ንዋይ ከአርሴማ ጋር የፍቅር ግንኙነት መስርቶ ለጋብቻ ሲበቃ፣ ሌላሠው ደግሞ በንዋይ ሰርግ ላይ ሚዜ ሆኖ በሔደበት ወቅት ከአርሴማ እህት ከንጹህ ጋር ይተዋወቃል፡፡ ትውውቁ ቀስበቀስ ወደ ፍቅርና ትዳር ይቀየራል፡፡ ከንጹህ ጋር ትዳር መስርተው በመኖር ላይ እያሉ ከፍተኛ የሆነ የአባቱን አደራ የመወጣትና ሀገሩን በሙያው የማገልገል ፍላጎት ያድርበታል፡፡ ይህን ፍላጎቱን ለማሟላትም የተወሰነ ጊዜ አሜሪካ የተወሰነ ጊዜ ደግሞ ኢትዮጵያ እያለ መስራት ይጀምራል፡፡ ጳውሎስ ሆስፒታል ተቀጥሮ በሚሰራበት ወቅትም ከጎንደር ዩኒቨርሲቲ የማስትሬት ዲግሪውን ለመማር ከመጣው ከሲራክ ጋር ይተዋወቃል፡፡ የሆስፒታሉ የረጅም ጊዜ ነርስ ከሆነችው ከሲስተር ዘቢባ ጋርም ወዳጅነትን ይመሰርታል፡፡ ከጥቂት ቀናት በኋላ ደግሞ ከምስጢር ጋር ይተዋወቃል፡፡ መስቀል አደባባይ በሔደበት አጋጣሚ ደግሞ ከሳንቾ (ሰኢድ) ጋር ይተዋወቃል፡፡ ብዙ ጓደኞችን እያፈራ ስራውን በጳውሎስ ሆስፒታል ማከናወኑንም ይቀጥላል፡፡*

*በጳውሎስ ሆስፒታል በመስራት ላይ እያለ ዝናሽ ከምትባል የስጋ ደዌ በሽተኛ ቤተሰብ ካሏት የአእምሮ በሽተኛ ጋር ይተዋወቃል፡፡ ስለዝናሽ ሲያጣራ ዘነበ ወርቅ አካባቢ የምትኖርና የስጋ*

*ደዌ ታማሚ ችግረኛ ቤተሰቦች እንዳሏት ይረዳል። ዘነበ ወርቅና የስጋ ደዌ ታማሚነት ሲነሳ የገነትና የእናቷ ትዝታ ያገረሽበታል። ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ስለገነት ማጠያየቅ ይጀምራል። ለዚህ እንዲረዳውም ከዝናሽ ቤተሰቦች ጋር ይተዋወቃል። ዝናሽንም በሳምንት አንድ ቀን ወደሚሰራበት አማኑኤል እንድትሔድና ተኝታ እንድትታከም ሪፈር ይጽፍላታል።*

*ሌላሠው በጳውሎስ ሆስፒታል ታዋቂና ዝነኛ የአእምሮ ሀኪም እየሆነና ሆስፒታሉም ወደ ላቀ ደረጃ እየተሸጋገረ ይሔዳል። የሆስፒታሉ ነባር ነርስ የሆነችው ሲስተር ዘቢባ በሆስፒታሉ የአጭር ጊዜ ስኬትና የስታፍ አባላት አንድነት ደስተኛ ትሆናለች። ይህንን በማስመልከትም የእራት ግብዣ መርሀ ግብር ታዘጋጃለች። በመርሀ ግብሩ ላይም ሌላሠው ከነ ባለቤቱ፣ ሲራክ፣ ምስጢርና ሳንቾ ይገኛሉ። ይህንን የተመለከተው የሲስተር ዘቢባ ባለቤት አቶ ሲራጅ ለአንድ የህክምና ማዕከል በቂ የሚሆን ባለሙያ እንዳለና ማዕከል መክፈት እንደሚገባቸው ሀሳብ ያቀርባል። በሀሳቡ ላይ ከተወያዩበት በኋላ በድጋሚ በሰፊው ሊያስቡበት ይስማማሉ። ቀድሞውንም ሲመኘው የነበረው ሀሳብ በሌሎች ዘንድ መነሳቱና ደጋፊ ማግኘቱ ሌላሠው ሀሳቡ ሁሉ የሚመኘውን አይነት ክሊኒክ መክፈት ላይ እንዲያተኩር ያስገድደዋል። ከባለቤቱ ጋር በሚገባ ከተመካከሩ በኋላም ክሊኒኩን ይከፍታል። ቀድሞ ሲያደርግ እንደነበረውም አንድ ጊዜ አሜሪካ አንድ ጊዜ ኢትዮጵያ እያለ ስራውን ማከናወን ይጀምራል። ሲስተር ዘቢባ፣ ሲራክ፣ ሳንቾና ምስጢርም የክሊኒኩ ሰራተኞች ይሆናሉ።*

*ከክሊኒኩ ድጋፍ ለማግኘት የተለያዩ የስነ ልቦና ችግር ያለባቸው ታማሚዎች መምጣት ይጀምራሉ። ከእነዚህም መካከል የምስጢር የረጅም ጊዜ አፍቃሪ ማስረሻ አንዱ ሲሆን ማስረሻ ምስጢርን የሁለተኛ ዓመት የዩኒቨርስቲ ተማሪ እያለች ካያት ወዲህ በአፈቀርኩሽ ስም ብዙ ነገሮችን ያደርስባታል። ፈላጊ በመምሰልና ስሙን በመቀየር ምስጢርን ለማግኘት ከምትሰራበት ቦታ ድረስ ይመጣል። ይህንን የሰማው ሌላሠውም የምክር አገልግሎት ይሰጠውና ለተወሰነ ጊዜ አሜሪካ እንደሚሔድና ሲመለስም በቀጠሮው ቀን በድጋሚ ሊገናኙ ይስማማሉ።*

*ማስረሻ፣ ሌላሠው አሜሪካ በሔደበት ወቅት ስምምነቱን በመጣስ ከቀጠሮው ውጭ ክሊኒኩ ይመጣና ከሲራክ ጋር ይገናኛል። ሲራክ ደግሞ ምስጢርን ቢያፈቅራትም ልቧን ማግኘት እየተቸገረ ያለና ሌላሠው ወክሎት በሔደበት ወቅት ከሌላሠው ቢሮ ባገኘው ስለእሱና ስለሌሎች የተመረጡ ታካሚዎችና የስታፍ ሰራተኞች የግል ማስታወሻ ውስጡ ተረብሾና ለበቀል ተዘጋጅቶ የሚጠብቅበት ሰዓት ስለነበር ማስረሻን ድንገት ሲያገኝ የበቀሉ መፈጸሚያ መሳሪያ ለማድረግ ምቹ አጋጣሚ ይፈጠርለታል። ሌላሠው በድጋሚ ወደ አሜሪካ በአስቸኳይ ተጠርቶ በሔደበት ወቅትም ማስረሻን በመጠቀምና ሳንቾን እንዲያጠፋው በማቀነባበር የበቀል እርምጃውን ይጀምራል። የንጹሕን ስልክ ከሌላሠው በመቀበልም የተለያዩ ሀሰተኛ መረጃዎችን በማስተላለፍ ባልና ሚስቶችን ለመለያየት ጥረት ያደርጋል።*

*ሲራክ ሁለቱም የበቀል እርምጃዎች መልሰው ራሱን ቢያገኙትም ለጊዜው ፍሬ ያፈሩለት ይመስለዋል። ማስረሻ ሳንቾን ለመግደል በሔደበት ወቅት ራሱ ለሞት ይዳረጋል። ሳንቾ ነፍስ አጥፍተሀል በሚል ማረሚያ ቤት ይገባል። በቋፍ ላይ የነበረችዋ ንጹህም ከሌላሠው ጋር ለመፋታት በመወሰን ከቀድሞ ጎረቤታቸው ጋር ትዳር ትመሰርታለች። የማስረሻ ቤተሰቦች ደግሞ ክሱን እያሰፉ ሆስፒታሉም እንዲጠየቅላቸው ያደርጋሉ። በዚህም በወቅቱ ሜዲካል ዳይሬክተር ሆኖ የተወከለው ሲራክ ተጠያቂ ይሆናል። ማስረሻን ግድያ እንዲፈጽም ሲያበረታታ እንደነበረም ማስረጃ ይገኝበታል። የአስራ አምስት ዓመት ጽኑ እስራትም ይፈረድበታል። ሳንቾ ደግሞ ምንም ቢሆን ነፍስ በእጅህ ጠፍቷልና በሚል የሶስት ወር እስራት ይበየንበታል። ሲራክ፣ ፍሬ ሊያፈራለት የመሰለው የበቀል አዝመራው ድንገት ይደርቅበታል። ይህንን በቀል*

*የተረዳቸውና በአዲሱ የትዳር ህይወት ደስታን ያጣቸው ንጹሕም ወደቀድሞ ትዳሯ እንዴት መመለስ እንዳለባት በማሰብ ላይ እያለች ሀሳቡ ድንገት በምስጢር በኩል ይደርሳታል። ምስጢርም ሌላሠውና ንጹሕ ተቀራርበው እንዲነጋገሩና ፍቅራቸውን እንዲያድሱ መንገዱን ትከፍታለች። ቀድሞውንም በልባቸው የሚፈላለጉት ጥንዶችም ክሊኒኩን በአዲስ መልኩ አደራጅተው አንድ ላይ ለመኖር ይስማማሉ።*

## 4.2. የገፀባህርያት ሰብእና አቀራረጽ ስልት በሌላ ሰው ረጅም ልቦለድ ውስጥ

በሌላ ሰው ረጅም ልቦለድ ውስጥ ያሉ ገፀባህርያት ሰብእና አንድም ካላቸው ውስጣዊ የሥነ ልቦና አወቃቀር የመነጨ ሁለትም ከቤተሰብ ከጎረቤትና ከአካባቢ የተወረሰና የተገነባ ነው። ገፀባህርያቱ አብዛኛዎቹ በሰብእና መዛባት የሚሰቃዩም ናቸው። ስቃያቸውም ከቤተሰባዊና አካባቢያዊ ጫና የመነጨ ነው። የተመረጡ ገፀባህርያት የሰብእና አቀራረጽም በሚከተለው መልኩ በዝርዝር ቀርቧል።

### 4.2.1. ውስጣዊ የአእምሮ መዋቅር ከአካባቢ ጋር በሚኖረው መስተጋር ሰብእናቸው የተቀረጸ ገፀባህርያት

በዚህ ርዕስ ስር ሰብእናቸው ከውስጣዊ ሥነ ልቦናና ከአካባቢ ጋር በሚኖር መስተጋብር የተቀረጹ ገፀባህርያት የሰብእና አወቃቀር ስልት ተብራርቷል። በዋናነትም የሌላሠውና[4] የንጹሕ ሰብእና አወቃቀር ስልት ከመጽሐፉ እየተመዘዙ በወጡ ማስረጃዎች እየተደገፈ ቀርቧል።

ሌላሠው ለልቦለዱ ርዕስነት ጥቅም ላይ የዋለ ዋናው ገፀባህርይ (Eponymous Character[5]) ነው። ሌላሠው በልቦለዱ ውስጥ በተለይ በታሪኩ የመጀመሪያዎቹ ክፍሎች ላይ ጤናማ ሰብእና ያለው፣ ቅን አሳቢ መልካም አድራጊ ሆኖ ቀርቧል። ለዚህም የስራ ባልደረባዎቹና ተግባሩን ያዩ ሌሎች ሰዎች ምስክርነትን ሲሰጡ ይስተዋላሉ። ወይዘሮ ኤደን ‹‹እንዳንተ አይነት **ሩኅሩኅና ሰውን ሁሉ በኩል ዓይን የሚያይ** … ደግሞም የሚሠራውን የሚያውቅ ሰው ቢኖር ይሄ ሕዝብ አዝሎ የሚዞረውን መከራ ገና ድሮ በጣለ ነበር (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 146) (አጽንኦት ተጨምሯል)›› ሲሉ ምስክርነታቸውን ይሰጣሉ።

---

[4] ሌላሠው የሚለው ቃል በሁለት አይነት መልኩ ተጽፎ ይገኛል። አንደኛው ሌላ በሚለው ቃልና ሠው በሚለው ቃል መካከል ክፍተት የሌለውና ሠው የሚለው ቃል በንጉሡ ‹‹ሠ›› ተጽፏል። ሁለተኛው ደግሞ ሌላ በሚለው ቃልና ሰው በሚለው ቃል መካከል ክፍተት ያለውና ሰው የሚለው ቃል በእሳቱ ‹‹ሰ›› የተጻፈ ነው። በመሆኑም የገፀባህርይውን ስም ለመግለጽ በንጉሡ ‹‹ሠ›› ቃሉን ለመግለጽ ደግሞ በእሳቱ ‹‹ሰ›› የተጻፈው ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል።

[5] የዋና ገፀባህርይው ስም የመጽሐፉ ወይም የትያትሩ ስም ሲሆን ‹‹eponymus character›› ተብሎ ይጠራል።

‹ደህና ዋልሽ ሲስተር … አባክሽ ላስቸግርሽ …› ሲላት፣ በሩን በእጁ እንደ ተደገፈች ዞር ብላ ስታየው ‹ዶክተር ሌላሠው አባላለሁ። ጠዋት ላይ አንድ ህመምተኛዬ ከአማኑኤል ሆስፒታል ወልዳ ነበር። ህፃኗ ትንሽ የመተንፈስ ችግር አጋጥሟት እዚህ ተኝታለች ብለውኝ እሷን ለማየት ነበር› ሲል ፈጠን ብላ

‹ማነው ስሟ?›

‹የናቷ ስም ዝናሽ በድሉ ነው።›

‹እስኪ ልይልህ … እናቷም እዚህ እኛው ጋ ናት ወይስ?› አለች፣ ሌላሠውን ከላይ እስከታች እያጠናች። ብዙ ሐኪሞች ለህመምተኛ ያን ያህል ተጨንቀው እንደዚህ ሲያደርጉ ስለማታይ ትንሽ ገርሟት። (*ሌላ ሰው፣* 2007፣ 184)

ሌላሠው ለህመምተኞች የሚሰጣቸው እንክብካቤ የመልካም ሰብእናውና የደግነቱ ማሳያ ነው። የሰብእና አወቃቀሩም የሱፐር ኢጎ ከፍተኛ ተጽእኖ ያለበት ነው። ሩህሩህነትና ሁሉንም ሰው በእኩል ዐይን ማየት እንዲሁም ለስራው ታማኝ መሆንና ታማሚዎችን መንከባከብ በሞራል ልእልናው ከፍ ካለ ሰው የሚጠበቅ ተግባር ነው። እነዚህ ተግባራት ደግሞ የሱፐር ኢጎ የሰብእና ውቅር ከፍተኛ መሆኑን አመላካቾች ናቸው። የሌላሠው በሞራል ልእልና ከፍ ማለት ሲስተር ዘቢባና ሲራክ ስለ ክሊኒኩ መከፈት በሚያደርጉት ቃለ ምልልስ ላይም ይታያል።

እንደ ነገረኝ ስራው ካለቀ በኋላ የክሊኒኩ ሙሉ ዋጋ ሲታወቅ ነው ያክስዮኑን መጠን ለመወሰን ያሰበው። እኛ ለመግዛት ከፈለግንና ከቻልን እስከ ሃምሳ ፐርሰንትም ብንወስድ ደስ እንደሚለው ነው የነገረኝ። **ምን አይነት ጥሩ ሰው ነው እንዲያው?**

‹**እንደሱ አይነት ኀበዝና ደግ ሰዎች ብዙ የሉም**› አለ፣ ሰዓቱን እያየ። (*ሌላ ሰው፣* 2007፣ 224) (አጽንኦት ተጨምሯል)

ሲራክ ሜዲካል ዳይሬክተር ሆኖ እንዲሰራ በተወከለበት ወቅት ከሳንቾ ጋር በተፈጠረው አለመግባባት ሲነጋገሩ ሳንቾ የሌላሠውን መልካም ሰብእና መላበስ ያነሳል። ‹‹ሁሉ ሰው እኮ ለዶክተር ሌላሠው በደስታ የሚታዘዘው ለምን እንደሆነ ታውቃለህ? እሱ ሁሉንም ሰው ያከብራል፣ የሌላው ሰው ኑሮና ሃሳብ ይገባዋል … ባጭሩ ሰው መሆን ስለሚያውቅበት ነው (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 329)።›› ሌላሠው በስራው ታታሪ ደግና የጥሩ ሰዎችን ሰብእና የተላበሰ ነው። ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ማሰብና መኖርንም የሚያውቅበት ነው።

ሰዎችን መርዳትን፣ መንከባከብን፣ ማገዝንና ነገሮችን ሁሉ በአወንታዊ መልኩ ማየት የሌላሠው የዘወትር ተግባሩ ነው፡፡ መልካም ሰብእናን የተላበሰና ማህበራዊ ተቀባይነት ያለው ታታሪ ሰራተኛ ሆኖ ቀርቧል፡፡ በከፈተው ክሊኒክ ለመረዳት ለሚመጡ ታካሚዎች የሚሰጣቸው ወንድማዊና አባታዊ የሆነ የሥነ ልቦና ምክርም ትልቅ ፈውስ ሲሆናቸው ይስተዋላል፡፡ ሆኖም ውስጣዊ ሰብእናውን ሁሌ ደስተኛና ታታሪ፣ ስራውን አክባሪ፣ ለሰው ቅን አሳቢ በሆነው ሰብእና ሽፍኖ ስለሚታይ ለሚያየው ሰው የጤናማ ሰብእና ባለቤት ይምሰል እንጅ በመጠኑም ቢሆን የሰብእና መዛባት ይስተዋልበታል፡፡ የመልካም ሰብእናው ጎልቶ መታየትም የሰብእና መዛባቱን እንደ ጭንብል ሽፍኖ ማስቀረት አልቻለም፡፡

መልካም ሰብእናን ተላብሶ የነበረው ሌላሠው የተለያዩ የስራ ሒደቶችና ግለሰቦች በሚፈጽሙት ድርጊት ምክንያት ለውጥ ያሳያል፡፡ ደግ፣ ቅን አሳቢና ሩህሩህ የነበረው በቀላሉ የሚናደድና የሚበሳጭ ይሆናል፡፡ ከንጉሕ ጋር የሚያደርገው ቃለ ምልልስም ይህን የሚያሳይ ነው፡፡ ‹‹‹እሺ … ምን አድርግ ነው የምትይኝ? ይሄ ሁሉ ስራ ከተጀመረ በኋላ ጥዬ ልሂድ? ወይስ … ዛሬ ጠዋት ስራ መግባቴና መቅረቴ የሚያመጣው ልዩነት አለ? እንደሱ ከሆነ ደውየላቸው ልቀር እችላለሁ› አለ፣ **በስጨት ባለ ድምጽ** (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 254) (አጽንኦት ተጨምሯል)፡፡››
ሌላሠው የሚያደርገው ክንውንና ሰዎችን ለመርዳትና ሀገሩን ለመጥቀም የሚያከናውነው ተግባር ትዳሩን በማፍረስ ራሱ በሌላ የሰብእና ጣጣ ውስጥ እንዲገባ ምክንያት ሲሆነው ይስተዋላል፡፡ በዚህም መልካም ሰብእናው እየተቀየረ በቀላሉ የሚበሳጭና የሚናደድ ሆኗል፡፡ የአባቱን አደራ ለመፈጸምና የግል ሕይወቱን አጣጥሞ ለመምራት ሲቸገር የሚስተዋልም ነው፡፡ የአባቱን አደራ ለመወጣት ሲያስብ የግል ህይወቱና ትዳሩ ሊበተንበት ይቀርባል፡፡ ትዳሩን ትቶ የአባቱን አደራ ለማሳካት ጥረት ሲያደርግ ልጆቹን ያለ አባት በማስቀረቱ ሌላ የጥፋተኝነት ስሜት ይሰማዋል፡፡ ሁለቱን ሀሳቦች ለማስታረቅ ከባለቤቱ ጋር በተደጋጋሚ የሚያደርገው ምክክርም ፍሬ የማያፈራለት ሆነ፡፡ ይህንን ሁኔታም ከምስጢር ጋር ቃለ ምልልስ በሚያደርጉበት ሁኔታ በራሱ አንደበት ሲናገር ይታያል፡፡

> ዩ ኖው ሚስጥር … አሁን የኔ ህይወት በሚገፋፉና በሚሳሳቡ ኃይለኛ ማግኔቶች መካከል እንዳለች ቁራጭ ብረት ግራና ቀኝ እየተጎተተች ነው፡፡ ለየትኛውም ጥያቄሽ መልስም ሆነ ስሜት የሚሰጥ ማብራሪያ ማቅረብ አልችልም አሁን ለምጫወተው የህይወቴ ሙዚቃ የተጻፈ ኖታና የተስተካከለ ቅኝት የለኝም፡፡ በቃ ምን ልበልሽ … አለ

አይደል … ቀለም ባለቀበት ብዕር የምጽፍ ያህል ነው የሚሰማኝ፡፡ (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 33)

በመጨረሻም ባለቤቱን እንደምንም በማስማማት የአባቱን አደራ ለማሳካትና ህይወቱንም ጎን ለጎነ ለመምራት በሚያደርገው ጥረት ተጠልፎ ሲወድቅ ይስተዋላል፡፡ የሌሎችን ሰብእና ለማከም የሚችል ትልቅና ጠንካራ የሚመስለው ሌላሠው በራሱ ውስብስብ የሰብእና ጥያቄ እየተሞላ መጥቷል፡፡ ይንንም በተመስጦ ልቦና[6] (Stream of Consciousness) በውስጡ ሲያብሰለስል ይታያል፡፡

> የሌላ ሰው ልጅ አተርፋለሁ ብዬ የራሴ ልጆች ሌላ ሰው ሆነው ጠበቁኝ፡፡ የሌላ ሰው ትዳር አስተካክላለሁ ብዬ የኔ ትዳር ራሱ በሌላ ሰው ላይ የምጠላውን አይነት ትዳር ሆኖ ቆየኝ፡፡ ሌላ ሰው አክማለሁ ብዬ ሄጄ ራሴ ሐኪም የሚያስፈልገኝ ህመምተኛ ልሆን ነው፡፡ በሌላ ሰው የማሳብበው ችግር የለም … ስለዚህ ከሌላ ሰው የምጠብቀው መፍትሔም አይኖርም፡፡ ብዙ ለውጥ ማድረግ ይኖርብኛል፡፡ እኔ እምቢ ብል እንኳን ለውጥ ራሱ እንደ ባህር ማዕበል ኑሮዬን ሊገለባብጥ ከቤቴ ገብቶ እያስገመገመ ነው፡፡ (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 376)

ሌላሠው የሌሎችን የተሰበረ ሰብእና ለመጠገን በሚያደርገው ሩጫ የእሱና የቤተሰቡ ሕይወትና ሰብእና መንሻፈፍ እየጀመረው ሲሔድ ይታያል፡፡ ይህም ለምስጢር ስለ ገነት ሲነግራት ይገለጻል፡፡ ‹‹[ምስጢር] ሌላሠው ያልጠበቀችው አይነት ሌላ ሰው ሆኖ ታያት፡፡ **ጠንካራውና ለሰው ሁሉ መልስ ያለው ሳይካትሪስት ሳይሆን ምስኪን በራሱ ጥያቄ የተሞላ ሆኖ አየችው** (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 30) (አጽንኦት ተጨምሯል)፡፡››

በማማከር ተግባሩም ቢሆን መልካም ሰብእናው ሲሸረሸር ይታያል፡፡ ይህንንም ንጹሕና ሌላሠው ከሚያደርጉት ቃለ ምልልስ መረዳት ይቻላል፡፡ ንጹሕና ሌላሠው በክሊኒኩ መከፈት ዙሪያ በሚያደርጉት ውይይት ላይ ሌላሠው፣ ምስጢርና እናቱ ለዚህ ስራ የሚሆን የሚከራይ ቤት እንዳላቸው የነገሩትን ሀሳብ ለንጹሕ ሲያስረዳት ንጹሕ የሌላሠውን አእምሮ የሚነካና ሞራሉን የሚፈትሽበት ሀሳብ ታነሳበታለች፡፡

---

[6] ተመስጦ ልቦና (Stream of Consciousness) *የገፀባህርያትን ህሊናዊና ሥነ ልቦናዊ ገጠመኝ ለማብራራት የሚጠቅም የአተራረክ ዘዴ ነው፡፡*

‹ከትናንት ወዲያ ሚስጥርና እናቷ አናግረውኝ ነበር። አንድ ለኪራይ ክፍት የሆነ በጣም ትልቅ ቤት ወደ አራት ሺህ ካሬ ሜትር ቦታ ያለው ግቢ አላቸው። ክሊኒክ መክፈት ካሰብኩ ልጠቀምበት እንደምችል ነግረውኛል።› አለ፣ ዓይን ዓይኗን እያየ።

‹ከህመምተኞች ጋር ገንዘብ ነክ በሆነ ጉዳይ መነካካቱ ከሕክምና ሥነምግባር አንጻርስ ጥሩ ነው? … እሱንስ አስበህበታል?› አለች፣ ከምስጢር ጋር ያለው ቅርርብ መጨመር አንዳች ደስ የማይል ስሜት እየፈጠረባት። (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 159)

ሌላሠው፣ የምስጢር እናት ከህመማቸው እያገገሙ እንደሆነና ምስጢርም በቅርቡ የስራ ባልደረባው እደምትሆን በመግለጽ ንጹሕንም ህሊናውንም ለመደለል ይሞክራል። ወዲያውኑ ደግሞ ‹‹አንድ ጊዜ ሕመምተኛህ የሆነ ሁሌም ህመምተኛህ ነው›› የሚለው አባባል ሞራሉን ሲፈታተነው ይስተዋላል። ሆኖም ከውስጣዊ ጭንቀቱ ለማምለጥ የራሱን ሥነ ልቦናዊ የጭንቀት መከላለከያ ስልት ይቀምራል። ‹‹በሕመምተኛና በሐኪም መሃል ያለውን የግንኙነትን ድንበር የሚወስነው የሞራል ደንብ ትዝ ሲለው ደግሞ **እናቷ ናቸው እንጂ ምስጢር ህመምተኛዬ አይደለችም ብሎ ራሱን ለማሳመን ሞከረ** (*ሌላ ሰው*፣ 2007 159) (አጽንኦት ተጨምሯል)።›› ይህ ራስን ከጭንቀት የመከላከያ ስልት ጤናማ የሆነ ሰብእናን ለመፍጠር የሚያገለግል አንዱ ስልት ነው። ሌላሠው ክሊኒክ ሊከፍትበት ያሰበው ቤት የምስጢር እንጂ የእናቷ አይደለም ወደሚል የተንሻፈፈ እይታ በመቀየስ ሥነ ልቦናዊ ጭንቀቱን ለማርገብ ጥረት አድርጓል። በዚህም ችግርን ማህበራዊ ተቀባይነት ባለው ተግባር የመተካት (Sublimate የማድረግ) ሒደትን አከናውኗል። ሌላሠው የህክምና ሙያ ሥነ ምግባር ከበሽተኞች ጋር በጥቅም መተሳሰር እንደሌለበት እያወቀ የእነ ወይዘሮ ኤደንን ቤት ለክሊኒክ መክፈቻነት ሲያመቻች ንጹሕ ማድረግ እንደሌለበት ስትነግረው ሥነ ልቦናዊ ጭንቀት ውስጥ ይገባል። ወዲያውኑ ደግሞ ከዚህ ሥነ ልቦናዊ ጭንቀቱ ለማምለጥ ሁኔታውን ምስጢር የክሊኒኩ ባልደረባ እንደምትሆንና ብዙ ህመምተኞችን መፈወስ እንደሚችል ያስባል። ይህም ማህበራዊ ተቀባይነት ባለው ተግባር መተካት (Sublimation) የምንለው የሥነ ልቦናዊ የጭንቀት መከላከያ ዘዴ ተግባራዊ መሆኑን ያመለክታል።

ሌላሠው የልጅነት ፍቅረኛውን ገነትን ደብዛዋን ያጠፋበት የእናቱ ቅስም ሰባሪ ንግግር እንደሆነ ሲገነዘብ ለገነት ካለው ጥልቅ ፍቅር የተነሳ እናቱን የመበቀልና የመቅጣት ፍላጎት አድሮበታል። ይህ ፍላጎቱም ኢንቁ በሆነው አእምሯዊ ክፍሉ ተቀብሮ ከቆየ በኋላ ድንገት ሲታወሰው ቁሳቁሶችን በመደብደብ ሊገለጥ ችሏል። ይህንንም የገነትን እናት ከምስጢር ጋር ለማየት

ሔደው ሲመለሱ ከሚያደርጋቸው ክንውኖች መረዳት ይቻላል፡፡ ‹‹[ሌላሠው] ‹ምን እንደማደርጋት አላቅም አታቲን … ወሽመጤን ነው የበጠሰችው› **ብሎ መሪውን በቡጢ መታውና በረጅሙ ተነፈሰ** (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 393) (አጽንኦት ተጨምሯል)፡፡›› ሌላሠው መሪውን በቡጢ መምታቱ አንድም እናቱን ለቀድሞ ፍቅረኛው ሲል የመበቀል ውስጣዊ ፍላጎት ማሳያ ሲሆን ሁለትም በገነት ላይ የተፈጸመው የእናቱ ድርጊት የፈጠረበትን ጭንቀት በእናቱ ፋንታ የመኪናውን መሪ በመምታት ለመቀነስ የተጠቀመበት ስልት ነው፡፡

ሌላሠው በውስጡ የተፈጠረውን ምስቅልቅል ያለ ስሜት ለማርገብ መሪውን ሲመታ ይስተዋላል፡፡ ‹‹‹… አንዳንዴ ራሴን እወቅሳለሁ› ብሎ መሪውን መታ አደረገ (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 445)፡፡›› ሌላሠው ክሊኒኩን በመክፈቱና የግል ማስታወሻ በመያዙ የተነሳ ራሱን ሲወቅስና ተጠያቂ ሲያደርግ ይስተዋላል፡፡ ይህም የሌላሠው ሰብእና ከክሊኒኩ መከፈት ጋር በተያያዘ አካባቢያዊ ችግርና ሱፐር ኢጎ በሚያይልበት ውስጣዊ የአእምሮ መዋቅር አማካኝነት የተገነባ እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡

ንጹህ ሌላኛዋ በውስጣዊ የአእምሮ መዋቅርና በአካባቢያዊ ሁኔታዎች ቅንጅት ሰብእናዋ የተዋቀረ ገጸ ባሕርይ ስትሆን በከፊል የራስ ወዳድ ሰዎችን ሰብእና (Narcissistic Personality Disorder) ተላብሳ የቀረበች የገሀዱ ዓለም ወኪል ናት፡፡ የዚህ ዓይነት ሰብእናን የሚያዳብሩ ግለሰቦች ራስ ወዳድ፣ የራሳቸውን ጥቅም ብቻ የሚያዩ፣ ከሰው ጋር ሲቀራረቡም ጥቅማቸውን የሚያሰላስሉና ቁጥጥርን የሚያዘወትሩ ናቸው፡፡ ንጹህም የራሷን ፍላጎት ብቻ እየተከተለች የሌላሠውን ድርጊት ሁሉ በአሉታዊ መልኩ ስትመለከት ትታያለች፡፡ ሀገር ውስጥ ገብተን ማህበረሰባችንን እናገልግል በሚል የሚቀርብላትን ጥያቄም የአሜሪካን ምቾትና ድሎት በማስታወስ መስማማት ይቸግራታል፤ ሚስቱ ከሞተችበት ጎረቤታቸው ጋር ግንኙነትን ስትመሰርትም በቢዝነሱ ዓለም የታወቀ በመሆኑ በዚህ ረገድ ሊሰጣት የሚችለውን ጠቀሜታ ብቻ በማሰላሰል ያደረገችው ነው፡፡ ለዚህም ማረጋገጫው በታሪኩ መጨረሻ ላይ ተመልሳ ከሌላሠው ጋር መታረቋ ነው፡፡ በተጨማሪም ንጹህ በተቻላት አቅም ሁሉ የትዳር አጋሯን ለመቆጣጠር ጥረት ታደርጋለች፡፡ ሆኖም የዚህ አይነት የሰብእና መዛባት ችግር የሚስተዋልባቸው ሰዎች እንደሚያደርጉት ሁሉ ይህንን ሰብእናዋን መልካም በሚመስል የሰብእና ጭንብል ስትሸፍን ትታያለች፡፡ ከራስ ወዳድ ሰዎች መካከልም አንዳንዶች ባሕርያቸውን በግልጽና በኩራት ማሳወቅ ሲፈልጉ አንዳንዶች ደግሞ ሆን ብለውና አስበውበት ለመደበቅ ጥረት ያደርጋሉ፡፡

ንጹህ ከሌላሠው ጋር ስትኮራረፍም ሆነ ሌላሠው በሌለበት ሰዓት ትራሷን አቅፋ ስትተኛ በተደጋጋሚ ትታያለች፡፡ ትራሷን አቅፋ መተኛቷ አንድም ኢንቁው አእምሯዊ ፍላጎቷ ሌላ ወንድን በምናቧ እንድታስብ እያስገደዳት ነው፡፡ ይህም በኋላ ሚስቱ ከሞተችበት ጓደኛቸው ጋር በመሰረተችው የፍቅር ግንኙነት ንቁ ሆኖ ሊረጋገጥ ችሏል፡፡ ሁለትም ወንዶችን በስር የማድረግ ድብቅ ፍላጎቷን በእንቅልፍ አማካኝነት ለመግለጽ እየተገለገለች ነው ማለት ይቻላል፡፡ ‹‹ንጹሕ ትራሱን እንዳቀፈች በደረቷ ጧ ብላ ተኝታለች፡፡ … ተጋጭተው የተኳረፉ ቀን እርሱ በጀርባው እጁን ማጅራቱ ስር አድርጎ እሷም በደረቷ ትራሷን አቅፋ ይተኛሉ (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 55)፡፡››

ንጹሕ በተለያዩ ትእምርታዊ ጉዳዮች አማካኝነት ሰብእናዋን ታንጸባርቃለች፡፡ በተለያዩ ቁሳቁሶች ላይ አካላዊ ቅጣት ስትፈጽም ትታያለች፡፡ ይህም አንድም ሌላሠውን የመበቀልና በቁጥጥሯ ስር የማድረግ ፍላጎቷን ለመግለጽ ሁለትም ትዳራቸው በመፍረሱ ምክንያት የተፈጠረባትን ውስጣዊ ሥነ ልቦናዊ ጭንቀት ለመግለጽ እና/ወይም ለማስታገስ የተከናወነ ነው፡፡ ‹‹ካናደዳት በላይ መልሶ አሳዘናት፡፡ እንደገና ደግሞ ይበልጥ አናደዳት፡፡ ‹የራሱ ጉዳይ ነው … ዋጋው ነው …› ብላ፣ ሶፋውን እጇን እስኪደክማት በቡጢ ነረተችው (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 372)፡፡››

ሌላሠው ደግሞ በበኩሉ ከንጹሕ ተለይቶ ሲሔድ የመኪናውን መሪ ይነርተው ጀመር፡፡ ከውስጣዊ ሥነ ልቦናዊ የጭንቀት መከላከያ ዘዴዎች መካከልም ስሜትን ለሌላ አካል ማስተላለፍን (Displacement) ተግባራዊ ሲያደርግ የሚያመለክት ነው፡፡ በአንድ ችግር ውስጣችን ሲታመም ያንን ችግር የፈጠረውን አካል የመቅጣቱ ሞራልም ይሁን አቅም ሳይኖረን ወይም በጉልበታችን ለመቆጣጠር የማንችለው ሲሆን በሌላ አካል ላይ አጸፋውን የምንመልስበትን ሒደት የሚመለከት ነው ችግርን በሌላ ችግር መተካት (Displacement)፡፡ ንጹሕና ሌላሠውም ይህንን ሲያደርጉ ይስተዋላሉ፡፡ አንዳቸው በአንዳቸው ላይ አካላዊ ቅጣት ለመፈጸም ሞራላቸው ስላልፈቀደላቸው ንጹሕ ሶፋውን ሌላሠው ደግሞ የመኪናውን መሪ በመደብደብ ውስጣዊ ጭንቀታቸውን ለማርገብ ሞክረዋል፡፡ ለአካላዊ ግጭት እንዳይጋበዙ ሲከላከል የቆየውም ውስጣዊ የሰብእና መዋቅራቸው ሱፐር ኢጎ በማሸነፉ ነው፡፡ በሁለቱ ጥንዶች መካከል የተፈጠረው የሀሳብ ልዩነት ወደ አካላዊ ግጭት እንዳይቀየር ሱፐር ኢጎ ከፍተኛውን ድርሻ ሲወስድ ይታያል፡፡ ተግባሩንም በኢድ ፈጻሚነት በሥነ ልቦናዊ የጭንቀት መከላከያ ስልቶች እንዲገለጽ አድርጓል፡፡

### 4.2.2. በቤተሰብና በማህበራዊ መስተጋብር ሰብእናቸው የተዋቀረ ገፀባህርያት

በዚህ ርዕስ ስር ሰብእናቸው ከቤተሰብና ከማህበረሰብ ጋር በሚኖር መስተጋብር የተቀረጸ ገፀባህርያት ሰብእና በዝርዝር ቀርቧል፡፡ ይህንን አይነት የሰብእና አወቃቀር ይዘው የሚገኙትም ምስጢር፣ የአስራ ሦስት ዓመቱ ልጅና ናቸው፡፡

ምስጢር ከርቀት ለሚያያት ሳቂታ፣ ፍልቅልቅ፣ ደስተኛና ያለጨዋታ ምንም የማታውቅ ትመስላለች፡፡ ቀረብ ብሎ ለሚያስተውላት ግን በድርብርብ የማንነት ቀውስ የተሞላች ብዙ አስከፊ ሁኔታዎችን በደስተኛነት ጭንብል አፍና የያዘች ናት፡፡ ሌላ ሰው ላይ ቢደርስ ሊሸከመው የማይችል መከራ ተሸክማ የምትኖር ናት፡፡ ይህንንም እናቷ (አሳዳጊዋ) ወይዘሮ ኤደን ሌላሠው ጋ ለህክምና በሔዱ ጊዜ ሲናገሩ ይደመጣሉ፡፡ ወይዘሮ ኤደን ልጃቸው አንድ እሷ ብቻ እንደሆነችና የተባረከች እንደሆነች ይናገራሉ፡፡ ሆኖም በብዙ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ እንዳለፈችም አልደበቁም፡፡ ሌላሠው ወይዘሮ ኤደንን ‹‹እርሷ ብቻ ናት ወይስ ሌሎችም ልጆች አለዎ?›› የሚል ጥያቄ ሲያቀርብላቸው ‹‹አይ እሷው ናት፡፡ እንዴት አይነት የተባረከች ልጅ መሰለችህ፡፡ ለሰው አዛኝ፣ በዛ ላይ ስማርት የሆነች ልጅ ናት (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 79)፡፡›› በማለት የምስጢርን መልካም ሰብእና ሲነግሩን ከቆዩ በኋላ በዚሁ ሰብእናዋ ተሸፍኖ የሚኖረውን ማንነቷን ደግሞ አባቷ ታመው አልጋ ላይ መዋል በጀመሩበት ወቅት ልጃቸው ስቃያቸውን አይታ ይቅር እንድትላቸው ሲማጸኗት ከምንም እንዳልቆጠረቻቸውና ‹‹አንተ አውሬ ነህና ለአንተ ይቅርታ አይገባህም (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 82)›› ብላው እንደሔደች ይተርኩልናል፡፡ ፈርጀ ብዙ ማንነት ይዛ እንደምትንቀሳቀስም ‹‹ላይዋን ስታየው ገርና ሳቂታ ትመስልሃለች እንጂ ውስጧ ያልበረደ ቁጣ አዝላ ነው የምትዞረው›› ብለው በሀዘኔታ ይተርካሉ፡፡

ምስጢር ይህንን ድርብርብ ማንነቷን የወረሰችው ከቤተሰብ ነው፡፡ ቤተሰቦቿ በተለይ አባቷ (አሳዳጊዋ) ያደረሰባት የህሊና ጠባሳ በጣም የከፋ ነው፡፡ አባት ተብሎ በሚታወቅ የቤተሰብ አባል ሊፈጸም የማይችል ድርጊት ሁሉ ተፈጽሞባታል፡፡ ይህንን ሁሉ የነፍስ ስቃይና የህሊና ስብራት በኢንቂው የአእምሮዋ ጓዳ እንዲቀመጥ ብታደርገውም በአንዳንድ አስገዳጅ ሁኔታዎች አማካኝነት ጎልቶ ይወጣል፡፡ ምስጢር የአባቷን ፎቶግራፍ በፊቱ የምትደፋው አባቷ በህይወት ሳሉ ያሳደሩባትን ጠባሳ ለመወጣት ነው፡፡ ይህንም የምታደርገውም ኢንቁ በሆነው የአእምሮዋ ክፍል ታምቆ የቆየውን አባቷ የፈጸሙባት ግፍ አጸፋ ለመመለስ ነው፡፡ ምክንያቱም አባቷ ያደረሱባት ጫና ይህንን ሰብእና እንድትይዝ ያስገድዳታልና ነው፡፡

ድንገት ብድግ አለችና ከቴሌቭዥኑ አንጻር ከፍ ብሎ የተቀመጠውን ትልቅ **የአባቷን ፎቶ ግራፍ አንስታ በፊቱ ደፍታ ከታችኛው መደርደሪያ ላይ ስታስቀምጠው**

‹እንዴ! ምነው ልጄ፣ እሱ ደግሞ ምን አደረገሽ? ለዛሬ አንኳን ይሁን እስኪ› አሉ እያመነቱ

ወደ እርሳቸው ዞር ብላ ቆጣ ባለ ድምጽ፣ **‹ይበቃዋል … ይበቃዋል፡፡ በህይወት እያለ ያፈጠጠብን ይበቃዋል፡፡ ቤቱ ህያዋን የሚኖሩበት እንጂ ሙታን በመንፈሳቸው የሚገዙበት አይደለም፡፡ እንዲያውም ነገ የሆነ ቦታ ካላስገባሽው ወደ ጓሮ ሊጣልም ይችላል›** አለች ስሜቷ እየጋለ፡፡ (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 68) (አጽንኦት ተጨምሯል)

ምስጢር ይህን የምታደርገው ቤተሰቡ ከአስመራ ከተመለሰ ወዲህ አባቷ ባመጡት የባሕርይ ለውጥ አማካኝነት ኢሰብአዊ ድርጊት ስለፈጸሙባት ነው፡፡ አባቷ በእድሜ ዘመናቸው ሁሉ የለፉበት ሀብትና ንብረት በኢትዮጵያና በኤርትራ ጦርነት ወቅት አስመራ በመቅረቱ የተነሳ ታላቅ የሰብእና መቃወስ ገጠማቸው፡፡ የአባወራው የሰብእና መዛባትም ለቤተሰቡ አባል በሙሉ ለሰብእናቸው መዛባት መንስኤ ሆነ፡፡ የምስጢር አባት ከአስመራ ከተመለሰ ወዲህ በተደጋጋሚ መጠጣትና ጥንብዝ ብሎ እየሰከረ ሌሊት ላይ ይገባና በእናቷ ላይ ብዙ ስቃይ ያደርስባት ጀመር፡፡ ቆይቶ ደግሞ ስቃዩ ከእናቷ ወደ እሷ ተሸጋገረ፡፡ አባት በልጁ ላይ ይፈጽመዋል ተብሎ የማይታሰብ ድርጊት ሁሉ ይፈጽምባት ጀመር፡፡ የእናቷን ስቃይ የተጋራች የመሰላት ምስጢርም በውስጧ ሀሳቡን እያወጣችና እያወረደች ለራሷ ብቻ አፍና ለመቆየት ተገደደች፡፡ ይህም ወንዶችን ጨካኝ አድርጋ እንድታስብና ህይወቷን በሙሉ በሽብር፣ በፍርሀትና በጥርጣሬ እየተመለከተች እንዲሁም ራሷን እንዳቆሸሸች በማሳብ ራሷን በመውቀስ ለመግፋት እንድትገደድ አድርጓታል፡፡ ይህንን የደረሰባትን የህሊና ስብራት ለሌላሠው በሚከተለው መልኩ ስትተርክለት ይስተዋላል፡፡

‹ካስመራ እስክንመጣ ድረስ በቃ ባቢ ጥሩ አባት ነበር፡፡ … እዚህ ከመጣን በኋላ ቀስ በቀስ ጸባዩ እየተለወጠ በጣም ሰካራምና ቁጡ ሰው ሆነ፡፡ ማሚን መከራዋን ሲያሳያት … ምን ላድርግ እኔ … ልጅ ስለሆንኩ በምንም መንገድ ልረዳት አልችልም ነበር፡፡ በኋላ ላይማ ስድቡና ድብድቡ እየባሰ መጣ፡፡ … የሚመጣው ደግሞ ሌሊት ስምንት ሰአት ምናምን ነው፡፡›

‹አንድ ቀን ጥንብዝ ብሎ በቀጥታ መጥቶ እኔ ጋ መጥቶ ጸጥ ብሎ ተኛ፡፡ በቃ ማሚን ያሳረፍኳት ስለመሰለኝ ደስ አለኝ፡፡ ከዛ በኋላ ከኔ ጋር መተኛት ልማዱ ሆነ፡፡›

‹ያኔ አስራ ሁለት አመቴ አካባቢ ነበር መሰለኝ፡፡ ከዛ የማይሆን ቦታ ሲነካካኝና ሲተሻሸኝ እየቀፈፈኝ ተው ስለው … አንዴ ያለቅሳል ወይ ደግሞ ማሚን እንደሚገድላትና ራሱንም እንደሚያጠፋ ሲነግረኝ እየፈራሁ ዝም ማለት ጀመርኩ፡፡ አንዳንድ ቀን ራቁቱን አልጋ ውስጥ ይገባና በቃ ምን ልበልህ … በመሸ ቁጥር ስቃይ ሆነ፡፡ ስቃዩ ጋብ ሲልላት መሰለኝ ማሚም ምንም እንዳልሆነ እሷም ዝም አለች፡፡ ትወቅ አትወቅ ርግጠኛ አልነበርኩም፡፡ ለሷ እንዳትጨነቅ ያገዝኳት ስለመሰለኝ መንገሩንም ፈራሁ፡፡›.

‹የተፈጠረውን ሰላም የሚበጠብጠው ወይም የሚፋቱብኝ ስለሚመስለኝ ዝምታን መረጥኩ፡፡ በቃ ለማን ልናገር … ነጋ ጠባ ራሴን መውቀስ … ቆሻሻ እደነካው እቃ ራሴን መጸየፍ ጀመርኩ፡፡ (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 271)

አንድ ቀን ድብልቅልቅ ያለ ጥል ሲጣሉ እናቷ ቤቱን ትታ ምስጢርን ይዛ ልትሔድ ስትል እንደከለከላት፣ ምስጢርንም ከሔድሽ ራሴን አጠፋለሁ በማለት አስፈራርቶ እንድትቀር ካደረጋት በኋላ በሁለተኛው ቀን ሰክሮ መጥቶ በግድ እንደደፈራት በሀዘን ተውጣ በእንባ ታጅባ ትተርክለታለች፡፡ ይህ ድርጊትም ወንዶችን ለማመንም ሆነ ለመከልከል እንዳትችል አድርጓታል፡፡ ወንዶችን ለማመን ስታስብ አባቷ የፈጸሙባት ኢሰብኣዊ ድርጊት ይታሰባታል፡፡ ለመከልከልም ስታስብ የአባቷ ጭካኔና ማስፈራሪያ ትዝ ይላታል፡፡ በመሆኑም ዝብርቅርቅ ያለውን ሰብእናዋን በተግባቢዋና ደስተኛዋ ምስጢር ጭንብል ይዛ ለመቀጠል ተገዳለች፡፡

ምስጢር በተደጋጋሚ በአፈቀርኩሽ ስም በተለያዩ አካላት ጉዳት ሲደርስባትም ትስተዋላለች፡፡ ከጥፊ እስከ እገድልሻለሁ የሚል ማስፈራሪያ ይደርስባታል፡፡ በተለይ ከሳንቾ ጋር እንደምትቀራረብ የተገነዘበውና የሁለተኛ ዓመት የዩኒቨርሲቲ ትምህርቷን ከምትከታተልበት ጊዜ ጀምሮ ዘወትር እየተከታተለ የሚስፈራራት ማስረሻ የሳንቾን መኪና ጎማ አስተንፍሶ ተጨማሪ የማስፈራሪያ መልዕክት በወረቀት እንዲደርሰው ያደርጋል፡፡ ሳንቾም ጉዳዩን ለምስጢር ከነገራት በኋላ መኪናውን እንዲያሰሩና ጉዳዩን በጋራ ለመከታተል ይመካከራሉ፡፡ ተገናኝተው በጉዳዩ ላይ እያወሩ በነበረበት ወቅትም ምስጢር በተደጋጋሚ ስለደረሱባት ሁኔታዎች ሁሉ እያነሳች ለሳንቾ አጋራችው፡፡ በዚህ መሀልም ‹‹‹ምን ማግኔት እላዬ ላይ እንዳለ አላውቅም …በሽተኛ በሽተኛውን የሚስብ› ብላ፣ በንዴት የተደገፈችውን ዛፍ በካልቾ አቀመሰችው (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 244)፡፡››

ምስጢር ያለፈ ታሪኳንና አሁን እየደረሰባት ያለውን ችግር ባገኘችው አጋጣሚ ለመበቀል የምታስብ ትመስላለች፡፡ ለዚህም ነው ተደግፋው የቆመችውን ዛፍ ለመምታት ጥረት የምታደርገው፡፡ ይህ በኢንቂው የአእምሮ ክፍል ታምቆ የሚኖረው የበቀል ፍላጎትም በተለያዩ ሁኔታዎች ይንጸባረቃል፡፡ በውስጥ የሚኖረውን ጭንቀት ለማስታገስም ችግርን በሌላ ችግር መተካት ይጀመራል፡፡ ምስጢርም ዛፉን ለመምታት የበቃችው በአካል ማስረሻን ለመበቀል ስላልቻለችና ዛፉን በማስረሻ በመመሰል ነው፡፡ ይህ  የምስጢርና የዛፍ ትዕይንት ሌላ ተምሳሌታዊ ውክልናም አለው፡፡ ይኸውም ግንዱ ምስጢርን የሚያስቸግሯት አካላት ተምሳሌት ነው፡፡ ግንድ ሲገፉት እንደሚከብድ ሲመቱት ራስን እንጂ ተመችውን እንደማያመው ሁሉ በተለይ ማስረሻ እንደማትጋፋው ተራራ ሆኖ የተደቀነባት እንደሆነ የሚያመላክት ትዕምርታዊ ውክልናም ሊሆን ይችላል፡፡

ማስረሻ የሳንቾን ጎማ ማስተንፈሱ አልበቃው ብሎ ዛቻና ማስፈራሪያ የተሞላበት ደብዳቤ ጽፎ ለምስጢር እንዲደርሳት ያደርጋል፡፡ የደብዳቤው ይዘትም ማንም ይሁን ምን ምስጢርን ከእሱ የመነጠል አቅም እንደሌለውና በፈለገው ጊዜ የግሉ ሊያደርጋት እደሚችል የሚገልጽ ነው፡፡ ምስጢርም በደረቀ ሌሊት ደብዳቤውን ከዘበኛቸው ተቀብላ ታነባለች፡፡ በፍርሀት ተዘፍቃ ሁሉ ነገር እንደተምታታባት ጋደም ባለችበት እንቅልፍ ያሸልባታል፡፡ ወዲያውኑ በውስጧ ያለው ፍርሀት አይሎ በህልሟ ማስረሻ በአንዲት አዲስ ተቀጣሪ የቤት ሰራተኛቸው አማካኝነት ለጥበቃውና እናቷን ጨምሮ በቤት ውስጥ ላሉት ሰዎች ሁሉ የእንቅልፍ መድሀኒት እንዲሰጣቸው አድርጎ ወደ መኝታ ክፍሏ ገብቶ ይዟት ይወጣና ወደ ቤቱ ይወስዳታል፡፡ ከዚያም በጭስ ጥቁር ካለች ቤት ሻማ አብርቶ ይቆልፍባታል፡፡ ከቆይታ በኋላ ፋኖስ እያበራ ይመጣና ምስጢር ጋ ሊደርስ ሲል የፋኖሱን መብራት ያጠፋል፡፡ በዚሁ ቅጽበት ምስጢርም በአቅራቢያዋ የሚገኘውን ሻማ ታጠፋለች (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 246 - 250) ፡፡ እነዚህ በህልም አማካኝነት የተከሰቱ ትዕይንቶች የተለያዩ ተምሳሌቶችን ወክለው የቀረቡ ናቸው፡፡

ቀድሞ ነገር ምስጢር እንደዚህ አይነት አስፈሪ ሕልም ማየቷ ከሁለተኛ ዓመት ጀምሮ እየተከታተለ የሚያሰቃያት ማስረሻ የፈጠረባት ጭንቀት ነው፡፡ በህልሟ የሚታዩት ትዕይንቶችም የመኝታ ቤት መስኮቷ ክፍት መሆኑ በእውኗ ስታየው የነበረ እና እረስታ ሳትዘጋው ስለተኛች ሲሆን ማስረሻ ከቤቱ ወስዶ በጭስ በጠቆረ ክፍል ውስጥ እንድትቀመጥ ማድረጉ የምስጢር ህይወት በጽልመት የተሞላ መሆኑን አመላካች ነው፡፡ ገና ከልጅነት ጀምራ እናቷን በሞት ተነጥቃ በወይዘሮ ኤደን አማካኝነት የማደግን እድል ብታገኝም ገና ለአቅመ

ሔዋን ሳትደርስ የተለያዩ መከራዎች ይፈራረቁባታል፡፡ ‹‹[ማስረሻ] ወደ መደርደሪያው ተጠግቶ ፋኖሱን ለማጥፋት ሲታገል የመውጫ በሩን አቅጣጫ በጥንቃቄ ለማየት ሞከረች፡፡ ልክ ፋኖሱን ሲያጠፋው አሷም ሻማውን አጠፋችው (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 250)፡፡›› ማስረሻ ይዞት የሚመጣውን ፋኖስ ማጥፋቱ ለምስጢር እንደብርሀን ሰጭ የምትመካበትን ሳንቾን እንደዚህ ነው ብርሀንሽን የማጠፋው በሚል ትዕይንት ሲያሳያት ነው፡፡ ሆኖም ምስጢር ሻማውን ስታጠፋው ማስረሻ ፋኖሱን መልሶ የማብራቱ ምሳሌ በሳንቾ ላይ የሚያደርገውን የከሸፈ የግድያ ሙከራ የሚያሳይ ነው፡፡ ምስጢር ሻማውን ማጥፋቷ እና እንደገና አለማያያዟ ደግሞ በፍቅሯ እየተቃጠለና እየነደደ የሚኖረው ማስረሻ በሞት ሊቀጠፍ እንደሚችል አመላካች ነው፡፡ ምስጢር ማስረሻና መሰሎቹ እንዲሁም አባቷ በየወቅቱ የተለያዩ ጉዳቶችን አድርሰውባታል፡፡ ሆኖም የሚደርስባትን በደል ሁሉ በኢንቁው የአእምሮ ጓዳ ውስጥ አርቃ በማስቀመጥ ጤናማ መስላ ትታያለች፡፡ በመሆኑም የምስጢር ሰብእና የቤተሰብና የአካባቢ መስተጋብር ውጤት ነው፡፡

የአስራ ሦስት ዓመቱ ገፀባህርይም በቤተሰብና በማህበራዊ መስተጋብር ሰብእናው የተዋቀረ ገፀባህርይ ነው፡፡ የአስራ ሶስት ዓመቱ ህመምተኛ ከእናቱ ጋር ሌላሠው ጋ ለህክምና ቢመጣም ህክምናውን ሳያገኝ እናቱን ገፍትሮ በመጣል ይሔዳል፡፡ እናቱም የእናትነት አቅም በማጣቷ ልጆቿን ለሰብእና መዛባት የዳረገች እየመሰላት ራሷን ስትወቅስ ይስተዋላል፡፡ ሆኖም ልጆቹ ለያዙት ሰብእና መከሰት ዋናው ምክንያት በአግባቡ በተሟላ ቤተሰብ አለማደጋቸው ነው፡፡ የተሟላ ሲባልም አባታቸው ገና በህጻንነታቸው ትቷቸው ወደ አሜሪካ ስለሔደ እናት ብቻዋን ቤተሰቡን የማስተዳደር ኃላፊነት ተሸክማለች፡፡ ልጆችን ያለ አባት ለማሳደግም ቢሆን ለመሠረታዊ ፍላጎት ማሟያነት የሚሆን ነገር መስራት ስለነበረባት ልጆቹን ትታ በስራ መጠመድ ነበረባት፡፡ ሞዴል የሚሆናቸውና በቅርብ የሚንከባከባቸው ያጡት ሕጻናትም የሚያዩትን የተዛባ ሰብእና ተግባራዊ ለማድረግ መጣር ጀመሩ፡፡ በመሆኑም አንደኛው በሌብነት ተሰማርቶ ቆይቶ ድንገት ሰው በመግደል ወንጀል ለመታሰር ሲበቃ አንደኛው ደግሞ የደረሰበት እንኳ አይታወቅም፡፡ ከእናቱ ጋር ያለው የመጨረሻው ልጅም የተለያዩ የወንጀለኛነት ድርጊቶችን ሲፈጽም ይስተዋላል፡፡ ሌብነት፣ አስገድዶ መድፈርና እንስሳትን መግደል ጀምሯል፡፡ ይህንንም እናታቸው ከሌላሠው ጋር ከምታደርገው ቃለ ምልልስ መረዳት ይቻላል፡፡ ‹‹ትልቁማ … ውይ ሰው እንዳይመስልህ … ከይሲ ዲያቢሎስ ራሱ ቆሞ የሚሄድ ነው የሚመስልህ፡፡ ሰው ቤት ገብቶ ሲበረብር፣ ባለቤትዬው ነቅተው ተያይዘው ሲታገሉ … ሕይወታቸው እጁ ላይ ጠፋ፡፡ መካከለኛው ብን ብሎ ከጠፋ አመት አለፈው (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 351)፡፡›› የታናሹን

አደገኛነትና የሰብእና መቃወስ ደግሞ ከእናቱ ጋር በክሊኒኩ ውስጥ ከሚፈጥሩት አለመግባባትና ግርግር መረዳት ይቻላል፡፡

> ‹‹የቤቱን እቃ ሸጠህ ጨረስከው … ዞር ካልኩልህ ሁሉንም ነገር ዞር ነው … እም … ሰፈር ውስጥ ባንተ ሌብነትና ተንኮል ያልተማረረ ሰው አለ? ስትፈልግ አምሽተህ … ደስ ካለህ ደግሞ አድረህ ትመጣለህ፡፡ ሌላው ቀርቶ የማይናገሩትን የሰፈሩን ውሾችና ድመቶች አንቀህ … ድብድበህ ትገድላለህ …
>
> ባለፈው አንዲት … አንድ ፍሪት የጎረቤት ልጅ ቤት አስገብቶ ሊደፍር ሲል ደርሼ ያስጣልኩት እኔ ነኝ … አሁንማ ለራሴም ሕይወት ያስፈራኛል፡፡ ገንዘብ አምጪ ነው … የለኝም ካልኩ … ጦርነት ነው … ባለፈው በሩን እጄ ላይ ዘግቶብኝ ሲሔድ ይሄው ጣቴ ተቆረጠ … (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 349)

ልጁ ይህን ድርጊት ለመስራት የሚነሳሳው ከውስጣዊ ስነ ልቦናዊ የሰብእና አወቃቀር የተነሳም ሊሆን ይችላል፡፡ ሁሉም የሚፈጽማቸው ተግባራት ግብታዊነት የሚታይባቸው የኢድ ፍላጎቶች ናቸው፡፡ የኢድ ፍላጎት ሲያይልና የኢጎና ሱፐር ኢጎ ድርሻ ውስን ሲሆን በራስ ላይ የሚደርሰውን ማህበራዊ ውግዘት አለማስተዋልና ለማህበራዊ ህጎችና ደንቦች አለመገዛት ይፈጠራል፡፡ ኢጎ በምክንያታዊነት የሚያምንና ለራሱ የሚጨነቅ ባሕርይን ሲያሳይ ሱፐር ኢጎ ደግሞ ለሞራልና ለማህበራዊ ህግና ደንቦች መጨነቅን ያበዛል፡፡ ሌብነት አስገድዶ መድፈርና እንስሳትን መግደል ከኢጎ የሰብእና ውቅር አንፃር በራስ ላይ ብዙ መዘዝ ስለሚያመጣ ለመተግበር ይከብዳል፡፡ ከሱፐርኢጎ የሰብእና ውቅር አንፃር ደግሞ ሞራላዊ ወቀሳንና ማህበራዊ ውግዘትን ስለሚያስከትል ለተግባር አይጋበዝም፡፡ በመሆኑም በኢድ የሰብእና ውቅር አማካይነት የተፈጠረ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ይህ ልጅ ይህን የተወላገደ ሰብእና ሊይዝ የቻለው አባቱ ባለመኖሩና ወንድሞቹም የሱን ተመሳሳይ የሆነ ሰብእና ተላብሰው በማየቱ ጥሩ ሞዴል ሊሆነው ሚችለውን አካል ባለማግኘቱ ነው፡፡ ሌብነቱ አንድም ከወንድሞቹ የወረሰው ሊሆን ሲችል ሁለትም የሚፈልገውን ነገር በቤቱ ውስጥ ማግኘት ባለመቻሉ ባገኘው አጋጣሚ የኢድ ፍላጎቱን ለማርካት ሊሆን ይችላል፡፡ አስገድዶ የመድፈር ሁኔታውም ከሚያየው ፊልምና ከፈጠረበት ተጽእኖ ጋር ተያይዞ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህንንም የሚያረጋግጥልን የሰባት ዓመቷን የጎረቤት ልጅ ፊልም እያየ ለመድፈር የሚያደርገው ሙከራ ነው፡፡ ይህንንም እናቱ ከሌላሠው ጋር በምታደርገው ምልልስ ‹‹ባለፈው

እቃ ረስቼ ከስራ ቦታ ተመልሼ ቤተ ስገባ … የሆነ የብልግና ቪዲዮ ከፍቶ … አንዲት ከኛ ቤት የማትጠፋ የሰባት አመት የጎረቤት ልጅ አለች … እጅና እግሯን ጠፍሮ … እዛ ቪዲዮው ላይ የሚያየውን ሊያደርግ ይሁን አላውቅም … እሷ ትጮሃለች … ደርሼ አስጣልኳት … (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 351)›› በማለት ትተርካለች፡፡

እንስሳትን መግደል መጀመሩም ወደ ፊት በጣም ከፍተኛ የሆኑ የወንጀለኛ ድርጊቶችን ከመፈጸም ወደ ኋላ እንደማይል የሚያመለክት ነው፡፡ ይህም ምናልባት በቪዲዮ ከሚያየው ነገር የተማረው ሊሆን ይችላል፡፡ ምናልባት ከእናቱም የተወረሰ ሊሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም እናቱም ለድብድብ የምትጋበዝ እንደሆነች በክሊኒኩ ውስጥ ሳይቀር ልጇን በጥፊ ስትወለውለው ትታያለችና፡፡

እናቱም ይህን ባሕርይዋን የወረሰችው ኃይለኛ ከነበረችው እናቷ ነው፡፡ ሌላሠው አስተዳደጓን በሚመለከት ለጠየቃት ጥያቄ ‹‹ከእናቴ የባሰኩ ሞገደኛ ነበርኩ ልጅ ሆኜ … እሷ ነጭ ነው ካለች እኔ ጥቁር ነበር የምለው፡፡ ያገሩን ዱላ እኔ ላይ ነበር የጨረሰችው (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 351)›› ስትል ትመልሳለች፡፡ የተደባዳቢነት ባሕርይዋን ከእናቷ የወረሰችው ነው ማለትም ይቻላል፡፡ ይኸው ባህርይ ወደ ልጆች ተላልፎ ሲበዛ ሞገደኛና ተደባዳቢ ለመሆን በቅተዋል፡፡ ታላላቅ የወንጀለኛ ድርጊቶችንም መፈጸም ጀምረዋል፡፡

ዳርጌ የጥገኝነት ሰብእናን (Dependent Personality Disorder) ያዳበረ ገጸ ባሕርይ ነው፡፡ ለዚህ የዳረገውም በልጅነቱ ወላጆችን ማጣቱና የሚኖርበት አካባቢ ማህበረሰብ የሚሰጠው ግምት ነው፡፡ ዳርጌ ቆሼ አካባቢ ያለወላጅና ተንከባካቢ ፍቅር ያደገ በመሆኑና ሞዴል የሚሆነው አካል ባለማግኘቱ በተንሻፈፈ ሰብእና ሊቀረጽ ችሏል፡፡ በመሆኑም ጥረት የሚያደርገው በራሱ በመተማመን ስራ ለመስራት ሳይሆን ከሌሎች መጠበቅን ነው፡፡ እነ ሌላሠውን ቆሼን ለማሳየት ይዞ በሔደበት ወቅትም በለቅሶ ታጅቦ ችግሩን የሚያዋይ የጥገኝነት ሰብእናው ስለሚያስገድደውና ከእነሱ የሚፈልገውን ነገር ለማግኘት ሲል ነው፡፡ ከሚፈጠር ቅርርብና ግንኙነት ሁሉ እርዳታን መጠበቅ የጥገኝነት ሰብእና መዳበር አንዱ መገለጫም ነው፡፡ ዳርጌም ይህንኑ ሲፈጽም ይስተዋላል፡፡

> [አርሴማ] ‹አንተ ቤተሰቦችህ እዚህ ሰፈር ናቸው?› ስትለው፣
>
> ‹እናቴ በልጅነቴ ነው የሞተችው … አውሬው ነው የገደላት … አባቴን አላውቀውም› አለ፡፡

‹የምን አውሬ?› አለ፣ ንዋይ ግራ ገብቶትና ደንግጦ፡፡

‹አይ ጅብ ምናምን መስሎህ ነው፡፡ ቫይረሱ ነው … አውሬው የምንለው› አለ፣ በሐዘን የተሸረበ ፈገግታው ብልጭ ብሎ እየጠፋ፡፡

‹ዘመድ ጋ ነው ያደግኸው?› አለ ድንጋጤው ያለቀቀው ንዋይ፡፡

‹ቆሼ ነው ያሳደገኝ … እዚሁ ያገኘሁትን እየለቃቀምኩ ነው ያደግሁት፡፡ ሲመሽ አንዱ ቤት ጥጋ ጥግ ካልሆነም ቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥ አድራለሁ፡፡ በዛ ላይ የሽሌ ልጅ … ኤይድስ አለበት እያሉ … ያገኘኝ ሁሉ እንደሰባራ የቆሼ ጠርሙስ ይጠልዝሀል› አለ፡፡ (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 210)

ሌላሠው፣ ንዋይ፣ ሳንቾና አርሴማ በዳርጌ መሪነት ቆሼን ለማየት በሔዱበት ወቅት ባዩት ነገር በመገረም የዳርጌን አስተዳደግ ሲጠይቁት በወቅቱ የሚታየውን ትዕይንት እየፈጸመ እንዳደገ ይገልጽላቸዋል፡፡ የሴተኛ አዳሪ ልጅ በመሆኑና እናቱን በአውሬው (ኤድስ) የተነጠቀ በመሆኑ ማንም እንደፈለገ እያንገላታውና መጠጊያ አጥቶ በየበረንዳው እያደረና ከቆሼ ‹‹ሲሳይ እየተቋደሰ›› እንዳደገም ይገልጽላቸዋል፡፡ ዳርጌ ‹‹የሽሌ ልጅ … ኤይድስ አለበት እያሉ … ያገኘኝ ሁሉ እንደሰባራ የቆሼ ጠርሙስ ይጠልዝሀል (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 210)፡፡›› ሲልም ይደመጣል፡፡ ይህም ዳርጌ ራሱን እንዳይችል ያሽማቀቀውና ኑሮውን በጥገኝነት እንዲገፋ ያደረገው ጉዳይ ነው፡፡

ማህበረሰቡ ለሴተኛ አዳሪዎች የሚሰጣቸው ስምና ከእነሱ ለሚወለዱ ልጆች የሚያሳያቸው ንቀት ልጆቹ የጥገኝነት ሰለባ እንዲሆኑና ከሌሎች የሰው ልጆች እኩል እንዳልሆኑ እንዲሰማቸው የሚያደርግ ነው፡፡ የዳርጌ ሰብእናም በዚህ ሁኔታ የተቀረጸ ነው፡፡

### 4.2.3. ከቤተሰብ ተጽእኖ ጋር ተያይዞ ሰብእናቸው የተዋቀረ ገፀባህርያት

በዚህ ርዕስ ስር የገፀባህርያት ሰብእና ከቤተሰብ ጋር በሚኖር መስተጋብር የተዋቀረበት ስልት የተገለጸ ሲሆን ለዚህም የሲራክ፣ የማስረሻና የሉሲ ሰብእና ቀርቧል፡፡

ሲራክ ጉረኛ፣ ትዕቢተኛ፣ ሆን ብሎ ሰዎችን ለመጉዳት የሚጥር፣ ሲበዛ ተንኮለኛና ከኔ በላይ ላሳር በሚል የሰብእና ውቅር የተገነባ ነው፡፡ ይህንን ሰብእናውን ያገኘው ደግሞ ከልደቱ ጀምሮ ነው፡፡ የተወለደው ታስቦበትና ታልሞ ሳይሆን በድንገት በተከሰተ የፍቅር ጨዋታ ነው፡፡ አወላለዱ ያላመረው ሲራክ አስተዳደጉም ከፋና አሁን ያለበትን ሰብእና ለመላበስ በቃ፡፡ ሲራክ

ከአንዲት የቤት ሰራተኛ፣ አባቱ ገና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ እያለ የወለደው ሲሆን ያደገው ደግሞ ከአባቱ ቤተሰቦች ከአያቱ ጋር ነው፡፡ አያቱም በአያትነት ሳይሆን በግዞት የሚያኖሩት እስኪመስሉ ድረስ ግፍና ስቃይን አበዙበት፡፡ የደረሰበትን ሁኔታም በአንድ ወቅት ከወንድሙ (አባቱ) ቤት በነበረበት ወቅት ሁለቱ ህጻናት በሚጣሉበት ጊዜ አባቱ ድንገት ‹‹የገረድ ልጅ›› የሚል ስድብ ሲሳደብ ውስጡን አስቆጣውና ወንድሙን (አባቱን) እዲህ ሲል ለማናገር ተገደደ፡፡ ‹‹የሃይ ስኩል ተማሪ ሆነህ የቤት ሰራተኛችሁን አስረግዘህ፣ ሳልፈልግ የተወለድኩ የገረድ ልጅ መሆኔን፣ ዛሬ ሳይሆን ገና በልጀነቴ ነው ያወቅሁት፡፡ አባታችን ከሞተ በኋላ … ያቺ ክፉ የእንጀራ አያቴ ልበላት እንጂ፣ እሷ እናቴ ልትሆን አትችልም … ያሳየችኝን ስቃይ ሳስበው እናቴ ባለመሆኗ ደስ ይለኛል (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 126)፡፡››

ሲራክ ይህንን ሁሉ ድብቅ ሰብእናውን በኢንቂው የአእምሮው ክፍል አግቶ ሲኖር ‹‹የገረድ ልጅ›› የምትል ሀረግ በመስማቱ ብቻ በኢድ አማካኝነት የነፍሱ ህመም ተቀሰቀሰበት፡፡ ማንነቱን በሚመለከት ከሉሲ ጋር በሚያደርገው ቃለ ምልልስም ይህንኑ ደግሞ ሲናገር ይስተዋላል፡፡ ‹‹የገረድ ልጅ›› የሚለውንም እንደእናት ጡት ገና በልጅነቱ እየጠባ እንዳደገ ይገልጻል፡፡ ‹‹ዕድሜ እናቴ ላልሆነችው ክፉ ‹እንጀራ አያቴ› በተበሳጨች ቁጥር ‹የገረድ ልጅ› እያለች ስትሰድበኝ ‹የገረድ ልጅ› ምን ይሆን እያልኩኝ ገና በልጅነቴ ግራ ይገባኝ ነበር (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 235)፡፡››

ግፍ የወለደው ሲራክ የሰዎችን ጭካኔ አስቀድሞ ስለተረዳ ለማንም አይጨነቅም፡፡ ስለዚህም ራሱን ከሁሉ የበላይ እንደሆነ አድርጎ በማሰብ ቀድሞ የደረሰበትን በደል ለማካካስ በሚያደርገው ጥረት አሁን የያዘውን ሰብእና ሊላበስ ቻለ፡፡ ሲራክ የራስ ወዳድ ሰዎችን ሰብእና የተላበሰ (Narcissistic Personality Disorder) ነው፡፡ ከልጅነቱ ጀምሮ በብዙ ስቃይ ያደገው ሲራክ ሲበዛ ራስ ወዳድ፣ የራሱን ጥቅም ብቻ የሚያሳድድ፣ እሱ የፈለገው ነገር ካልተሳካ ለበቀል የሚጋበዝ፣ ትዕቢተኛ፣ ጉረኛ፣ ትኩረት የሚፈልግና ሁሉ በእጁ የሚመስለው ነው፡፡ ሲራክ ተግባሩ ሁሉ እኩይ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታም እኩይ ገፀባህርይ (Evil Character) ነው፡፡ ምክያቱም እኩይ ገፀባህርይ ግብረ ገብነት የሌለው፣ የከፋ ራስ ወዳድነትና የጭካኔ ተግባርን የሚያከናውን ነው፡፡ በተለያዩ ክፍሎች ላይም እነዚህን የሰብእና መዛባት ምልክቶች ሲያንፀባርቅ ይስተዋላል፡፡ ከምስጢር ፍቅር ስለያዘው ብቻ የራሱን ጥቅም ለማሳደድ በተደጋጋሚ በትዕቢት ሲወጠር የሚስተዋል፣ ትኩረት እንደማትሰጠው ሲያውቅ የሚበሳጭ፣

ምስጢር ፊት እንዳልሰጠችው በማሰብና ሌላሠው በጻፈው ማስታወሻ የሚያሳየውን የሰብእና ቅጥ በማየቱ ምስጢርንም ሌላሠውንም ለመበቀል ሲል ማስረሻን እንደመሳሪያ የተጠቀመ ነው፡፡

ሲራክ በከፋ ራስ ወዳድነት ውስጥ በመሆኑ ምስጢር ህመምተኛው ሆና በእጁ እንድትወድቅ ይመኛል፡፡ ምስጢርን ህመምተኛው እንድትሆን የሚመኘው በውስጡ ታምቆ የኖረውን ፍቅር ህመምተኛው ሆና እንድትለግሰው በማሰብ ነው፡፡ ይህንንም ከሌላሠው ጋር በሚያደርጉት ቃለ ምልልስ በራሱ አንደበት ‹‹… ግን በቃ አንዳንዴ ሕመምተኛዬ ብትሆን ብዬ አስብና ምን ያህል ከባድ የእጅ *ሥራ* እንደምትሆን ይታየኛል (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 109)፡፡›› ሲል ይደመጣል፡፡ ይህም አንድም ራስ ወዳድነቱን የሚያሳይ ሲሆን አንድም ኢንቁ በሆነው የአእምሮው ክፍል ተቀብሮና ታጭቆ የቆየው የምስጢር ፍቅር ድንገት ሳያስበው ሲገለጽበት የሚያሳይ ነው፡፡ ወይም ደስታን ብቻ አጥብቆ የሚፈልገውና ለማህበራዊ ደንቦች የማይጨነቀው ኢድ የአእምሮው ክፍል በውስጡ ያለውን ሀሳብ ድንገት ዝርግፍ ሲያደርግ የሚያሳይ ነው፡፡ ምክንያቱም ኢድ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የመጣለትንና የመሰለውን ሀሳብም ይሁን ድርጊት ከመፈጸም ወደኋላ አይልም፡፡

ሲራክ ለምስጢር ካለው ጥልቅ ፍቅር የተነሳ የምታደርገውን እንቅስቃሴ ሁሉ ለመቆጣጠር ይሞክራል፡፡ የሚቀርባትን ሰው ሁሉ በአንክሮ ይመለከታል፡፡ ከሳንቾ ጋር የጀመረችው የአጭር ጊዜ ቅርርብም ውስጡን ሰላም እያሳጣው ነው፡፡ በመሆኑም በምስጢር በኩል የሚመጣበትን ሁሉ ለመጋፈጥ በውስጡ ያምናል፡፡ ከሲስተር ዘቢባ ቤት በነበረው የራት ግብዣ ላይም ምስጢርና ሳንቾ አንድ ላይ መምጣታቸው የፈጠረበት ስሜት የተለየ ነው፡፡ በዚህም ሳንቾን ለማጥፋት ቆርጦ ይነሳል፡፡ ሳንቾን መጥላቱንና ለመበቀል ማሰቡን ከሚያደርገው እንቅስቃሴ ለመታዘብ ይቻላል፡፡ ከእራት ግብዣው ሲመለስም ‹‹አልፎ አልፎ መሪውን በእጆቹ ይመታና፣ ‹ሺት … መምጣት አልነበረብህም ሲራክ … ቆይ እኔ አይደለሁም ብቻ› ይልና ደግሞ ተመልሶ ከት ብሎ በራሱ ይ*ሥ*ቃል (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 132)፡፡›› ሲራክ የመኪናውን መሪ መደብደቡ ኢንቁ በሆነው የአእምሮው ክፍል ውስጥ ሲራክን ለመበቀል ማሰቡንና ይህንም ለመወጣትና ንዴቱን ለማስታገስ ድርጊቱን በቅርቡ ባገኘው ግዑዝ ነገር ላይ ሲፈጽም ይስተዋላል፡፡ ይህም በውስጡ የተፈጠረውን *ሥነ* ልቦናዊ ስሜትን ለሌላ አካል በማስተላለፍ (በDisplacement) ለማስታገስ የሚያደርገው ጥረት ነው፡፡ ምክንያቱም ከአንድ አካል ጋር የተፈጠረን ቅራኔ በሌሎች ላይ በመበቀል ውስጣዊ ጭንቀትን መከላከል ይቻላልና፡፡

ለብቻው ሲሆን ብዙ የሚያቅደው ሲራክ በልቡ ከሚመኛትና ከሚያፈቅራት ምስጢር ጋ ሲደርስ የሚይዘው የሚጨብጠው ይጠፋዋል፡፡ ይህንንም እንደመሸነፍ ስለሚቆጥረው ውስጡ ይጨነቃል፡፡ ከዚህ ጭንቀቱ ነጻ ለመውጣትም የሚይዘውን የሚያሳጣው ስሜት የእውነተኛ ፍቅር ምልክት እንደሆነ ለማሰብ ይገደዳል፡፡

‹‹[ምስጢር] የምታሳየው ቸልታ የንቀት ስለሚመስለው እልህ ውስጥ ገብቷል፡፡ ለብቻው ሲሆን ብዙ ያቅድ ይፎክርና አጠገቧ ሲደርስ፣ ለምን ጌታውን እንዳየ ውሻ ጭራውን እንደሚቆላ አይገባውም፡፡ ነገሩ የሚፈጥርበትን ብስጭት ለማርገብ ለራሱ የሚያቀርበው ምክንያት፣ **ለምስጢር ያለው ስሜት የእውነተኛ ፍቅር ስሜት ስለሆነ** የርሱ እጣ ፋንታ እሷ መሆኗን ለራሱ እየተናዘዘ ውስጡን በተስፋ ይሞላል፡፡ (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 133) (አጽንኦት ተጨምሯል)

ሲራክ የሌሎችን ትኩረት የሚፈልግና ሲበዛ እልኸኛም ነው፡፡ ሁልጊዜም ቢሆን በሚደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ሁሉ የሌሎችን ትኩረት ለመሳብና ዓለም በእሱ ዙሪያ ብቻ እንድትሽከረከር ይፈልጋል፡፡ ትኩረት ያልተሰጠው በመሰለው ጊዜም የሰብእና መዛባቱ በኢድ ገፋፊነት ሲንጸባረቅ ይገኛል፡፡ ወይዘሮ ኤደንና ምስጢርን ከሌላሠው ጋር ለማገናኘት በጳውሎስ ሆስፒታል በሚገኘው ካፌ በሔዱበት ወቅት ከአስተናጋጇ ጋር የሚፈጠረው እሰጥ አገባ ከሲራክ አብዝቶ ትኩረት ፈላጊነት የመጣ ነው፡፡

[ሲራክ] **አስተናጋጇን ደጋግሞ ምልክት ቢያሳያትም ችላ ያለችው ስለመሰለው በስጨት ብሎ አጨብጭቦ ጠራት፡፡** የሰበሰበችውን ስኒዎችና ሰሃኖች እንደ ያዘች ፈንጠር ብላ ስትቆም ቆጣ ብሎ

‹ቆይ ሁሌ መለመን አለባችሁ ማለት ነው? እስኪ ፈጠን ብለሽ ሦስት ማኪያቶ … ኖርማል … አሰሪልን› ብሎ ከመጨረሱ ፊቷን አዙራ ልትሄድ ስትል ‹እንዴ … ምንድን ነው ነገሩ ዛሬ? ምን ያንቀለቅልሻል … ምን አይነቷ …› አለና፣ ሊል ያሰበውን ዋጥ አደረገው፡፡

ራቅ ብላ የቆመችው አስተናጋጅ ደንታም እንዳልሰጣት፣ ‹ቢቃ … አዘዛችሁ አይደል? …› አለችና ትክሻዋን ከፍ ዝቅ አደረገች፡፡

‹እንዲየውም ተይው … ተይው በቃ ሂጂ፡፡ ይቅርታ ስትክለፈለፍብኝ እኮ ምን እደምትፈልጉም ሳልጠይቃችሁ፡፡ ምን ይምጣላችሁ?› አለ፣ በልጅቷ ሁኔታ በስጨት ብሎ፡፡ ሁለቱም ማኪያቶው እንዲሆንላቸው ሲስማሙ፣ በንዴት ፈንጠር ብሎ ተነሳና ዝም ብሎ አልፏት ወደ ውስጥ ገብቶ ተመለሰ፡፡

‹አንጀት አድብን ብቻ እኮ ነው የተሰበሰበው፡፡ ከየት እንደሚለቃቅሟቸው አላውቅም፡፡ ትንሽ ከተሻለ ብዬ፣ ውስጥ ራሴ ለባሬስታው ነግሬው መጣሁ፡፡› (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 77) (አጽንኦት ተጨምሯል)

ሲራክን ከመጀመሪያውም ትኩረት ያልሰጠችው አስተናጋጇ አሁንም በንቀት መንፈስ ያየችው ስለመሰለው የበለጠ ንዴት ውስጥ ገባ፡፡ ስድብና ዘለፋንም ካዥጎደጎደ በኋላ ራሱ ሔዶ ለማዘዝ ተጋበዘ፡፡ ይህ ሁሉ ጣጣ ከሲራክ የሰብእና መዛባት የመጣ ነው፡፡ ካለበት የሰብእና መዛባት የተነሳም ከሌሎች በተለየ መልኩ የተናቀና ከሁሉም በታች የሆነ ይመስለዋል፡፡

ቀጣዩ ሳምንት ለሲራክ አስቸጋሪ ጊዜ ነበረ፡፡ ብዙ ህመምተኞች መጥተው ሌላሠው ስለሌለ ዶክተር ሲራክ ይያችሁ ሲባሉ አሻፈረኝ እሱ እስኪመጣ እንጠብቃለን እያሉ ቀጠሮ አስቀይረው መሄዳቸው የበለጠ አናዶታል፡፡ ከካፍቴሪያ ሰራተኛዋ ጀምሮ ሁሉም ለሌላሠው እንጂ ላንተ አንታዘዝም የሚሉት መሰለው፡፡ ዘበኛው በሩን ቶሎ አይከፍቱለትም … ሁለት ሦስት ጊዜ ቡና አዝዞ ከብዙ ውትወታ በኋላ ቆይቶ ነው የሚመጣለት፡፡ ለማኔጅመንት ሳምንታዊ ስብሰባው ሲስተር ዘቢባ ብቻ ናት የመጣችው፡፡ (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 328)

ሌላሠው ክሊኒኩን በሜዲካል ዳይሬክተርነት እንዲመራ ወክሎት ወደ አሜሪካ በሔደ ጊዜ ሁሉም የእስታፍ ሰራተኛ ለሱ አንታዘዝም ያሉት እየመሰለው ለስነ ልቦናዊ ጭንቀት ተጋልጧል፡፡ ከዚህ ጭንቀቱ ለመገላገልና ያለበትን የሰብእና መዛባት ለማሳወቅም የጽዳት ሰራተኛን እስከማባረር ደርሷል፡፡ ሳር ቅጠሉ በሱ የሚስቅ የሚሳለቅ የሚመስለው ሲራክ አብዝቶ ትኩረት የማግኘት በሽታ የሚያሰቃየው ነው፡፡ ከሁሉ የሚያንስና የሚናቅ ስለሚመስለው ከሁሉ የሚበልጥና የሚሻል ለመምሰል ይጥራል፡፡ ይህም የታህታይ ምስቅልቅል (Inferiority Complex) ጣጣ ነው፡፡ ሲራክ ገና ከህጻንነቱ ጀምሮ ‹‹የገረድ ልጅ›› እየተባለ ያደገና በበታችነት ስሜት ሲሰቃይ የኖረ ነው፡፡ ይህንን የበታችነት ስሜት ለማካካስም ሌሎችን ሲጎዳ ይታያል፡፡

ይህንን ሰብእና እንዲላበስ ያደረገው ደግሞ በአያቱ ቤት ‹‹የገረድ ልጅ›› እየተባለ ማደጉና ልጅ ማግኘት የሚገባውን የወላጅ እንክብካቤ በአግባቡ ባለማግኘቱ ነው፡፡

ማስረሻም እንደ ሲራክ ሁሉ ከቤተሰብ ጋር በሚኖር መስተጋብር ሰብእናው የተገነባና ሌላው እኩይ ገፀባህርይ ሲሆን የተለያየ የሰብእና መዛባት ችግር ይስተዋልበታል፡፡ በዋናነትም ለማህበራዊ ህግና ደንብ ግድ የለውም (Antisocial Personality Disorder ይታይበታል)፡፡ በመሆኑም ሆን ብሎ አካላዊና ሥነ ልቦናዊ ጥቃት ለማድረስ ጥረት ያደርጋል፡፡ በምስጢር ላይ ከሁለተኛ ዓመት የዩኒቨርሲቲ ቆይታ ጀምሮ በተለያዩ ጊዜያት በሚያደርስባት ማስፈራሪያና ዛቻ ሥነ ልቦናዊ ጥቃት አድርሷል፡፡ በሳንቾ ላይ ደግሞ የግድያ ሙከራ በማድረግ አካላዊ ጥቃት ለመፈጸም ጥረት አድርጓል (ምንም እንኳ የሞት ጽዋው ተቀባይ ራሱ ቢሆንም)፡፡ የምስጢርንም ስሜት ለመረዳት ጊዜ አይሰጣትም፤ እሱ እንደሚወዳትና እንደሚያፈቅራት እንጂ እሷ እንደማትፈልገውና የኔ የምትለው ሰው እንዳላት ለማረጋገጥ ጥረት አያደርግም፡፡ ባጠፋው ጥፋት ጸጸት አይሰማውም፤ ተሞክሮ በመውሰድ ራሱን ለማሻሻልም ጥረት አያደርግም፡፡ ልክ የለሽ መተማመን (Hubris) ይታይበታል፡፡ ችግሮችን ሁሉ በእብሪተኝነት፣ በእውቀት፣ በገንዘብና በስልጣን አቅም በጥቅሉ በጉልበት እንደሚፈቱ ያምናል፡፡ በረቀቀ መንገድ ባይሆንም ወንጀል ፈጽሞ የማምለጥ ዕድል አለው፡፡ በምስጢር ላይ በሚያደርሰው ማስፈራሪያና ዛቻ ምክንያት ለህግ ቢቀርብም ስልጣን ላይ ባሉት ዘመዶቹ አማካኝነት ይፈታል፡፡

ማስረሻ በአንድ ነገር ላይ ብቻ በማተኮር በኃይልም ይሁን ሌሎችን አማራጮች ተጠቅሞ የግሉ የማድረግ ምኞት ከቤተሰቡ የወረሰውና አብሮት ያደገ ነው፡፡ በተለይ ደግሞ የእናቱ ተጽእኖ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ የራሷን ተሞክሮ በልጇ ላይ በመጻፍ ለትውልድ ለማስተላለፍ የምትፈልግ እስከምትመስል ድረስ ማስረሻን እንደምታደፋፍረው ከሌላሠው ጋር ከሚያደርገው ምልልስ መረዳት ይቻላል፡፡

> ‹እናቴ ገና የሃይስኩል ተማሪ ሆና ነው የወለደችኝ፡፡ አባቴ ከእናቴ ፍቅር ተጠናውቶት ነገር ዓለሙን ትቶ፣ ስትወጣ ስትገባ ለሦስት አመት ያህል እሷን መከተል ነበር ሥራው፡፡ እናቴ እነደነገረችኝ እሷ ደግሞ እንደሱ የምትጠላው ሰው በምድር ላይ አልነበረም፡፡ በዕድሜም ብዙ ይበልጣት ነበር መሰለኝ፡፡ በኋላ አንድ ቀን አላናግር ስትለው ክፉኛ ደበደባትና ነገሩ ወደ ቤተሰብ ደረሰ …› (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 278)

> ‹አሁን አብሬው የምኖረው አጎቴ፣ ያባቴ ታላቅ ወንድም ነው፡፡ በሁለቱ መሃል ጣልቃ ገብቶ አባቴን ወደ ክፍለ ሀገር ሥራ አስይዘው ሲያርቁት ነገሩ ትንሽ ፋታ አገኘ፡፡ በዚህ መሀል አጎቴ ከእናቴ ጋር ቀስ በቀስ ተቀራርበው እኔ ተረገዝኩ፡፡ … እርጉዝ መሆኗን ሲያውቁ እንዴት እንዳሳመናት አላውቅም፣ የሆነ የሆነ ነገር ተደርጎና ተሸፋፍኖ ከአባቴ ጋር ተጋብተው እኔም የእሱ ልጅ ተብዬ ተወለድኩ፡፡› (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 278 - 279)

> ትንሽ አብረው እንደኖሩ ያ የምትጠላውንና እንደ ጦር የምትፈራውን ሰው በፍቅር አበደችለት፡፡ እናቴ … ላባቴ ያላትን ፍቅር ልነግርህ አልችልም፡፡ እንደነገረችኝ ከሆነ … እንደዛ አይነት ጥሩ ሰው መሆኑን ብታውቅ ኖሮ፣ እንደዛ በሷ ፍቅር ሲሰቃይ እሷም ለማይሆን ሰው ሲሳይ አትሆንም ነበር፡፡› (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 279)

> **‹[እናቴ] ናት ተስፋ አትቁረጥ … አባትህ ተስፋ ስላልቆረጠ ነው እኔን ያገኘው ብላ ነገሩን ተስፋ አስቆርጦኝ በፍቅር ህመም ሳቃስት የምታበረታታኝ›** አለ አይኑ እየረጠበ፡፡ (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 280) (አጽንኦት ተጨምሯል)

የማስረሻ እናት ሰብእና በማስረሻ አባትና አጎት አማካኝነት በደረሰ በደል ሲዛባ የማስረሻ ሰብእና ደግሞ በእናቱ አማካኝነት ተዛብቷል፡፡ በሰብእና አቀራረጽ የቤተሰብ ሚና ምንያህል ሊሆን እንደሚችልም ለማሳየት ታስቦ ጥቅም ላይ የዋለ ነው፡፡

ማስታወስም ሆነ መርሳት ለህይወት እጅግ አስፈላጊ ነገሮች ናቸው፡፡ አስፈላጊ ያልሆነንና በህይወት ዑደት ውስጥ በአንድ አጋጣሚ የተከሰተን ክስተት ሁሌ እያሰላሰሉ ነፍስን ማስጨነቅ ውስጥን የሚያቆስል ጉዳይ ነው፡፡ ማስረሻም የሚስተዋልበት የዚህ አይነት ሁኔታ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ከሰውነት ደረጃ እስኪወጣ ድረስ እየተፈታተነው ይገኛል፡፡

ማስረሻ ምስጢርን ለማግኘት በሚወጣ በሚወርድበት ወቅት የተለያዩ መሰናክሎች ሲያጋጥሙት ሥነ ልቦናዊ የጭንቀት መከላከያ ስልቶችን ለመጠቀም ጥረት ሲያደርግ ይስተዋላል፡፡ ምስጢርን ለማየት ወይም ለማግኘት ሲል ከምትሰራበት ክሊኒክ ስሙን ቀይሮ በሽተኛ በመምሰል ለመታከም ይሔዳል፡፡ ቀድሞ ነገር ስሙን መቀየሩና በሽተኛ መስሎ ለመታከም ጥረት ማድረጉ ለችግሩ ሌላ ችግርን በመፍጠር ውስጣዊ የፍቅር ነበልባላዊ እሳት ከሚያደርስበት ቃጠሎ እራሱን ነጻ ለማውጣት የቀመረው ዘዴ ነው፡፡ ይህ ዘዴው ግን ወዲያውኑ ክሊኒኩ ከመድረሱ ይታወቅበትና ምስጢርን ሳይሆን ሌላሠውን ያገኛል፡፡

> [ሌላሠው] ‹ይቅርታ ስምህ ማን ነበር?› ሲለው ሳያስበው አመለጠውና ‹ማስረሻ …› አለ፡፡
>
> ‹ኦህ … ቻርትህ ላይ እንደሱ ነው የሚለው?› ግራ እንደገባው ሆኖ ቻርቱን ገልበጥ አድርጎ ሲያይ ግንባሩ ላይ ያቸፈፈውን ላብ በመዳፉ ጠረገና፣
>
> ‹ፍቅሩ ታደሰ የቤት ስሜ ነው … አንዳንዴ እሱንም እጠቀማለሁ› አለ፣ ለመረጋጋት እየሞከረ፡፡ (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 277)

ከሌላሠው ጋር በሚያደርጉት ቃለ ምልልስም ‹‹ይቅርታ ስምህ ማን ነበር?›› የሚል ድንገተኛ ጥያቄ በሌላሠው ሲጠየቅ ማስረሻ ብሎ ይመልሳል፡፡ ይህንን ቀበል አድርጎ ሌላሠው ቻርቱ ላይ እንደዚያ እንደማይል ሲያስረዳው ፍቅሩ ታደሰ የሚለው ስሙ ቤት ላይ የሚጠራበትና አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀምበት ለማስረዳት ይሞክራል፡፡ ይህም ሌላ ሥነ ልቦናዊ የጭንቀት መከላከያ ስልት ነው፡፡ ምክንያቱም ለማጭበርበር ያደረገው ሙከራ የፈጠረበት ውስጣዊ ውጥረት ፊቱ ላይ በላብ መልኩ እየወጣ ያጋልጠው ስለጀመረ ይህን ለመሸፈን የተጠቀመበት ጭንብል ነው፡፡

ሉሲ ሌላኛዋ ራስ ወዳድነት የሚታይባት (Narcissistic Personality Disorder) ገፀባህርይ ሆና ቀርባለች፡፡ ሉሲ ይህን ሰብእናዋን ለመላበስ የበቃችው እናቷ በምታደርስባት ስቃይ ነው፡፡ የሉሲ እናት በልጇ ላይ የምታደርስባት ግፍና መከራ ባለቤቷ ያደረሰባትን የልብ ስብራትና የሰብእና ቀውስ ለማካካስ ነው፡፡ ባለቤቷ እቤታቸው ድረስ እያመጣ ከሌሎች ሴቶች ጋር መቃበጡ በጣም ስለጎዳትና ባለቤቷን እንደፈለገች ለመናገር አቅሙ ስላልነበራት አጸፋውን በልጇ ላይ ለመፈጸም ተገደደች፡፡ በውስጧ የተፈጠረውን ሥነ ልቦናዊ ጭንቀት ለማርገብም ስሜትን ለሌላ አካል ማስተላለፍ (Displacement) በመባል የሚታወቀውን የጭንቀት መከላከያ ስልት ተግበራዊ ስታደርግ ትስተዋላለች፡፡ በመልኳም ይሁን በባሕርይዋ አባቷን ትመስላለች ተብላ የታሰበችው ሉሲም የአባቷን አበሳ ተሸካሚና የእናቷ የቁጣ በትር ማረፊያ ለመሆን ተገደደች፡፡ ‹‹ያኔ እኔ የሰባት አመት ልጅ ነበርኩ መሰለኝ፡፡ እሱን ስለምመስላት ይሁን እንጃ በማላውቀው ምክንያት ጥምድ አድርጋ ያዘችኝ (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 325)፡፡›› ሉሲ ይህ ሁሉ ሲሆን ምክንያቱ አልተገለጸላትም፡፡ በኋላ እናቷ እሷንና ባለቤቷን ትታ ሁለቱን ልጆቿን ይዛ አሜሪካ ሔደች፡፡ ሉሲም በእናቷ መሔድ ብዙም አልተጨነቀችም፡፡ እንዲያውም የእናቷ ስድብና ድብደባ ስለቀረላት ደስተኛ ሆነች፡፡ ይህንንም ለሲራክ ታሪኳን በምታጋራበት ወቅት ‹‹ዱላዋና ስድቧ ስለቀረልኝ እናቴ አለመኖሯ ብዙም አልረበሸኝም ነበር (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 325)›› ስትል

ትደመጣለች፡፡ ይህ ደስተኛነት ግን ለረጅም ጊዜ የሚቆይ አልነበረም፡፡ አባቷ፣ እናቷ አሜሪካ ከሔደች ከሁለት ዓመት በኋላ ከሚቃበጣቸው ሴቶች አንዷን ካገባ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ደስታዋ በአጭር እንዲቀጭ ሆነ፡፡ አዲሷ የአባቷ ሚስት መጀመሪያ አካባቢ ጥሩ መስላ ቀርባ ያልተገባ ስራ እንድትሰራ አደፋፈረቻትና ከአባቷ ጋር እንድትጣላ አድርጋ ከቤት አስወጣቻት፡፡ ሉሲም በጠዋቱ የጎዳና ሕይወትን ለመኖር ተገደደች፡፡ በከፍተኛ የበቀል ስሜትም ተሞላች፡፡ ክብሬ ዝናዬ ተገፈፈ ብሎ ከቤት ያባረራትን አባቷን ክብሩ እስከምን ድረስ እንደሆነ ለማሳየት ቆርጣ ተነሳች፡፡ ይህን ለመፈጸምም ጓደኞቹን እንደመሳሪያ መጠቀም ጀመረች፡፡

> *መጀመሪያ ላይ የማያውቁኝ የሱ ጓደኞችና ደንበኞች የሚገቡበት ቤት እገባና አብሬያቸው ከወጣሁ በኋላ ገንዘባቸውን ኪሴ ከትቼ የማን ልጅ እንደሆንኩ ስነግራቸው የሚገቡበት ይጠፋቸዋል፡፡ ወሬው እንዲደርሰው አደርጋለሁ፡፡ ሲሰማ ሊያብድ ምንም አይቀረውም፡፡ መጨረሻ ላይ እሱም ልጄ አይደለችም ብሎ ሲክደኝ እኔም ከሱ ጋር ትግሌን ትቼ ወደ ራሴ ሕይወት ተመለስኩ፡፡* (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 327)

ሉሲ ይህን በበቀል የተሞላ ሰብእናዋን ለመገንባት የቻለችው እናቷና አባቷ በኋላ ላይ ደግሞ ‹‹የእንጀራ እናቷ›› ተጋግዘው ባጠጧት የመከራ ጽዋ አማካኝነት ነው፡፡ ቤተሰቦቿ የራሳቸው ሰብእና ተዛብቶ የሌሎችን ሰብእና ለማቃወስ በቁ፡፡

**4.2.4. ከአካባቢና ከማህበረሰብ ጋር በሚኖር መስተጋብር ሰብእናቸው የተዋቀረ ገፀባህርያት**

በ*ሌላ ሰው* ረጅም ልቦለድ ውስጥ የሚገኙ ገፀባህርያት ሰብእና ከአካባቢያቸውና ከማህበረሰቡ ጋር በሚኖራቸው መስተጋብር ላይም የተመሠረት ነው፡፡ ይህንን ከሚያንጸባርቁት መካከልም አቶ ገብረመድህን፣ አቶ በድሉ፣ ወይዘሮ ኤደንና ዝናሽ ይጠቀሳሉ፡፡

በጣም አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮችንና የህይወት መመሪያዎችን ብሎም ሁሉንም ነገር የመርሳት ችግርም ትልቅ በሽታ ነው፡፡ የሌላሠው ታካሚ የሆኑት የ83 ዓመቱ አቶ ገብረመድህን በህይወት ዘመናቸው የፈጸሙትንም ሆነ ያከናወኑትን ተግባር ለማስታወስ ተቸግረዋል፡፡ የሚያስታውሱት ነገር ቢኖር ስማቸውንና የልደት ቀናቸውን ብቻ ነው፡፡ ይህንንም ሌላሠው መሠረታዊ ጥያቄዎችን ሲጠይቃቸው እንኳ መመለስ እንዳልቻሉ ከሚያደርጉት ምልልስ መገንዘብ ይቻላል፡፡

> [ሌላሠው] *‹አቶ ገብረመድህን … የዛሬን ቀን ይነግሩኛል? ቀኑን ወሩንና ዓመቱ ምህረቱን?› ሲል ትኩር ብለው አዩት፡፡*

‹መስከረም ሁለት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስድሳ ሰባት …› አሉ፣ በጣታቸው ለመቁጠር እየሞከሩ፡፡ ሌሎች ቀለል ያሉ ጥያቄዎችን ቢጠይቃቸውም ከስማቸውና ከልደት ቀናቸው ውጪ፣ የቀረውን ሁሉ ሊያስታውሱ አልቻሉም፡፡

‹እሷ ምንዎ ናት?› ብሎ ወደ ልጃቸው ጠቆማቸው፡፡ እንደማያውቋት ትኩር አሉ አዩዋትና፣ አሷማ ባለቤቴ … የልጆቼ እናት ናት … አሉ፡፡ (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 297)

በዕድሜ መግፋትና በሌሎች ሁኔታዎች አማካኝነት የሚፈጠር የመርሳት በሽታ (Alzheimer) አቶ ገብረመድህንን ልጆቻቸውንም እስከመርሳት አድርሷቸዋል፡፡ ለህክምና ይዛቸው የመጣችውን ልጃቸውን ‹‹እሷ ምንዎ ናት?›› ብሎ ሲጠይቃቸው ‹‹እሷማ ባለቤቴ የልጆቼ እናት ናት›› በማለት የሚመልሱትም የመርሳት በሽታው ባደረሰባቸው ተጽእኖ ምክንያት ነው፡፡ በመሆኑም ከሰብአዊነት ተራ እንዲወጡ አስገድዷቸዋል፡፡ በእርግጥ የመርሳት በሽታው የዕድሜ ብቻ ሳይሆን ማህረ ፖለቲካዊ ምክንያትም ሊኖረው ይችላል፡፡ ለዚህም ማረጋገጫው ሌላሠው የእለቱን ቀን ሲጠይቃቸው አስራ ዘጠኝ ስልሳ ሰባትን መጥቀስ ችለዋል፡፡ በኢትዮጵያ ማህረ ፖለቲካዊ ተጨባጭ ሁኔታ ደግሞ 1967 ደርግ ስልጣን የተረከበበት ነው፡፡ ወቅቱም ልዩ ልዩ ድርጊቶች ይፈጸሙበት የነበረና ብዙዎችን ለሰብእና መዛባት ጣጣ የዳረገ ነው፡፡ የአቶ ገብረመድህን የሰብእና መዛባትም ከዚህ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል፡፡ መርሳትም ሆነ ማስታወስ ካልተመጣጠነ የሰብእና በሽታ መሆኑ አይቀሬ ነው፡፡ ማስታወስ ከልኩ ሲያልፍ ለማስረሻ በሽታ እንደሆነው ሁሉ መርሳት ደግሞ ለአቶ ገብረ መድህን ትልቅ የሰብእና ህመም ሆኖባቸዋል፡፡

አቶ በድሉም ከአካባቢና ከማህበረሰብ ጋር በሚኖር መስተጋብር ሰብእናቸው የተቀረጸ ገፀባህርይ ናቸው፡፡ አቶ በድሉንና የቆሼ ሰፈር ነዋሪዎችን የስጋ ደዌ በሽታ ባደረሰባቸው ጠባሳ ምክንያት ሰው ሁሉ ያገላቸው ጀምሯል፡፡ የሚኖሩበትን አካባቢም በተለያዩ ምክንያቶች በማሳበብ በተደጋጋሚ ያስለቅቋቸዋል፡፡ በዚህ ተስፋ የቆረጡት አቶ በድሉና መሰሎቻቸውም ቀደም ሲል የመቃብር ቦታ በነበረው ላይ ጎጆ ቀልሰው ሽራ ወጥረው ኑሮን በመግፋት ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህን የሰብእና ቅጥና እየደረሰባቸው ያለውን ኢሰብአዊ ድርጊትም በአንድ ወቅት ምስጢር፣ ሳንቾና ሌላሠው ሊጠይቋቸው በሔዱ ወቅት ሕያዋኑ ሲሸሹን ጊዜ ተሙታኑ ተጠግተን እንኖራለን በማለት ቁጭትና ንዴት በተቀላቀለበት ድምፀት ሲገልጹ ይደመጣሉ፡፡

‹እየህ ሰፈር ከመምጣታችን በፊት ወደ ላይ ዘውዴ ሜዳ የሚሉት ሰፈር አለ። ከፍ ብሎ ተመንገዱ ብዙም ሳይገባ ነበር የምንኖር ኋላ ግን ሰውም ቲበዛ ቦታው ለንግድ ሲፈለግ ኪራዩም ሰማይ ነካ። ይሄ ያኔ መቃብር ቦታ ነበር። ኋላ አዲሱ ቤተስኪያን ቲሰራ ጊዜ እንደ እኛ ኑሮ የከበደውና መድረሻ ያጣው ሁሉ ጎጆ እየቀለሰ እዚሁ መስፈር ጀመረ። አሁን ይሄ የምንተኛበት መደብ ተበታቹ የመቃብር ቦታ ነው፣ እዚያ መደርደሪያ ስርም ሌላ መቃብር ነው።አንዳንዴ ቅዠቱም መጫጫኑም መከራ ነው። ግን ምን ይደረግ እንግዲህ ሕያዋኑ ቲሸሹን ጊዜ ተሙታኑ ተጠግተን እንኖራለን› ብለው፣ ቁዘማቸውን ሲቀጥሉ ሁሉም ጸጥ አሉ። (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 193)

በአቶ በድሉ አነጋገር ህያዋን የተባሉት አካላት ልዩ ድጋፍና እንክብካቤ የሚሹትን ወገኖች ተጨማሪ ችግር እየፈጠሩ ከቦታ ቦታ ሲያንቀሳቅሷቸው ለሌላ የሰብእና መዛባት እየዳረጓቸው እንደሆነ የሚያመለክት ነው። ምክንያቱም ሰብእና ከቁስነት ከእንስሳነት መለየት ነውና። ቁስነት እና እንስሳነት ደግሞ መገለጫዎቹ ለሌሎች አለማሰብና ለራስ ብቻ መኖር ነው። የአዲስ አበባ ህዝብም ለእነ አቶ በድሉና መሰሎቻቸው ማሰቡን ትቶ ለራሱ ብቻ እንደሚኖር በምስጢር አማካኝነት በሚደረግ ተመስጦ ልቦና ቀርቧል።

ዘነበወርቅ፣ ካፈሩ ወርቅ ባይታፈስም ከወርቅ ይልቅ የከበሩት እንደ ከዋክብት የሚያበሩት የዝናሽ ልጆችና ሰፈሩ ውስጥ የሚርመሰመሱት ሌሎች ሕፃናት ታዩዋት። ሰው ሚሊዮን ዶላር አፍስሶ ከድንጋይ መሀል ወርቅ ያስሳል። እዚሁ ከተማ መሀል የፈሰሱት ሕያዋን ወርቆች ላይ ግን የቤትና የሆቴሉን ቆሻሻ ይደፋባቸዋል። ይህን እያሰበች አንገቷ ላይ ያለውን የወርቅ ሀብል አውልቃ በጥንቃቄ አስቀመጠች። የዝናሽ ልጆች በጭቃ ዳክረውና በረሀብ ጠውልገው፣ በእናታቸው ሞት ቅስማቸው ተሰብሮ አልጋ በሌለበት ሜዳ ላይ ወዳድቀው ታዩዋት። (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 188)

በአቶ በድሉና በመሰሎቻቸው ላይ ግፍና ስቃይን የሚያበዙባቸው አካላትም ከዚህ የተለዩ አይደሉም። አቶ በድሉ ልጃቸው ዝናሽ ታማ በሞትና በህይወት መካከል ሆና ጳውሎስ ሆስፒታል ባለችበት ወቅት የጽዳት ሰራተኛዋ አካላዊ ቁመናቸውን በመመልከት እንዳይገቡ ትከለክላቸዋለች።

የዝናሽ አባት ለመግባት ፈርተው በራፉ ላይ ሲያጮልቁ ኖሮ ልክ [ሌላሠውን] ሲያዩት ተንደርድረው ገቡ።

ከፊት ለፊት የነበሩ በዕድሜ ገፋ ያሉ የጽዳት ሠራተኛ ‹እንዴ የት ነው የሚወላከፉት … ይሄ የማዋለጃ ክፍል ነው፡፡ እስኪ ወደ ደጅ … ምነው አሁንስ የማንም ግሳንግስ ሁሉ … ደግሞ ኮ ቤቱን አጨቀዩት› ሲሉ፣ የሰማው ሌላሠው፣ ስድባቸው ዘግንኖት ዞር ሲል፣ የዝናሽ አባት መሆናቸውን ሲያይ ቁጣውን በትግል ተቆጣጥሮ፣

‹የሕመምተኛዋ አባት ናቸው› አለ፣ ረጋ ባለ ድምጽ፡፡ (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 169)

የጽዳት ሰራተኛዋ ግልፍተኛነት በአቶ በድሉና መሰሎቻቸው ላይ የሰብእና መዛባትን የሚያመጣ ነው፡፡

ወይዘሮ ኤደን ከላይ ሲታዩ ደስተኛና ምንም የሰብእና መዛባት የሌለባቸው ይመስላሉ፡፡ በጥልቀት ለሚመለከታቸው ግን የብዙ ውስብስብ ሰብእና ድምር ውጤት ናቸው፡፡ ከፍተኛ የሆነ የአእምሮ መቃወስና የሰብእና መዛባት ይታይባቸዋል፡፡ ለሚያሳዩት የሰብእና መቃወስና የባሕርይ ምስቅልቅልነት የዳረጋቸውም በህይወት ዘመናቸው ያጋጠማቸው ድርጊት ነው፡፡ ይኸውም አባታቸውንና ወንድሞቻቸውን በግድያ ሲነጠቁ በዐይናቸው በማየታቸው ነው፡፡ በቁማቸው እያቃዠ በህልማቸው እያስለመለመ ጤናቸውን የነሳውና ሰብእናቸውን ያዛባው ይህ አሰቃቂ ድርጊት ነው፡፡ ‹‹አ-ባ-ቴንና ወን-ድ-ሜን ዓይኔ እያየ ነው የገደሏቸው፡፡ ሻቢያ ናችሁ ብለው ደጃፋችን ላይ ደፍተዋቸው ሄዱ (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 83)፡፡›› የወይዘሮ ኤደን ሰብእና የተዛባውና በፍርሀት የተሞላ ኑሮ እንዲኖሩ ያደረጋቸው በሀገራችን በተደጋጋሚ ይካሔድ የነበረው የእርስ በእርስ ጦርነት ነው፡፡ በተለይ ደግሞ በደርግ ውድቀት ዋዜማና መባቻ ላይ የነበረው እልቂት የብዙዎችን ሰብእና የተፈታተነ ጉዳይ ነው፡፡ ወይዘሮ ኤደንም አንድን ድርጊት ተከትሎ የሚመጣ የፍርሀት በሽታ (Post Traumatic Stress Disorder) ተጠቂ ሆነዋል፡፡ በዚህ የታመመ ሰብእናቸው ምክንያት የሚደርስባቸውን ስቃይም ‹‹የሌሊቱ መላቅጥ የሌለው ቅዠት ሳያንስ ቀኑን ሙሉ ደግሞ የሆነ ያልሆነው ነገር እንደፊልም ፊቴ ደንቅሮ ሲያጫውተው ይውላል፡፡ በር ሲዘጋ ወይ የሆነ ነገር ወድቆ ኳ ያለ እንደሆን ፈንጂ የፈነዳ ያህል መዝለል መደንበር ነው (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 82)፡፡›› ሲሉ ይደመጣሉ፡፡ ወይዘሮ ኤደን በሚሰሙት ድምጽ ሁሉ የመረበሽ ስሜት የተፈጠረባቸው ወንድሞቻቸው ፊታቸው ላይ በመሳሪያ በመገደላቸው ምክንያት ነው፡፡ የወንድማቸውና የአባታቸው እንዲሁም በእስር ቤት ሆነው የደረሰባቸው የግርፋትና የመደፈር ስቃይ የህይወት መስመራቸውን ያሳታቸው ጉዳይ ነው፡፡ የፈንጅ ድምጽ የመሰለ ነገር ሁሉ ጭንቀትን ሊፈጥርባቸው ችሏል፡፡ ይህ የሰብእና መዛባት የተከሰተው በአካባቢዊና ማህበረ ፖለቲካዊ ሁኔታ አማካኝነት ነው፡፡

ወይዘሮ ኤደን ከውጭው ዓለም ሸሽተው በራሳቸው አለም የሚኖሩ የ(Schizoid Personality Disorder) ባሕርይ የሚታባቸውም ናቸው፡፡ የዚህ አይነት ሰብእና መዛባት ያለባቸው ሰዎች ትስስር መፍጠር የማይፈልጉ፣ ከማህበራዊ ግንኙነት ተነጥለው የሚኖሩ፣ ብቸኝነትን የሚመርጡ፣ ደስታቸውንም ይሁን ፍላጎታቸውን ለቤተሰብ አባል እንኳ የማይናገሩና የመጀመሪያ ከሚሏቸው የቅርብ ዘመዶቻቸው ውጭ የምስጢር ተካፋይ የሌላቸው ናቸው፡፡

ወይዘሮ ኤደንም ከሰዎች ጋር ግንኙነትን ለመፍጠር ሲያስቡ አስቀድመው የሚደክማቸው፣ ከሰው ጋር ከመገናኘት ይልቅ አልጋቸው ውስጥ ተደብቀው መዋል ማደርን የሚመርጡ ናቸው፡፡ ‹‹ሰው ማግኘትማ ገና ሳስበው ይደክመኛል፡፡ ጨለም ያለ ቦታ ሆኜ ስተክዝና ስቆዝም ለብቻዬ ቁጭ ብዬ መዋል ነው የምመርጠው፡፡ ጠዋት ሲነጋ ካልጋ መውጣት ስቃይ ነው (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 82)፡፡›› ሲሉም ይደመጣሉ፡፡ ደስታቸውንም ይሁን ችግራቸውን ለአንዲት ልጃቸው ለምስጢር እንኳ የማይናገሩ (የጡት እናቷ እንደሆኑ እንኳ ለመናገር ሳይችሉ ለሞት ተቃርበው ሲጣጥሩ ለመንገር ቢፈልጉም ሳይችሉ በደብዳቤ ለመንገር የተገደዱ ናቸው፡፡)፣ ከመጀመሪያ ወዳጃቸው ከእትየ ዘምዘም ውጭ ምስጢራቸውን ለማንም የማያጋሩ ናቸው፡፡ የምስጢር ተካፋያቸው ወይዘሮ ዘምዘም ብቻ እንደሆነች በተለያየ የጽሑፉ ክፍል ላይ ሰፍሮ እናገኛለን፡፡ ‹‹ከሚች ባለቤታቸው ዘመዶች ወይዘሮ ዘምዘም የቅርብ ጓደኛቸውና የረጅም ጊዜ ምስጢረኛቸው ናት (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 68)፡፡›› በሚል በተራኪው አማካይነት የቀረበ ሲሆን፣ ደግሞ ሌላሠው ከሲስተር ዘቢባ ጋር በሚያደርገው ቃለ ምልልስ ‹‹[ወይዘሮ ዘምዘም] የናቷም የሚስጥርም **ብቸኛ** ቅርብ ዘመድና ምስጢረኛ ናት (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 422)፡፡›› ሲል ይስተዋላል፡፡ እንዲሁም ከምስጢር ጋር በሚያደርገው ምልልስም ይህንኑ ያረጋግጥልናል፡፡

> [ምስጢር] እናቷ ትዝ በሚላት የመጨረሻ ቃላቸው ‹ዘምዘም … ዘምዘም› ያሉት ትዝ አላትና፣ ‹ትዬ ዘሚስ መቼ ነው ያወቀችው?› አለችው፡፡
>
> ‹እሷ የናትሽ ሚስጥረኛ ስለሆነች … ለረጅም አመታት ሁሉንም ነገር ሳታውቅ አትቀርም› ሲላት፣ ጸጥ ብላ ስታስብ ቆየች፡፡ (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 451)

ዝናሽ ሌላኛዋ በአካባቢና በማህበረሰብ መስተጋብር ሰብእናዋ የተገነባ ገፀባህርይ ናት፡፡ ዝናሽ በስጋ ደዌ በሽታ ከሚሰቃዩና በድህነት ከሚኖሩ ቤተሰቦች የተገኘች ስትሆን እናትና አባቷን ከድህነት ቀንበር ነጻ ለማውጣትም የተለያዩ ሙከራዎችን አድርጋለች፡፡ ከነዚህም መካከል አረብ ሀገር በመሔድና በመስራት ቤተሰቡን ከድህነት አረንቋ ማውጣት አንዱ ርምጃዋ ነበር፡፡

ሆኖም አረብ እንዳሰበችው አልተቀበላትም፡፡ ይልቁንም በአሰሪዋ ተደፍራና አርግዛ የሰራችበትን ደሞዝ ሳትቀበል ተባረረች፡፡ ብዙ ነገር አስባ ባጭሩ ህልሟ የተቀጨው ዝናሽ የሰብእና መዛባት ሰለባ ሆነች፡፡ ህመሟን ተሸክማ ወደ ቤተሰቦቿ ተመለሰች፡፡ በእናቷ እርዳታ አማኑኤል ሆስፒታል ስትረዳ ቆየች፡፡ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ደግሞ በሽተኛ የነበሩት እናቷ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ አምርራ በማዘኗና ህክምናዋን በማቋረጧ ጨርቋን ጥላ ወደ ጎዳና ለመውጣት ተገደደች፡፡

ዝናሽ ይህን ሰብእና ልትላበስ የቻለችው የማህበረሰቡ አካል የሆኑት ወንዶች በተደጋጋሚ ባደረሱባት *ፆታዊ ጥቃት* ነው፡፡ በአነጋገሯና በድርጊቷ የሰብእና መዛባት እንዳለባት የሚታወቅባት ዝናሽ ጎዳና ላይ በምትኖርበት ወቅት የሶስት መኪናዎችን መስኮት በመሰባበር ብዙ ነገሮችን ስትናገር ትስተዋላለች፡፡ ይህም በአነጋገራቸው በአስተሳሰባቸውና በባሕርያቸው የሰብእና መዛባት (Schizotypal Personality Disorder) እንዳለባቸው ከሚታወቁት ግለሰቦች (በእኛ ሀገር ተጨባጭ ሁኔታ ደግሞ ‹‹እብድ›› ከሚባሉት የህብረተሰብ ክፍሎች) እንድትመደብ ያደርጋታል፡፡ በዚህ ድርጊቷ ምክንያትም ወደ ፖሊስ ጣቢያ ከሔደች በኋላ የበለጠ አስቸጋሪ መሆኑን የተረዱት ፖሊሶች ወደ ጳውሎስ ሆስፒታል ይወስዷታል፡፡ ሆስፒታል እንደደረሰችም ‹‹‹ብር ያለው ደደብ … ደደብ ሁላ … ብር ብቻ … ደደብ የያዘው ብር! የደደብ ብር… ዝም ብሎ መብረር … ብር ብርቅ መስሎሻል … ብ--ር ማለት የደ-ደ-ብ ክ--ብር ነው› ትልና እጇን ከፖሊሶቹ ለማስለቀቅ ጎትታ ጎትታ ሲያቅታት ‹ኡ ኡ ኡ! ብላ እሪታዋን ታስነካዋለች (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 96)*፡፡›››* ዝናሽ *ያልተፈጠሩ ነገሮችን የማየትና የመስማት ሁኔታም* ይታይባታል፡፡ ሌላሠው ምን ይሰማሻል ብሎ ሲጠይቃት ሰዎቹ መድሀኒቱን አትውሰጅ እንደሚሏትና ልጃችንን ትገድያለሽ በማለት እንደሚያንገራግሯት ትተርካለች፡፡

> ‹ተይ ኪኒኑን አትውሰጂ ይቅርብሽ ሊገድሉሽ ነው ይሉኛል፡፡ እስኪ ተው … ኡፍ› አለችና በስጨት በማለት እጇን ስታወናጭፍ፣
>
> ‹እነማን ናቸው እነሱ?› አለ፣ ፊቱን ቅጭም አድርጎ፡፡
>
> ‹ያው የልጁ ባለቤቶች ናቸዋ፡፡ ልጁን ሊገድሉብን ነው ኪኒንና መርፌ የሚሰጡሽ ይላሉ፡፡ ሌሊት መጥተው ደግሞ … ኡፍ … ፍ … አይሰማችሁም ሲያንሾካሹኩ፡፡ ግን መድሀኒት ሰው ይገድላል እንዴ?› ትክ ብላ ስታየው መረበሿን በመረዳት እንዴት ሊያስረዳት እንደሚችል ትንሽ አሰበ፡፡ (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 96)

በዚህም የውስጥ መረበሽ የተነሳ የንግግር፣ የድሪጊት፣ የባሕርይና የስሜት መዛባትን ታሳያለች። ለዚህ የዳረጋትም አረብ ሀገር በአሰሪዋ መደፈሯ መሆኑን ቀጥሎ ከቀረበው ማስረጃ መገንዘብ ይቻላል።

> [አቶ በድሉ] ‹ዝናሽ ለኛ አሳልፋለሁ ብላ አረብ አገር ሒዳ ነው ከንቱ ተቀጭታ እንደዋዛ የቀረች› አሉና በትካዜ ተዋጡ። (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 193)

> [ዝናሽ] ‹አዎን … ትልቁ እኮ አባቱን ቁጭ ነው፣ ምን ያደርጋል ብር ብቻ … ደደብ አረብ ሆነ እንጂ …› አለች፣ ፊቷ ልውጥውጥ ብሎ። (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 149)

> [ሌላሠው] ‹የመጀመሪያ ልጇን የወለደችው የቤተሰቦቿን ድኽነት ለመቅረፍ አረብ አገር ሄዳ ሰው ቤት ስትማስን ጌታዋ አስገድዶ ደፍሯት ነው። ምን የመሰለች ልጅ አእምሮዋን ስታ ህመምተኛ ሆና መጣች። የምታዩት ትልቁ ልጅ የዛ እርግዝና ውጤት ነው› ብሎ፣ ጸጥ ብለው የሚሰሙትን ሰዎች አየት አየት አድርጎ ንግግሩን ቀጠለ። (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 214)

በድህነት ውስጥ ከመኖር ለማምለጥ ወደ አረብ ሀገር የሸሸችው ዝናሽ ያላሰበችው ችግር ድንገት ሲጋረጥባትና ቤተሰቦቿ ለፍሬ ሲጠብቋት በአበብዋ መድረቋ ሲታወሳት ውስጣዊ የሰብእና አወቃቀሯ ተዛባና ‹‹እብድ›› ለመባል በቃች።

**4.2.5. ውስጣዊ የአእምሮ መዋቅርን መሠረት በማድረግ ሰብእናቸው የተቀረጸ ገፀባህርያት**

አርሴማ፣ ዲንሳና ሲስተር ዘቢባ ሰብእናቸው በውስጣዊ አእምሮ አወቃቀራቸው አማካኝነት የተገነባ ገፀባህርያት ናቸው።

የሌላሠውና የንጹሕ መንትያ ልጆች (አርሴማና ዲንሳ) እናትና አባታቸው በፍቅር ጨዋታ በሚላፉበት ወቅት አርሴማ ለአባቷ ዲንሳ ደግሞ ለእናቱ የሚያደርጉት አገዛ በተለይ በህጻናት ላይ የሚስተዋለውን የኤዲፐሳዊ ቅዠት (Oedipus Complex) ኢሌክትራዊ ቅዠት (Electra Complex) ሰብእና አመላካች ነው።

> ከጎን መኝታ ቤት የእነሱን ልፊያ የሰማችው ትንሿ አርሴማ በሩን ብርግድ አድርጋ ስትበርር መጣችና  አልጋው ላይ ፊጥ አለች። አባቷ ከታች፣ እናቷ ከላይ ሆና ስታይ እንደለመደችው ለአባቷ ለመርዳት የእናቷን አንገት ይዛ ለማውረድ ስትሞክር ሌላሠውም እንደተጎዳ አስመስሎ

‹ኸልፐ ኸልፐ…አርሲ…ኡሀ…ኡሀ…› ሲል፣ በበለጠ ሞራል ንጹህን ከሌላሠው ላይ ለማውረድ ትግሏን ቀጠለች፡፡

ዘግይቶ የደረሰው የአርሴማ መንትያ ወንድም ዲንሳ ተንደርድሮ አልጋው ላይ ወጣና በተራው ለእናቱ እርዳታ የአባቱን አንገት ይዞ ለመጣል ትግል ውስጥ ገባ (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 56-57)፡፡

በዚህ የሚጀምረው የልጆች የእናት አባት ውስጣዊ ፍላጎት ወይም ኤዲፐሳዊና ኢሌክትራዊ ቅዠት በዚህ አያበቃም፡፡ አርሴማ በህፃን ጉልበቷ የአባቷን የጣት ቀለበት ለማውለቅ ስትታገል ድምጽ አውጥታም እኔ አንተን ነው የማገባ ስትል ትደመጣለች፡፡

**አርሴማ አባቷ ጣት ላይ ያለውን ቀለበት ለማውለቅ ያቅሚን ታግላ ሲያቅታት፣**

‹ባቢ ይሄ ምንድን ነው? ማነው የገዛልህ?› አለችው፡፡…

‹ይሄ ቀለበት ይባላል፡፡ ማሚ ናት የሰጠችኝ፡፡ እኔና እሷ ባልና ሚስት ስንሆን ነው የገዛችልኝ፡፡ እኔም እርሷ ያደረገችውን ገዛሁላት፡፡›…

‹ለኔስ መቼ ነው የምትገዛልኝ ታዲያ?› ስትለው፣ …

‹አርሲ … አንቺ የኔ ልጅ ነሽ፡፡ እነደዚህ አይነት ቀለበት ለሚስትና ለባል ብቻ ነው የሚሰጠው፡፡ ሌላ አይነት ቀለበት ግን ወደ ፊት ትምህርት ስትጨርሺ እኔና ማሚ እንሰጥሻለን፡፡›

**‹አይ … እኔ የማገባው አንተን ነው፡፡ ማሚ ከፈለገች ዲንሻን ታግባ …›** (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 57-58)፡፡ (አጽንኦት ተጨምሯል)

ሌላሠው እሷ ልጁ እንደሆነች፣ የእሱ ሚስት ንጹሕ እንደሆነችና መጋባት እንደማይችሉ ሲገልጽላትም፣ ማሚ ከፈለገች ዲንሳን ታግባ የሚል መልስ በመስጠት በውሳኔዋ ትጸናለች፡፡

የሁለቱን ቃለ ምልልስ ሲያዳምጥ የነበረው ዲንሳም ለእህቱ የአጸፋ መልስ ይሰጣል፡፡ ‹‹‹**እኔ የማገባው ማሚን ነው፡፡ ባቢ ከፈ[ለ]ግክ አልሺን አግባ**› ብሎ፣ እናቱን እንቅ አድርጎ ሲይዝ ሌላሠውና ንጹሕ ተያይተው ፈገግ አሉ (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 58) (አጽንኦት ተጨምሯል)፡፡››

ወንድሟ ዲንሳም ንጹሕን ማግባት እንደሚፈልግና ሌላሠው አርሴማን ማግባት እንዳለበት ሀሳቡን ይሰነዝራል፡፡

አርሴማና ዲንሳ ለእናትና አባታቸው ያላቸው ኤዲፐሳዊና ኢሌክትራዊ ቅዠት ያሉበትን ሥነ ልቦናዊ የእድገት ደረጃ ጠቋሚና በዚሁ እድሜያቸው የሚዳብረውን ሰብእና ያመለክታል፡፡ ይህም ግብታዊ የሆነውና ለማህበራዊ ጉዳዮች የማይጨነቀው እንዲሁም ፍላጎትን ለማሟላት ብቻ የሚተጋው ኢድ በአርሴማና ዲንሳ ሰብእና አወቃቀር ላይ ከፍተኛውን ድርሻ እንደያዘ ያመለክታል፡፡

ሲስተር ዘቢባ ሰብእናዋ ውስጣዊ የአእምሮ መዋቅርን መሠረት በማድረግ የተቀረጸች ገፀባህርይ ስትሆን በኑሮዋ የተሟላላት፣ በስራዋስኬታማና ደስተኛ፣ ለሰው ቅን አሳቢ፣ ደግ፣ ርህሩህ ናት፡፡ በልቦለዱ ውስጥም መልካም ሰብእናን ተላብሳ ቀርባለች፡፡ ለምሳሌ ምስጢር ከሳንቾ ጋር በሲስተር ዘቢባ ቤት ለእራት ተጋብዛ ስትሔድ በምታደርገው ምልልስ ‹‹ሲስተርዬ እኮ ነፍሴ ናት፡፡ እናት ነገር የሆነች ሰው (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 124)››፡፡  ስትል ትታያለች፡፡ ከምስጢር አባባል ለመረዳት እንደሚቻለውም ሲስተር ዘቢባ የእናትን ያህል ተወዳጅ ሰብእና ያላት እነደሆነች ነው፡፡

ባለቤቷ አቶ ሲራጅም ስለ መልካም ሰብእናዋ ለእነ ሌላሠው ምስክርነቱን ሲሰጥ ይስተዋላል፡፡

> ‹ይኼ ሁሉ የዘቢባ ስራ ነው … ይሄው ሠላሳ አንድ ዓመታችን ከተጋባን፡፡ ሁል ቀን እንዳስገረመችኝ ነው፡፡ እዚህ ቤት ውስጥ የምታዩትም ሆነ ደጅ ያለው የሷ የእጅ ስራ ነው፡፡ ሆስፒታል ለሚያውቃት ሰው ነርስ ብቻ ትመስለዋለች፡፡ እንደሷ አይነት ሁለገብ የሆነ ሰው እኔ በበኩሌ አይቼም አላውቅም፡፡ አላህ እንዴት ቢወደኝ ነው እንደሷ አይነት ሚስት የሰጠኝ ብዬ ሁልጊዜ እደነቃለሁ› ሲል፣ እንደ ማፈር ብላ ተሽኮረመመችና፣
>
> ‹አየ ሲራጅ አንተ መቼም በጣም ታበዛዋለህ …› ስትል፣ ምስጢር አጠገቧ ያለችውን ሲስተር ዘቢባን እቅፍ አደረገቻት፡፡ (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 129)

በመጽሐፉ ሌላኛው ክፍል ላይ የተገለጸው የዘቢባ ድርጊትም የመልካም ሰብእናዋ አመልካች ነው፡፡ ‹‹[ሌላሠው] የቤት ሰራተኛ አድርጎ የቀጠራት ከሁለት ልጆቿ ጋር መግቢያ አጥታ ስትንከራተት እነ ሲስተር ዘቢባ ቤት ለጊዜው ያሳረፏት የሰራተኛቸው እህት ናት (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 395)፡፡›› ሲስተር ዘቢባ በአዲስ አበባ የኑሮ ሁኔታ ሁለት ልጅ ያላትንና ምንም የስጋ

ዝምድና የሌላትን የሰራተኛዋ እህት ተቀብላ እንድታርፍ ማድረጓ መልካም ሰብእና እንዳላት አመላካች ነው፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለውና ለሞራል እርካታን የሚሰጥ ነው፡፡ በዚህም ሲስተር ዘቢባ የሱፐር ኢጎ አእምሯዊ መዋቅር ባለቤት ናት ማለት ይቻላል፡፡

ሲስተር ዘቢባ ከገፀባህርያት ጋር በምታደርጋቸው ቃለ ምልልሶች ሁሉ አወንታዊ አስተሳሰቧና ለሰው ያላት መልካም እይታ ይንጸባረቃል፡፡ በሌላ አገላለጽ ሲስተር ዘቢባ የእኩይ ገፀባህርያት ተቃራኒ በመሆን ሰናይ ገፀባሕርይ (Virtuous Character) ሆና ቀርባለች፡፡ ምክንያቱም ሲስተር ዘቢባ በድርጊቷ፣ በአስተሳሰቧና በጸባይዋ ከእኩይ ገፀባህርያት ተቃራኒ ናት፡፡ በአንጻሩ የግብረ ገብነት ደረጃዋ ከፍ ያለ፣ በአስተሳሰቧና በምግባሯ መልካም አቅጣጫን የያዘች ገፀባህርይ ናት፡፡ ለዚህም በሰብእና አወቃቀሯ ረገድ የሱፐር ኢጎ አእምሯዊ መዋቅር ከፍተኛውን ድርሻ ይዟል፡፡

## 4.3. የገፀባህርያት ሰብእና ውቅር ኪናዊ ፋይዳ በሌላ ሰው ረጅም ልቦለድ

የገፀባህርያት ሰብእና ውቅር በ*ሌላ ሰው* ውስጥ አንድም በጭብጥነት የቀረበውን የሥነ ልቦና ጉዳይ ሳቢና ማራኪ አድርጎ ለማቅረብ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ይህም የሚሆነው የገፀባህርያት የኋላ ታሪክ በምልሰት አማካኝነት ቀስ በቀስ እንዲቀርብ በማድረግ ነው፡፡ ሁለትም ለቴክኒክ ማዋቀሪያነት በተለይ ደግሞ ገፀባህርያት በሚፈጽሙት ድርጊት ንግርን፣ በትዝታ ወደ ኋላ በመመለስ ደግሞ ምልሰትን ለማዋቀር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ አብዛኛዎቹ በንግር ወይም ለወደፊት ጥቁምታነት የቀረቡት የገፀባህርያት ድርጊቶች ተምሳሌታዊ በሆነ መልኩ የቀረቡና ተተርጉመው የሚገኙ ናቸው፡፡ ቀጥሎ የቀረቡትም ለዚህ አስረጅዎች ናቸው፡፡

ሌላሠው በከፊል መልካም ሰብእናን ተላብሶ የቀረበ ገፀባህርይ ቢሆንም ከአካባቢ ጋር በሚኖረው መስተጋብር መልካም ሰብእናው ሲደናቀፍ ይታያል፡፡ ንጹህ ደግሞ በከፊል የራስ ወዳድ ሰዎችን ሰብእና ተላብሳ ቀርባለች፡፡ ይህ ሰብእናቸውም በተለያዩ ትእምርቶች አማካኝነት እየተንጸባረቀ ለቴክኒክ ማዋቀሪያነት አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ ሌላሠውና ንጹሕ ላንጋኖ ለመዝናናት በሔዱበት ወቅት ስለ ወደፊት እቅዳቸውና ሁኔታቸው ከሐይቁ ዳርቻ ባለው አሸዋ ላይ ተቀምጠው በሚነጋገሩበት ወቅት ሌላሠው አሸዋ ጨብጦ ሲበትን ይታያል፡፡ ይህ ሁኔታ በህይወት ዘመኑ ሲመኘው የነበረው ክሊኒክ ከፍቶ ማህበረሰቡን የማገልገል ምኞትና የያዘው ዓላማ እንዲሁም ትዳሩ ድንገት እንደሚበተን የሚጠቁም ነው፡፡ ‹‹[ሌላሠው] በእጁ የያዘውን አሸዋ ጭምቅ አድርጎ መልሶ በተነው (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 158)፡፡›› በእርሱ አባወራነት ሲመራ የነበረው ቤተሰብ በሁለቱ ጥንዶች ዓላማ መለያየት ምክንያት ድንገት ሲበተን ይስተዋላል፡፡

ንጹሕ ደግሞ በበኩሏ ‹‹ለረጅም ደቂቃ ተጠንቅቃ ስትገነባ የቆየችውን የሚያምር የአሸዋ ቤት ባንዴ አፈራረሰችው (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 162)፡፡ ይህም በንግር መልኩ አስቀድሞ ጥቆማ ለመስጠት የተቀመጠ ተምሳሌታዊ ሁነት ነው፡፡ በተለይ የንጹህ ራስ ወዳድነት እነዚህን ተምሳሌታዊ ድርጊቶች ለመፈጸም ያስገድዳታል፡፡ በሌላ አንፃር ደግሞ ሌላሠው ቤተሰቡን የበተነበትና ትዳሩን ያፈራረሰበት ዓላማው ድንገት በሚከሰት አለመግባባት ብትንትኑ እንደሚወጣ ጥቆማ የሚሰጥ ነው፡፡ ቀጥሎ የቀረበው በሁለቱ ጥንዶች መካከል የሚታየው የሀሳብ ልዩነትም ተጨማሪ ማስረጃ ነው፡፡

> ‹እሺ … ምን አድርግ ነው የምትይኝ? ይሄ ሁሉ ስራ ከተጀመረ በኋላ ጥዬ ልሄድ? ወይስ … ዛሬ ጠዋት ስራ መግባቴና መቅረቴ የሚያመጣው ልዩነት አለ? እንደሱ ከሆነ ደውየላቸው ልቀር እችላለሁ› አለ፣ በስጨት ባለ ድምጽ፡፡
>
> ‹ሌ-ላ … እኔ የምልህ ነገር እኮ የገባህ አይመስለኝም፡፡ ራስህ አስበህ የማታደርገው ነገር ምንም አይጠቅመኝም፡፡ ጉዳዩ ዛሬ ጠዋት ሥራ መግባትህ አለመግባትህ ላይ አይደለም፡፡ ቤተሰቡ ላይ እየፈጠርክ ያለውን ጫና የተረዳኸው አይመስለኝም፡፡ አቅሜንም ፍቅሬንም እየገዘገዝከው ነው፡፡ ቢያንስ ያለችውን ትንሽ ጊዜ ሥራ ስብሰባ ቅብጥርሴ እያልክ የምታጠፋ ከሆነ … ተለያይተን በምንቆይባቸው ወራት በምን አቅም ነው እንደ ቤተሰብ ተያይዘን የምንቆየው?› ተመልሳ ራሷን በሁለት እጇ ይዛ ተቀመጠች፡፡ (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 254)

ንጹሕ የሰራችውን ቤት ማፈራረሷ አንድም ለትዳር መፍረስ መነሻ እንደሆነች ጥቆማ የሚሰጥ ሲሆን ሁለትም በውስጧ ስታሰላስለው የቆየችውን የትዳር ሁኔታ የመፍረሻው ጊዜ መድረሱን ማሳየቷና አዲስ ህይወት ለመጀመር በሒደት ላይ መሆኗን የሚያመለክት ነው፡፡ ይህም በንጹህ ራስ ወዳድ ሰብእና መላበስ የተከሰተ ነው፡፡ ምክንያቱም ራስ ወዳድ ሰዎች የራሳቸውን ጥቅም ብቻ የሚያሰላስሉ ናቸውና፡፡ ንጹሕም ከቀድሞ ጓደኛቸው ጋር ጥቅሟን በማሰላሰል ትዳር ልትመሰርት እንደምትችል በትእምርታዊ ጉዳዮች አስቀድማ ጥቆማ ትሰጣለች፡፡ ይህ የከፋ የራስ ወዳድ ሰብእናዋም ነው ለንግር ማዋቀሪያነት ጥቅም ላይ የዋለው፡፡

ሌላሠውና ንጹሕ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሳዩት ያለው የባህርይ ለውጥ ስላሳሰባቸው ለመመካከርና ለመዝናናት በአሜሪካ ውስጥ የሚገኘውን የግራንድ ካንዬን ግዛት ይመርጣሉ፡፡ ጥንዶቹ ኮሎራዶንና አሪዞናን ለሁለት የከፈለውን የግራንድ ካንዬን ግዛት የመጎብኘታቸው ተምሳሌትም

ወደ ፊት በትዳራቸው መካከል የማያገናኝ ትልቅ ገደል እንዳለ ጠቋሚ ነው፡፡ ለዚህ ያበቃቸው ደግሞ ውስጣዊ የሰብእና አወቃቀራቸውና አካባቢያዊ ሁኔታዎች የፈጠሩት የሰብእና ቅጥ ነው፡፡ ‹‹ሁለቱም በመካከላቸው የተፈጠረው ገደል እየሰፋ እንዳለ በደምሳሳው ቢሰማቸውም፣ ቃል ፈጥረውለትና ስም አውጥተውለት ሊያወሩት አልቻሉም፡፡ የግራንድ ካንየኑ ገደልስ መች ባንድ ቀን እንዲህ ሰፍቶ ሁለት ግዛቶችን ማዶ ለማዶ ከፈለ፡፡ ሁለቱም ይህ ድንቅ ገደል እንዴት ሊፈጠር እንደቻለ መላምት በመስጠትና በመገረም ተጫወቱ (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 312)፡፡›› በሌላ በኩል ደግሞ በሁለቱ ግዛቶች መካከል ያለው ድልድይ ጥንዶቹ ተመልሰው ሊገናኙ እንደሚችሉ በተምሳሌታዊ አቀራረብ በንግር መልኩ የተገለጸ ነው፡፡ ሁለቱ ግዛቶች ቢለያዩም በድልድይ ገደሉን አቋርጠው እንደሚገናኙ ሁሉ ለፍቺ ተዳርገው የነበሩት ጥንዶችም በምስጢር አማካኝነት እንደገና ይገናኛሉ፡፡

በሌላ የመጽሐፉ ክፍል ላይ አንድ አምስት ወይም ስድስት ዓመት የሚሆነው ልጅ ከእናቱ ጋር ለህክምና ሌላሠው ጋ በመጣበት ወቅት ድንገት የንጉሕንና የልጆቹን ፎቶ ሲመለከት ከእጁ አምልጦ ይወድቅና ፍሬሙ ይሰበራል፡፡

> … በፍጥነት መቀመጫው ላይ ቆመና ተንጠራርቶ የንጉሀንና የልጆቹን ፎቶ ብድግ አድርጎ፣ ‹ማናቸው እነዚ?› አለ ወደ ልጆቹ እየጠቆመ፡፡
>
> ‹እነሱ ልጆቼ ናቸው፡፡›
>
> ‹ይቺስ?› ብሎ ንጉህን ሊጠቁም ሲሞክር ፍሬሙ ከጁ አምልጦ ወደቀና መሬት ላይ ወድቆ መስተዋቱ ተከሰከሰ፡፡ (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 345)
>
> [ሌላሠው] የተሰበረውን የፎቶ መስታዋት ሰብስቦ ቆሻሻ መጣያ ውስጥ ጣለ፡፡ አቧራ የጠጣውን ፎቶ ጠራረገና ፒያኖው ላይ በፊቱ ደፍቶ አስቀመጠው፡፡ (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 347)

የልጁ ሰብእና አወቃቀር ኢድ የአእምሮ መዋቅር የሚያይልበትና ያየውን ሁሉ ለመንካትና የራሱ ለማድረግ የሚታገል ነው፡፡ ለህክምና በመጣበት ወቅትም በቀጥታ ያለ ምንም ይሉኝታ ውስጣዊ ምኞቱን ለማሟላት የፎቶ ፍሬሙን መመልከት ይጀምራል፡፡ ይህ አይነት ይሉኝታ ቢስነትና ከውስጥ ለሚመጣ ስሜት ሁሉ ወዲያውኑ ምላሽ መስጠት የኢድ ሰብእና ውቅር የሚያይልባቸው ሰዎች አይነተኛ ባህርይ ነው፡፡ ልጁም ይህንን ሰብእና የተላበሰ ነው፡፡ ይህም

የሌላሠውና የንጉሕ ትዳር እንክትክቱ ስብርብሩ እንደሚወጣ ለማሳየት ታስቦ የቀረበ ሲሆን ሌላሠው ፎቶግራፉን አንስቶ ፒያኖው ላይ በፊቱ ደፍቶ ያስቀመጠው ምንም እንኳ በስራ ብዛት ምክንያት ቢሆንም ለትዳሩ ጀርባ መስጠቱን አመልካችም ነው፡፡ የሌላሠው ሰብእና በንጉሕ የራስ ወዳድነት ሰብእና መላበስ ምክንያት እየተሸረሸረ በመሔዱ እሱም ለሰብእና መዛባት ተጋልጧል፡፡ ለዚህም ነው ሀሳቡን በትእምርት ለመግለጽ ፎቶግራፉን ደፍቶ ማስቀመጡ፡፡

በሁለቱ ጥንዶች መካከል የነበረው ምክክር በንጉሕ ራስ ወዳድ ሰብእና ምክንያት መግባባት ላይ ለመድረስ ስላላስቻላቸው ንጉሕ አኩርፋ ትንሽ ብቻዬን የምቆይበት ጊዜ ስጠኝ ብላ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ትሔዳለች፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ደግሞ ምዕራብ የሲያል ተምሳሌት ነው፡፡ ቀኑን ሙሉ ብርሀኗንና ሙቀቷን ለፍጥረታት ሁሉ ስትለግስ የዋለችው ፀሐይ ወደ ምዕራብ ስትጠጋ ብርሀኗ ተዳክሞ የጨለማ ጉልበት እየጠነከረ ሙቀቷ ቀዝቅዞ ቁርና ብርድ እየሰገረ የሚመጣበት ነው፡፡ ይህም የሁለቱ ትዳር መፍረስ የሕይወት ጨለማንና ቅዝቃዜን ሊያመጣ እንደሚችል በትእምርትነት የቀረበ ነው፡፡ ‹‹[ንጉሕ] ፊቷን አዙራ ነጠላ ጫማዋን በእጇ እንደያዘች፣ ወደ ፀሐይ መጥለቂያ አቅጣጫ በሐይቁ ዳር ስትሄድ፣ እርሱ ደግሞ ግማሽ እግሩን ውሃው ውስጥ እንደነከረ በጀርባው ተጋደመ (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 162)፡፡›› ይህም በንጉሕ የራስ ወዳድነት ሰብእና ምክንያት የተፈጠረ ነው፡፡ በዚሁ ቅጽበት ንጉሕን ለማስረዳትና ለማግባባት ያልተሳካለት ሌላሠው ግማሽ እግሩን ውሀ ውስጥ ይነክርና በጀርባው ይጋደማል፡፡ ይህም ውሀ የንጽሕና ምሳሌ እንደመሆኑ መጠን ንጉሕ በውስጧ ስታሰላስለው የነበረው እኔን ትቶ የቀድሞው ፍቅረኛውን ገነትን ሊያገባ ይችላል፤ እንዲሁም ልጅ እግሯን ምስጢርን ሊያገባ ነው ከሚለው የቅናት መንፈስ ነጻ መሆኑን ጠቋሚ ነው፡፡ ግማሽ እግሩን ብቻ መንከሩ ደግሞ ምናልባት ገነትን ቢያገኛት እንኳ ምን ሊፈጠር እንደሚችል የጠራ ስሜት በውስጡ እንደሌለ ለመጠቆም የገባ ተምሳሌታዊ አገላለጽ ነው፡፡ ይህም ከንጉህ የራስ ወዳድነት ሰብእናና ከሌላሠው ከፊላዊ መልካም ሰብእና መላበስ የመነጨ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ሌላሠው በአንፃራዊነት መልካም ሰብእናን ተላብሶ የቀረበ ገፀባህርይ ነው፡፡

የእነ ሌላሠው ትዳር ለመፍረስ ሊቃረብ እንደሚችል በመጽሐፉ የመጀመሪያው ገጽ አካባቢ ላይ መንትያ ልጆቻቸው በኤዲፐሳዊና ኢሌክትራ ቅዠት የሰብእና ውቅር አማካኝነት በሚያደርጉት ትዕይንት ለአንባቢው ተገልጿል፡፡ ይኸውም አርሴማ ከአባቷ ጣት ላይ ያለውን ቀለበት ለማውለቅ ስትታገል ትታያለች፡፡ ሆኖም ለማውለቅ ሳይሳካላት ይቀራል፡፡ ይህ ሁኔታ ንጉሕ ሌላሠውን ትታ ሚስቱ የሞተችበትን ጎረቤታቸውን ለማግባት እንደምታስብና የተወሰነ ደረጃ

ከሔደች በኋላ እንደምትመለስ የሚያሳይ ነው። አርሴማ ለማውለቅ መታገሏ ንጹሕ ከጎረቤታቸው ጋር የምታደርገውን የፍቅር ግንኙነት ሲጠቁም፣ ለማውለቅ አለመቻሏ ደግሞ ምንም እንኳ ሙከራ ቢደረግም ትዳራቸው እንደማይፈርስ ይጠቁማል።

የምስጢር ሰብእናም በልቦለዱ ውስጥ ለንግርና ምልሰት ማዋቀሪያነት ጥቅም ላይ ውሏል። ምስጢር በማስረሻ ደብዳቤ አማካኝነት በህልሟ የምታየው ትዕይንት ወደፊት ስለሚሆነው ነገርና ስላለፈ ታሪኳ የሚገልጽ ነው። ምስጢር በህይወቷ የገጠሟትን አስቸጋሪ ሁኔታዎች በኢንቁ የአእምሮ ክፍል አግታ በመኖር ላይ እያለች በህልም አማካኝነት ድንገት ይገለጽባታል። በህልም አማካኝነት የቀረቡት ጉዳዮችም የምስጢርን የወደ ፊት ሁኔታዎች ጠቋሚ ናቸው። በመሆኑም ለልቦለዱ ንግር መዋቅር ሰብእናዋ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል።

> [ምስጢር] ደክሟት ኖሮ ብዙም ሳይቆይ ደብዳቤውን እንደ ያዘች እንቅልፍ ይዟት ሄደ።
>
> ሌሊት ላይ የተንኳኳ ነገር ሰምታ ብንን ስትል የመኝታ ቤቷ መስኮት ተከፍቶ ንፋሱ መጋረጃውን ከመስኮቱ ጋር ወዲያ ወዲህ ሲያደርገው አየችና ዘላ ተነሳች። … መጋረጃውን በትክክል ግጥም አድርጋ ሸፍና፣ ዋናውን መብራት አጥፍታ ወደ አልጋዋ ዞር ስትል ትልቅ ስለት የያዘ ሰው ከፊቷ ተገትሮ ስታይ ደርቃ ቀረች።
>
> … ‹ከዚህ ቶሎ ወጥተን መሔድ አለብን› ሲላት፣ በፍርሃት በሚንቀጠቀጥ ድምፅ፣
>
> ‹እኔ ከዚህ የትም አልሔድም› ስትለው፣ ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ አንገቱን ዘንበል፣ አፉን ጠመም አድርጎ፣
>
> መሄዳችንማ የግድ ነው፣ የኔ ፍቅር። ምናልባት የማይሆን ነገር እንዳትሞክሪ [አለና] … በሳሎን በኩል ዋናውን የበረንዳ በር ከፍቶ ወጡ። … ወደ ሲ ኤም ሲ አቅጣጫ አዙረው ፍጥነታቸውን ጨምረው ሲገሰግሱ ከኪሱ ውስጥ ጥቁር ሻሽ አወጣ። … አይኗን በሻሹ ሸብ አደረገና እጁን ትከሻዋ ላይ አድርጎ ጸጥ እንዳሉ ጉዟቸውን ቀጠሉ።
>
> … ፍጥነታቸውን እየጨመሩና እየቀነሱ … እየተጣደፉ ሲሔዱ ቆይተው ድንገት ቀጥ አሉ። ከመኪናው ሲወርዱ ዓይኗ ላይ ያሰረውን ሻሽ ሲያወርድላት የት እንዳለችም ለማወቅ አልቻለችም። ለመጥለቅ አፋፍ ላይ ባለችው ጨረቃ ብርሃን በአካባቢው የሚታይ ሌላ ቤት እንደሌለና ከቤቱ ጀርባ ያለውን ጫካ ለማየት ብቻ ችላለች።

> ቤት ከገቡ በኋላ ከመደርደሪያ ላይ ያለውን ትልቅ ፋኖስ ለኮሰው፡፡ … ባንድ እጁ ክንዷን አፈፍ አድርጎ ወደ ጓዳ ካለ አንድ ክፍል ይዟት ገባ፡፡ ‹እዚህ ጠብቂኝ፡፡ የሞኝ ሥራ ለመሥራት እንዳትሞክሪ› ብሎ በሩን ዘግቶባት ተመልሶ ወጣ፡፡ ክፍሏ መስኮት የላትም፡፡ ጣራው በጭስ የጠቆረና ከፍ ያለ ነው፡፡
>
> ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከውጪ ያለው በር በሃይል ተዘጋ፡፡ ብዙም ሳይቆይ መኪናዋ ጮሃ ስትሄድ ተሰማት፡፡ በከፍተኛ ድምጽ እየተሳደበ ወዳለችበት ክፍል ሲመጣ፣ ኮቴውን ሰምታ ውስጧ በፍርሃት ራደ፡፡ በሩን ከፍቶ ሊገባ አለና መልሶ በሃይል ደርግሞት ወደ ሳሎን ተመለሰ፡፡ ወደ በሩ ጠጋ ብላ ስታየው በሩ አለመቆለፉን አረጋገጠች፡፡ ወደ መደርደሪያው ተጠግቶ ፋኖሱን ሊያጠፋ ሲታገል የመውጫ በሩን አቅጣጫ በጥንቃቄ ለማየት ሞከረች፡፡ ልክ ፋኖሱን ሲያጠፋው እሷም ሻማውን አጠፋችው፡፡ (*ሌላ ሰው፣* 2007፣ 47-50)

ማስረሻ ከቤት ጠልፎ ወስዶ በጭስ ጥቁር ካለች ቤት ምስጢርን ማስቀመጡ የምስጢር ህይወት በሙሉ በጨለማ የተዋጠ መሆኑን የሚገልጽ ሲሆን ይህም ለልቦለዱ ንግር ማዋቀሪያነት ጥቅም ላይ የዋለ ነው፡፡ ማስረሻ ወደ ክፍል ሲገባ ይበራ የነበረውን የፋኖስ መብራት ማጥፋቱም ለምስጢር የህይወት ብርሀንን ያህል የሆናት የሳንቾ ህይወት በማስረሻ አማካኝነት ሊጠፋ እንደሚችል የሚያሳይ ነው፡፡ ማስረሻ መልሶ ፋኖሱን ማብራቱም በሳንቾ ላይ የሚያደርገው ግድያ ሊከሽፍ እንደሚችል ያመለክታል፡፡ ምስጢር ካጠገቧ ያለውን ሻማ ማጥፋቷ ደግሞ በእሷ ፍቅር ምክንያት እራሱን እንደ ሻማ እያቀለጠ  የሚኖረው የማስረሻ ህይወት ሊጠፋ እንደሚችል ጠቋሚ ነው፡፡ እነዚህ ትእይንቶች የማስረሻንና የሳንቾን የወደፊት እጣ ፋንታ በንግር የሚጠቁሙ ሲሆኑ የምስጢርን የሰብእና መቆርቆዝ ለመግለጽም አገልግለዋል፡፡ ይህ ትእይንታዊ ጉዳይ የሚከሰተውም አካባቢያዊ ሁኔታዎች በምስጢር ሰብእና ላይ ባሳደሩት ተጽእኖ ነው፡፡ ምስጢር በአባቷ (በአሳዳጊዋ) አማካኝነት በደረሰ በደል ለሰብእና መዛባት ችግር ትጋለጣለች፡፡ ይህን የሰብእና መዛባት መንስኤ ለሌላሠው ለማስረዳትም ወደ ኋላ ተመልሳ ታሪኳን መናገር ትጀምራለች፡፡

> በሁለተኛው ቀን ስክር ብሎ መጥቶ …› ብላ፣ እንደገና መንታ መንታ እንባዋ ዱብ ዱብ እያለ ማልቀስ ስትጀምር ሲያባብላት ረጅም ደቂቃ ወሰደበት፡፡

[የ]ዛን ሌሊት በግድ ከደፈሯት በኋላ ህይወቷ ሁሉ እንዴት እንደተመሰቃቀለና ከቤት ጠፍታ አክስቷ ጋ እንደገባች በዝርዝር ነገረችው። ይህም ወንዶችን ለማመንም ሆነ ራሷን ያለ መከልከል ለሌላ ሰው ለመስጠት የፈጠረባትን ችግር ልታስረዳው ሞከረች። (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 272)

በሁለቱ ገፀባህርያት መካከል የተካሔደው የሀሳብ ልውውጥም ምልልስንና ምልሰትን በተመሳሳይ ሁኔታ ለማዋቀር ጥቅም ላይ ውሏል። ደራሲው ይህን የምስጢር ሰብእና ያዋቀሩበት መንገድ ታሪኩ አንድ ጊዜ ዝርግፍ ብሎ እንዳይቀርብና አሰልችነትን እንዳይፈጥር አድርጎታል። እንዲሁም ተደራስያን የራሳቸውን ፈጠራ እየጨመሩና እየተመራመሩ ንባባቸውን እንዲያካሒዱ አግዟቸዋል። ይህም ሊሆን የቻለው የምስጢር ሰብእና መዛባት መንስኤን ለመግለጽ በተደረገ ሙከራ ነው።

የማስረሻ ራስ ወዳድ ሰብእናም ምልሰትን ለማዋቀር ከፍተኛ ጠቀሜታን አበርክቷል። ይኸውም ማስረሻ ሰብእናውን ከእናቱ እንደወረሰ ከሌላሠው ጋር በሚያደርገው ምልልስ የቀረበ ሲሆን ይህንንም ሲያጋራ ወደ ኋላ በመመለስ ምልሰትን ለመጠቀም ተገዷል። ‹‹‹[እናቴ] ናት ተስፋ አትቁረጥ … አባትህ ተስፋ ስላልቆረጠ ነው እኔን ያገኘው ብላ ነገሩን ተስፋ አስቆርጦኝ በፍቅር ህመም ሳቃስት የምታበረታታኝ› አለ አይኑ እየረጠበ (ገጽ፣ 280)።›› ማስረሻ ሰብእናው የተዛባበትን መንገድ ወደ ኋላ መለስ ብሎ በማስታወስ በእናቱ ገፋፊነት እንደጀመረ በትረካ ይገልጻል። ማስረሻ ለማህበራዊ ህግና ደንቦች የማይጨነቅ ሰብእናውን በቤተሰቡ ተጽእኖ ምክንያት በተላበሰው ሲሆን ይህ ሰብእናውም ለምልሰት ማዋቀሪያነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል።

ሌላሠው አማኑኤል ሆስፒታል በሽተኞችን በመጎብኘት ላይ እያለ ከዕለቱ ኃላፊ ነርስ ጋር በሚያደርገው ቃለ ምልልስ የዝናሽ የሚረዳት አካል አለመኖርና አባቷም በልመና የሚተዳደሩ መሆናቸው የተገለጸበት መንገድ የዝናሽን የወደፊት ተስፋ የሚያጨልም ነው። ‹‹‹ኡ-ይ ዶክተር ሌላሠው … አባቷ ድክም ያሉ ሽማግሌ ናቸው። ለራሳቸውም በልመና ነው የሚተዳደሩት። …. እንዲያው ምንም ተስፋ ያለውም አይመስለኝም።› ስትል፣ ክፍሉ በጨለምተኛ ድባብ ተሞላ (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 94)።›› ይህ የኃላፊ ነርሷ አገላለጽ ዝናሽ ወደፊት የሚገጥማት ዕድል ጽልመት እንደሆነ ይጠቁማል። በቴክኒክ ጠቀሜታውም በንግር መልኩ ወደፊት ሊከሰት የሚችለውን ነገር ለአንባቢ ጠቁሞ ያልፋል። በጥንቃቄ የሁነቶችን ቅደም ተከተል በአግባቡ እየመረመረ የሚያነብ ተደራሲም የዝናሽ የህይወት መስመር በጽልመት መዘጋቱን የሚረዳው

ከዚሁ ንግግር ነው። ይህም ገና አስቀድሞ የዝናሽ ሰብእና በሰዎች አማካኝነት በመዛባቱ የወደፊት ህይወቷም ተስፋ የሌለው እንደሆነ በሚጠቁም መልኩ ቀርቧል።

የሲራክ ራስ ወዳድ ሰብእናን ተላብሶ መቅረብና በታህታይ ምስቅልቅል መሰቃየት ለልቦለዱ ምልሰት ማዋቀሪያነት ጥቅም ላይ ውሏል። ሲራክ ለታህታይ ምስቅልቅል የዳረገው ሁኔታም ‹‹የገረድ ልጅ›› እየተባለ ማደጉ እንደሆነ ይገልጻል። ‹‹ሳልፈልግ የተወለድኩ የገረድ ልጅ መሆኔን፣ ዛሬ ሳይሆን ገና በልጅነቴ ነው ያወቅሁት። አባታችን ከሞተ በኋላ … ያቺ ክፉ የእንጀራ አያቴ ልበላት እንጂ፣ እሷ እናቴ ልትሆን አትችልም … ያሳየችኝን ስቃይ ሳስበው እናቴ ባለመሆኗ ደስ ይለኛል (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 126)።›› ሲራክ ቀደም ሲል የደረሰበትን በደል ለማካካስ ጥረት የሚያደርግና ሰዎችን ለመበቀል የሚነሳሳ ራስ ወዳድ ሰብእና ያለው ነው። ይህ ራስ ወዳድ ሰብእናው በአስተዳደጉ ምክንያት የተላበሰው ነው። የሚያሳየው ሰብእና አስገድዶት የኋላ ታሪኩን በምልልስ የሚያቀርብበት ሁኔታም ምልሰትን ለማዋቀር አገልግሏል። ሲራክ ኢንቁ በሆነው የአእምሮው ክፍል ውስጥ ታጭቆ የኖረውን አስተዳደጉን ‹‹የገረድ ልጅ›› የሚል ዘለፋ በሚሰማበት ጊዜ በድንገት በኢድ ገፋፊነት ታምቆ የኖረውን አስተዳደጉን ዝርግፍ አድርጎ ለመናገር ይገደዳል። ይህም ለልቦለዱ ምልሰት ማዋቀሪያነት ጥቅም ላይ ውሏል።

ዳርጌ የጥገኝነት ሰብእናን ያዳበረ ገፀባህርይ ነው። ለዚህም አስተዳደጉ ዋነኛው ምክንያት ነው። ይህንን አስተዳደጉን ለእነ አርሴማና ንዋይ በሚተርክበት ወቅት ወደ ኋላ መለስ ብሎ አስተዳደጉን ለመፈታሽ ተገዷል። ይህም ለልቦለዱ ምልሰትን ለማዋቀር አስችሎታል።

> [አርሴማ] ‹አንተ ቤተሰቦችህ እዚህ ሰፈር ናቸው?› ስትለው፣
>
> ‹እናቴ በልጅነቴ ነው የሞተችው … አውሬው ነው የገደላት … አባቴን አላውቀውም› አለ።
>
> ‹የምን አውሬ?› አለ፣ ንዋይ ግራ ገብቶትና ደንግጦ።
>
> ‹አይ ጅብ ምናምን መስሎህ ነው። ቫይረሱ ነው … አውሬው የምንለው› አለ፣ በሐዘን የተሸረበ ፈገግታው ብልጭ ብሎ እየጠፋ። (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 2010)

ዳርጌ ወላጆቹን በልጅነቱ ስላጣና በሌሎች ድጋፍ ህይወቱን መምራት ስለለመደ የጥገኝነት ሰብእናን እንደገነባ ለእነ አርሴማ የሚናገረው በምልሰት ወደ ኋላ ሔዶ አስተዳደጉን በማውሳት

ነው፡፡ ይህም ሰብእናው በልቦለዱ ውስጥ ምልሰትን ለማዋቀር ጥቅም ላይ እንደዋለ የሚጠቁም ነው፡፡

ወይዘሮ ኤደን አንድ ድርጊት ጥሎት ባለፈ ጠባሳ የሚሰቃዩ ናቸው፡፡ ይህንንም ለሌላሠው በሚያማክሩበት ወቅት በሚያደርጉት ምልልስ ይገልጻሉ፡፡ ‹‹አ-ባ-ቴንና ወን-ድ-ሜን ዓይኔ እያየ ነው የገደሏቸው፡፡ ሻቢያ ናችሁ ብለው ደጃፋችን ላይ ደፍተዋቸው ሄዱ፡፡ እኔ ያኔ ወጣት የኮሌጅ ተማሪ ነበርኩ፡፡ ታናሽ ወንድሜ ብቻ ሸሽቶ ወደ ጫካ ገባ፡፡ እኔም ብዙም ሳይቆይ እስር ቤት ተወሰድኩ (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 83)፡፡›› ወይዘሮ ኤደን የሥነ ልቦና ስቃያቸውን ለሌላሠው ለማስረዳት ቀደም ሲል በህይወታቸው የደረሱ መጥፎ ድርጊቶችን ወደ ኋላ ተመልሰው በማስታወስ አቅርበዋል፡፡ ይህም በልቦለዱ ውስጥ ምልሰትን ለመገንባት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ወይዘሮ ኤደን በህይወት ዘመናቸው ብዙ የህይወት ጠባሳዎችን አሳልፈዋል፡፡ እነዚህን የህይወት ጠባሳዎች በኢንቁው የአእምሮ ክፍላቸው ውስጥ አርቀው ለማስቀመጥ ቢታገሉም በእንቅልፍ እና በቀን ቅዠት አማካኝነት እየተገለጠ ለሰብእና መዛባት ዳርጓቸዋል፡፡ ለዚህ የሰብእና መዛባት የዳረጋቸውን ምክንያት ለሌላሠው የሚናገሩበት ሒደት ለልቦለዱ ምልሰት ማዋቀሪያነት አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡

በአቶ ገብረመድህን የተከሰተው የመርሳት በሽታና ያሉበት የሰብእና መዛባትም የምልሰት መዋቅሩ አካል ነው፡፡ ይኸውም አቶ ገብረመድህን ሌላሠው ጋ ለህክምና በሔዱበት ወቅት መስከረም 1967ን ብቻ እንደሚያስታውሱ ይናገራሉ፡፡

> [ሌላሠው] ‹አቶ ገብረመድህን … የዛሬን ቀን ይነግሩኛል? ቀኑን ወሩንና ዓመተ ምህረቱን?› ሲል ትኩር ብለው አዩት፡፡
>
> ‹መስከረም ሁለት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስድሳ ሰባት …› አሉ፣ በጣታቸው ለመቁጠር እየሞከሩ፡፡ (*ሌላ ሰው*፣ 2007፣ 297)

የአቶ ገብረመድህን የሰብእና መዛባት በልቦለዱ ለምልሰት ማዋቀሪያነት በሚያመች መልኩ ተቀርጾ ቀርቧል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና አስተያየት

## 5.1. ማጠቃለያ

የገፀባህርያት ሰብእና ውቅር በበምህረት ደበበ *ሌላ ሰው* ረጅም ልቦለድ ውስጥ፤ ከፍሮይዳዊ ፍካሬ ልቦናዊ ሒስ አንፃር በሚል ርዕስ የገፀባህርያትን ሰብእና ውቅር ለመመርመር የተካሔደው ይህ ጥናት አይነታዊ የምርምር ሥነ ዘዴንና ገላጭ የጥናት ንድፍን በመከተልና በተመረጠው ረጅም ልቦለድ ላይ ጥልቅ ንባብን አካሒዶ መረጃዎችን በመሰብሰብ በፍሮይዳዊ ፍካሬ ልቦና ንድፈ ሀሳባዊና ትወራዊ ማህቀፎች በመታገዝ ጽሑፋዊ ትንታኔ አድርጓል፡፡ የገፀባህርያቱ ሰብእና አወቃቀር ትንተናም ከፍሮይዳዊ የሰብእና ሞዴሎች አንፃር የተካሔደ ሲሆን የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡ ደራሲው የተለያየ ማህበረ ባህላዊ ዳራ ያላቸውን ገፀባህርያት ከተለያየ ማህበራዊ እርከን ላይ እየጨለፉ አቅርበዋቸዋል፡፡ ገፀባህርያቱ ግማሾቹ በጎዳና ህይወትና በድህነት አረንቋ የሚማቅቁ ግማሾቹ በሀብት የሚንፈላሰሱ እንዲሁም በህመምተኛነትና በሐኪምነት የሚከሰቱ ናቸው፡፡ አብዛኛዎቹ ደግሞ በሰብእና መዛባትና በተለያዩ የአእምሮ መቃወስ በሽታዎች የሚማቅቁ ናቸው፡፡ ገፀባህርያት ወደ አእምሮ ህክምና ማዕከል እንዲሔዱ በማድረግ ከሀኪሞቻቸው ጋር በሚደረግ ቃለ ምልልስ የኋላ ታሪካቸው እንዲነገር ተደርጓል፡፡ የሚነገረውም በአንድ ቦታ ላይ ዝርግፍ ብሎ ሳይሆን የልብ ሰቀላን በሚፈጥር መልኩ ከሌሎች ታሪኮች ጋር እየተሰባጠረ ነው፡፡ በዚህ መልኩ የቀረበው ታሪክ ለልቦለዱ ንግርና ምልሰት ማዋቀሪያነት ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ የበሽታዎቻቸው መንስኤዎችም ውስጣዊ፣ ቤተሰባዊና አካባቢያዊ ሲሆኑ በሽታው ከሚፈጥርባቸው የሰብእና መዛባት ለማምለጥም የተለያዩ ሥነ ልቦናዊ የጭንቀት መከላከያ ዘዴዎችን ሲጠቀሙ ይስተዋላሉ፡፡ ደራሲው ሰብእናቸውን በኢድ ኢጎና ሱፐር ኢጎ እንዲሁም በንቁ ኢንቁና ከፊል ንቁ የሰብእና ውቅር በማደራጀት አቅርበዋቸዋል፡፡ ሰብእናቸውን ከኢንቁውና ከጥልቁ የሀሳብ ባህር እየቀዱ በኢድ አማካኝነት እንደወረደ፣ በኢጎ አማካኝነት በተለያዩ ሥነ ልቦናዊ የጭንቀት መከላከያ ስልቶች አማካኝነት እያለዘቡ እንዲሁም ከፍተኛ ሞራላዊ ጉዳዮችን ደግሞ በሱፐር ኢጎ እየሸፈኑ ውስብስብ ማንነታቸውን ይዘው ብቅ እንዲሉ በሚያስችል ሁኔታ ቀርጸዋቸዋል፡፡ እነዚህን የጥናት ውጤቶች መነሻ በማድረግም ቀጥለው የቀረቡት አስተያየቶች ተሰጥተዋል፡፡

## 5.2. አስተያየት

በሌላ ሰው ረጅም ልቦለድ ውስጥ ያልተካተቱ ሌሎች ሥነ ልቦናዊ ጉዳዮች ወደ አንባቢያን ቢደርሱ ተደራስያን በሰው ልጆች ላይ በሥነ ልቦናዊ ጉዳዮች ምክንያት ሊደርስ የሚችልን ችግር ከወዲሁ እንዲገነዘቡና ለችግረኞችም ተፈላጊውን እንክብካቤ እንዲያደርጉ ያግዛቸዋል፡፡ በመሆኑም ደራሲው ወደፊትም እንደዚህ አይነት በይነ ዲሲፕሊናዊነት ያላቸውን ጽሑፎች ለአንባቢያን ቢያቀርቡ እውቀታቸውን ለማካፈል ያስችላቸዋል፡፡

ተደራስያን ልቦለዱን በሚያነቡበት ወቅት በገፀባህርያት ላይ የሚስተዋለው የሰብእና መዛባት ከሰብእና አወቃቀራቸው ጋር የሚያያዝ እንደሆነና የሰብእና መዛባቱ የሚፈጥርባቸውን ውጥረት ለመቀነስም ሥነ ልቦናዊ የጭንቀት መከላከያ ዘዴዎችን ተግባራዊ እንደሚያደርጉ ከግምት ውስጥ እያስገቡ ንባባቸውን ቢያካሒዱ ጽሑፉን ለመረዳት ያስችላቸዋል፡፡ እንዲሁም ሰብእና በጭብጥነት የገባና በቴክኒክ ረገድ ደግሞ በተለይ ንግርንና ምልሰት ለመገንባት ጥቅም ላይ እንደዋለ ከግምት ውስጥ እያስገቡ ንባባቸውን ቢያካሒዱ ይዘቱን ለመረዳት ግልጽነትን ይፈጥርላቸዋል፡፡

ወደ ፊት ጥናታቸውን በሰብእና ዙሪያ የሚያደርጉ ተመራማሪዎች የሥነ ጽሑፍ ስራው ከደራሲው ሰብእና ጋር ያለውን ዝምድና እንዲሁም የሥነ ጽሑፍ ስራው በተደራስያን ሰብእና ላይ ሊያሳድር የሚችለውን ተጽዕኖ ቢመለከቱ ከዚህ ጥናት የተለየ ግኝትን ሊያበረክቱ ይችላሉ የሚሉት በአስተያየትነት የቀረቡ ሀሳቦች ናቸው፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች


ምህረት ደበበ። (2010)። *ሌላ ሰው* (10ኛ እትም)። አዲስ አበባ፣ ርኆቦት አታሚዎች።

ቴዎድሮስ አለበል። (2006)። *‹‹ልጅነት›› በማሕሌትና አለንጋና ምስር፤ ሥነ ልቡናዊ ንባብ* (ያልታተመ ለኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት)። አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

ቴዎድሮስ ገብሬ። (2001)። *በይነ ዲሲፕሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባብ*፡ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ። (1948)። *መጽሐፈ፡ሰዋስው፡ወግስ፡ወመዝገበ፡ቃላት፡ሐዲስ*፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

Abrhams, M. H. (1999). *A Glossary of Literary Terms* (7th ed.). Heinle & Heinle: Cornell University.

Aras, G. (2015). Personality and Individual Differences: Literature in Psychology-Psychology in Literature. Elsevier Ltd. *Procedia - Social and Behavioral Sciences* 185 (2015) 250 - 25.

Barlow, D. H. and Durand, V. M. (2015). *Abnormal Psychology: An Integrative Approach*(7th ed.). Australia, Brazil, Mexico, Singapore, United Kingdom, United States: Cengage Learning.

Bienvenu, O. J. (2011). Personality and Psychopathology. Institute of Psychiatry. *International Review of Psychiatry*, June 2011; 23: 234–247. DOI: 10.3109/09540261.2011.588692.

Burger, J. M. (2010). *Personality* (8th ed.). Australia, Brazil, Japan, Korea, Mexico, Singapore, Spain, United Kingdom, United States: Cengage Learning Inc.

Cloninger, C. R. (2005). Antisocial Personality Disorder: A Review. In Maj M., Akiskal H.S., Mezzich J.E., and Okasha A. (Eds.), *Personality Disorders*. (P.125-169). England: John Wiley and Sons Ltd.

Cloninger, S. (2009). Conceptual issues in personality theory. In Corr P. J. and Matthews G. (Eds.). *The Cambridge Handbook of Personality Psychology*. (P.3-26). New York: Cambridge University Press.

Cudden, J. A. (1999). *The Penguin Dictionary of Literary Terms and Literary Theory*. 5th ed. England, Blackwell Ltd Publishers.

Ellis, A., Abram M. and Abrams L. D. (2009). *Personality Theories: Critical Perspective*. Los Angeles, London, New Delhi, Singapore: Sage Publication Inc.

Faisal. (2011). *Analysis of Main Character in Bruce Almighty Movie Viewed from Personality Traits Theory by Costa and McCrae* (Unpublished Thesis Submitted to Faculty of Adab and Humanities in Partial Fulfillment of the Requirements for the Degree Strata). State Islamic University “Syarif Hidayatullah”: Jakarta.

Fauziyah, N. (2008). *Psychological Analysis of Character’s Personality in Go Ask Alice* (Unpublished Thesis Partial Fulfillment of the Requirement for the Degree of Sargana Sastra). The State Islamic University of Malang.

Flekova, L. and Gurevych I. (2015). Association for Computational Linguistics. Lisbon: Portugal. *Proceedings of the 2015 Conference on Empirical Methods in Natural Language Processing*, pages 1805-1816.

Gask, L., Evans M. and Kessler D. (2013). Personality disorder. BMJ. *British Medical Journal*, Vol. 347, No. 7924 (14 September 2013), pp. 28-32.

Gbenoba, F. E. and Okoroegbe F. N. (2014). *Literary Theory and criticism.* Nigeria: National Open University of Nigeria.

Gill, C. (1986). The Question of Character and Personality in Greek Tragedy. Duke University Press. *Poetics Today*, Vol. 7, No. 2 (1986), pp. 251-273.

Habib, M. A. R. (2005). *Modern Literary Criticism and Theory*. Blackwell Publishing Ltd.

Hampson, E. (1988). *The Construction of Personality an Introduction*. Second edition (2nd ed.). London and New York: Rutledge.

Jess, F. and Gregory F. J. (2006). Theories of Personality (6th ed.). New York: McGraw Hill.

Johnson, J. A., Carroll J., Gottschall J. and Kruger D. (2010). Portrayal of personality in Victorian novels reflects modern research findings but amplifies the significance of agreeableness. Elsevier. *Journal of Research in Personality*. xxx (2010) xxx–xxx. doi:10.1016/j.jrp.2010.11.011.

Kusumawati, P. F. (2013). The Personality of the Main Character as Reflected in Paulo Coelho's the Devil and Miss Prym: A Psychological Study. *Muhammadiyah University of Metro*. Vol. 2 No. 2, October 2013, PP 158-168.

Lawrie, R. (1974). Personality. International Phenomenological Society. Philosophy and Phenomenological Research, Vol. 34, No. 3 (Mar., 1974), pp. 307-330.

Lenzenweger, M. F. and Clarkin J. F. (Eds) (2005). *Major Theories of Personality Disorder* (2nd ed.). New York: Guilfford Press.

McAdams, D. P. (1997). A Conceptual History of Personality Psychology. In Hogan R., Johnson J. and Briggs S. (Eds.), *Hand Book of Personality Psychology*. (P.1-29). San Diego: Acadamic Press.

McAdams, D. P. (2007). The Role of Theory in Personality Research. In Robins R. W., Robins R. C. and Krueger R. F. (Eds.). *Handbook of Research Methods in Personality Psychology*. (P.3- 20). New York and London: The Guilford Press.

Montes, J. M. and Alvarez M. P. (2004). Personality as A Work of Art. Elsevier. *New Ideas in Psychology* 22 (2004) 157-173.

Parnas, J., Licht D. and Bovet P. (2005). Cluster A Personality Disorders: A Review. In Maj M., Akiskal H.S., Mezzich J.E., and Okasha A. (Eds.), *Personality Disorders*. (P.1-74). England: John Wiley and Sons Ltd.

Paulhus, D. L., Fridhandler B. and Hayes S. (1997). Psychological Defense: Contemporary Theory and Research. In Hogan R., Johnson J. and Briggs S. (Eds.) *Hand Book of Personality Psychology*. (P544-580) San Diego London Boston New York Sydney Tokyo Toronto: Academic Press.

Robinson, J. M. (1985). Style and Personality in the Literary Work. Duke University Press. *The Philosophical Review*, Vol. 94, No. 2 (Apr., 1985), pp. 227-247.

Ronningstam, E. (2005). Narcissistic Personality Disorder: A Review. In Maj M., Akiskal H.S., Mezzich J.E., and Okasha A. (Eds.), *Personality Disorders*. (P.277-327). England: John Wiley and Sons Ltd.

Stone, M. H. (2005). Borderline and Histrionic Personality Disorders: A Review. In Maj M., Akiskal H.S., Mezzich J.E., and Okasha A. (Eds.), *Personality Disorders*. (P.2001-231). England: John Wiley and Sons Ltd.

Susan, C. (2009). Conceptual Issues in Personality Theory. In Philp, J. C. and Gerald M. (Eds). The Cambridge Handbook of Personality Psychology. (P.3-26). Cambridge University Press.

Taye Assefa and Shiferaw Bekele. (2000). The Study of Amharic Literature: An Overview. Institute of Ethiopian Studies. *Journal of Ethiopian Studies*, Vol. 33, No. 2, Special Issue Dedicated to the XIVth International Conference of Ethiopian Studies (November 2000), pp. 27-73.

Tyrer, P. (2005). The Anxious Cluster of Personality Disorders: A Review. In Maj M., Akiskal H.S., Mezzich J.E., and Okasha A. (Eds.), *Personality Disorders*. (PP.349-375). England: John Wiley and Sons Ltd.

Tyson, L. (2006). *Critical Theory Today: AUser-Friendly Guide* (2nd ed.). New York: Routledge.

Wellek, R. and Warren A. (1949). *Theory of Literature*. New York: Harcourt, Brace And Company Inc.

Winter, D.G. and Barenbaum N. (1999). History of Modern Personality Theory and Research. In Pervin, L.A. and Jhon, O.P. (Eds). *Handbook of Personality Theory and Research* (2nd ed) (PP.3-30). New York: The Guilford Press.